# ክብርት ቤተ ክርስቲያን




ፓ/ር ዶ/ር ተስፋ ወርቅነህ

# ክብርት ቤተ ክርስቲያን

በፓር. ዶር. ተስፋ ወርቅነህ

1996 ዓ.ም

The Glorious Church

By Rev. Dr. Tesfa Workeneh

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

© Tesfa Workeneh - 2004

8526 Northern St., Houston, TX 77071, USA

የሽፋን ዲዛይን :- አንተነህ አያሌው



## አበርክቶ

ወርቅ ወርቅነቱ የሚታወቀው በእሳት ተፈትኖ ሲወጣ ነው። ሻይም ሻይነቱ የሚታወቀውና ቅላቱ የሚወጣው ቀዝቃዛ ሳይሆን የፈላ ውሃ ሲፈስበት ብቻ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ በብዙ መከራና ስደት ውስጥ አልፋለች። ይሁን እንጂ በውስጥዋ የሚንፀባረቀውን የክርስቶስን ክብር ሊያጠፋው የቻለ ምንም ኃይል አልተገኘም። መሥራቿ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉዋትም» እንዳለው እንዲሁ ሆኖዋል።

ይህችን መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ስደት ውስጥ ባለፈችበት ወቅት በመከራ እሳት ውስጥ ሲያልፉ ፀንተው በመቆም ምሳሌ ለሆኑት፤ ለመጋቢ ተሾመ ወርቁ፥ ለመጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶና እንደ እነርሱ ዋጋ ለከፈሉ ቅዱሳን ሁሉ መታሰቢያ እንድትሆን አበረክታለሁ።

ደራሲው

## ምስጋና

ይህንን ትምህርት ለማዘጋጀት ምክንያት የሆኑኝን «የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን» በሂውስተን ምዕመናንን እና ትምህርቱ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ እንዲቀርብ ለአበረታቱኝ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

በተጨማሪም ጽሑፉን በኮምፒዩተር በማዘጋጀት የረዳችኝን ወሮ. ገነት ሙሉጌታን፤ በማንበብና በማረም የረዱኝን ባለቤቴን ወሮ. ውሂብ ዘውዱን፥ ፓስተር ኅሩይ ጽጌንና ወጣት ናይእግዚ ኅሩይን ከልብ አመሰግናለሁ።



# ክብርት ቤተ ክርስቲያን

## ማውጫ


| ምዕራፍ | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | 7 |
| 1. | የቤተ ክርስቲያን ማንነት | 9 |
| 2. | የቤተ ክርስቲያን አጀማመር | 14 |
| 3. | ክብርት ቤተ ክርስቲያን | 17 |
| 4. | ዓለም አቀፏና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን | 23 |
| 5. | ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችባቸው ምሳሌዎች | 28 |
| 6. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና አባሎችዋ | 38 |
| 7. | ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት የሚያበቁ መመዘኛዎች | 47 |
| 8. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አደረጃጀትና አገልጋዮችዋ | 50 |
| 9. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ | 57 |
| 10. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት | 62 |
| 11. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስትመርጥ | 66 |
| 12. | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሃላፊነት | 71 |
| 13. | የመንፈስን አንድነት መጠበቅ | 87 |
| 14. | የቤተ ክርስቲያን ዲሲፕሊን | 105 |

«... በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት፤ ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን፤ ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» (ኤፌ. 5፥25-27)።



# መግቢያ

የቤተ ክርስቲያንን ማንነትና የቤተ ክርስቲያንም አባልነት ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ማወቅ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ስለ አንድ ነገር ምንነት ትክክለኛ እውቀትና መረዳት ከሌለ ውጤቱ ሁል ጊዜ ችግርና ጥፋት ነው። አለማወቅ የበርካታ ችግርና ጥፋት ምንጭ ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በትንቢተ ሆሴዕ ላይ፥ «ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል» የሚለው (4፥6)።

ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ሰዎች ሊያደርሱት ስለሚችሉት ጥፋት ባሰብኩ ቍጥር ትዝ የሚለኝ፥ እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ ዓመታት ውስጥ «የኢየሱስ ንቅናቄ» (The Jesus Movement) በሚባለው እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩት ወጣቶች አንግበው ይዞሩት የነበረው መፈክር ነው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው በዚህ ጉዳይ ሲጽፉ፥ «ወጣቶቹ በሕዝብ አደባባዮችና የመናፈሻ ስፍራዎች ስብሰባ በማድረግ የተለያዩ መፈክሮች ያሰሙ ነበር። ለሕዝብ እንዲነበብ አንግበው ይዞሩ ከነበሩት መፈክር አንዱ ‹እሺ! ለኢየሱስ፤ እምቢ! ለቤተ ክርስቲያን› የሚል ነበር»። ለኢየሱስ «እሺ» ብሎ ለቤተ ክርስቲያን «እምቢ» ማለት ይቻላልን? የሚገርም ነው!

እነዚያ ወጣቶች ለምን እንደዚህ እንደተሰማቸውና ፀረ ቤተ ክርስቲያን የሆነ አቋም እንዲይዙ እንደተገፋፉ ምክንያታቸውን መርምሮ ማወቅ አስቸጋሪ አይደለም። ነገር ግን እኔ ለመጥቀስ የፈለግኩት ማንም የኢየሱስ ወዳጅ ሆኖ ፀረ ቤተ ክርስቲያን አቋም መያዝ የማይችል መሆኑን ለማስረዳት ስለሆነ፤ እዚያ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ አይደለም። ወጣቶቹ ያነግቡና በተግባርም ይገልጹት የነበረው መፈክር እርስ በርሱ የሚቃረን (Paradox) አካሄድ ነው። ለኢየሱስ «እሺ» ብሎ ለቤተ ክርስቲያን «እምቢ» ማለት ፈጽሞ አይቻልም። ማንም ፀረ ቤተ ክርስቲያን የሆነ አቋም እየተከተለ ኢየሱስን አስደስታለሁ ብሎ ቢያስብ ድንቍርና ነው። እውነትም በትንቢተ ሆሴዕ እንደተባለው አለማወቅ አጥፊ ነው።

ለኢየሱስ እየዘመሩ ፀረ ቤተ ክርስቲያን መሆን የሚቻል ይመስላቸው የነበሩት የእነዚያ ወጣቶች እንቅስቃሴ ያለፈ ነገር በመሆኑ ዝርዝሩን ለታሪክ መተው አስፈላጊ ነው። ይሁንና ትናንት በእነዚያ ወጣቶች በአለማወቅ በቤተ ክርስቲያን ህልውና ላይ ይደረግ የነበረው የተቃውሞ ዘመቻ፥ ዛሬም በሚገኘው ትውልድ እንዳይደገምና የሚታዩት ተመሳሳይ ክስተቶች ሥር እንዳይሰዱ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ምንነት፥ በቤተ

ክርስቲያንና በክርስቶስ፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያንና በምእመኖቿ መካከል ስላለው ግንኙነት መወያየት አስፈላጊ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሳስብ አንድ ሸክም ይሰማኛል። ይህም ዛሬ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚገኙት ክርስቲያኖች አብዛኞዎቹ የዳኑት፥ ብዙዎቹ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው በነበረበት የስደት ዘመን ውስጥ ነው። ቤተ ክርስቲያን በስደት ላይ ስለነበረች የቤተ ክርስቲያንን ወግና ሥርዓት በቅርብ ለማወቅ ዕድሉ አልነበረም። ከዚህም የተነሣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አሠራር የማይረዱት ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዛሬ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያም ውጭ በሚገኙት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በመከሰት ላይ ያለው አንዳንድ ችግር :- ጌታን ካወቁበት ወቅት ጀምሮ በአግባቡ ደቀ መዝሙር ሆኖ አለማደግ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት፥ ስለ ሥርዓትና ወግዋ ጠንቅቆ ከአለማወቅ የተነሣ የመጣ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ይህ የእኔ ግምት ነው፤ ማንም በአሳቡ ላይስማማ ይችላል። እንደ ቃሉ የሆነው ወግና ልምምድ በተግባር ላይ ሲውል አለማየትና የቃሉ እውቀት ጉድለት፥ አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር በሚኖረው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ አለው።

እንደ ቤተ ክርስቲያን መጋቢነቴ በርካታ ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው አመለካከት ለእቁብ፥ ለእድር፥ ለማኅበር ካላቸው አመለካከት ያልተለየ እንደሆነ ተገንዝቤአለሁ። በተለይም በኢትዮጵያ አብዮት ከተካሄደ በኋላ አንዳንዶች ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ያላቸው አተያይ ስለተለወጠ የመሪዎችን ምክርና ትምህርት ከመስማት ይልቅ ማመፅና የመንፈስን አንድነት ማናጋት እንደሚቀላቸው አይቻለሁ። በልዩ ልዩ ከተማዎች ለማስተማር ስዞር ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት፥ ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና አባሎቿ፥ እንዲሁም ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸው ትልቅ አለመረዳት እንዳለ ተገንዝቤአለሁ። ዛሬ ይህ አለማወቅና አለመረዳት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ችግር ውስጥ ጥሏታል።

ይህንን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍና ለማቅናት በማሰብ የበኩሌን አስተዋጽዖ ማድረግ ስለሚገባኝ፤ በማገለግላት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዚህ ርዕስ ላይ የማስተማር ግዴታ ነበረብኝ። ይህም ጽሑፍ የቀረበው «የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና አባሎቿ» በሚል ርዕስ ለሦስት ወራት ያህል በተከታታይ ከሰጠሁት ከተጠቀሰው ትምህርት ነው። ትምህርቱ በመጽሐፍ መልክ ቢቀርብ ለብዙ ሰዎች ጥቅም እንደሚሰጥ በማመን በዚህ መልክ አቅርቤዋለሁ። የሚያነቡት ሁሉ ደግሞ በመታዘዝ የሚገኘውን በረከት እንዲያተርፉበት ጸሎቴ ነው።



## ምዕራፍ አንድ

# የቤተ ክርስቲያን ማንነት

ዛሬ ሰዎች «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል በልማድ ለተለያየ ነገር ይጠቀሙበታል። «ቤተ ክርስቲያን» ሲሉ የሚያስቡትን ነገር ሁሉ ለመዘርዘር ጊዜ ይወስዳል። ስለሆነም «ዌብስተር ዲክሽነሪ» የተባለውና ሌሎቹም የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት «ቤተ ክርስቲያን» ለሚለው ቃል ከሚሰጡት ትርጉሞች መካከል ሦስት ያህሉን ብቻ አቀርባለሁ።

- ሕዝብ ለአምልኮ የሚሰበሰብበት ሕንፃ (Building for public Worship)
- አንድ የክርስትና ቤተ እምነት (A particular denomination or sect of Christians)
- በአንድ ላይ የተሰበሰቡ አምላኪዎች (A group of Worshipers)።

በእነዚህ ትርጉሞች መሠረት ሰዎች ተሰብስበው «የሚያመልኩት ምንም ቢሆን» «የሚመለክበት ስፍራ» ቤተ ክርስቲያን ይባላል ማለት ነው። ለምሳሌ፥ በምዕራቡ ዓለም ሰዎች ተሰብስበው ሰይጣንን የሚያመልኩበት ስፍራ «የሰይጣን ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ ይጠራል።

እኛም ክርስቲያኖች «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል በተለያየ መልኩ በዘወትር ንግግሮቻችን እንጠቀምበታለን።

«ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ስብሰባ አለ»

«እሁድ ቤተ ክርስቲያን እንገናኝ» ወዘተ።

እንደዚህ በምንነጋገርበት ጊዜ ሁሉ ከላይ በጠቀስናቸው መዝገበ ቃላት የተሰጡትን ትርጉሞች ማንፀባረቃችን ነው። «ቤተ ክርስቲያን» ስንል የምንናገረው ስለ መሰብሰቢያ ሕንፃ ነው።

«የእግዚአብሔር ጉባዔ ቤተ ክርስቲያን»

«ፕሪስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን»

«ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን»

«መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን»

«መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን» ወዘተ. ስንል ደግሞ ስለ አንድ የክርስትና ቤተ እምነት (Denomination) መጥቀሳችን ነው።

ከዚህ መረዳት እንደምንችለው በዕለታዊ ንግግሮቻችን ቃሉን የምንጠቀምበት መንገድ ራሱ እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን ትርጉም እንዳናውቅ ግርዶሽ ሆኗል። ለቃሉ የሰጠነው ትርጉም ከእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ትርጉም ጋር አይገናኝም። ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት መወያየትና መማር የሚያስፈልገው ለዚህ ነው።

የእንግሊዝኛው ቃል "Church" (ቤተ ክርስቲያን) የተገኘው፥ «ኩርያኮስ» (Kuriakos) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ትርጉሙ «የጌታ መሆን» (belonging to the Lord) ማለት ነው። በግሪክኛው አዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል የተጠቀሰው ሁለት ጊዜ ነው። ይህም በ1ቆሮንቶስ 11፥20 ላይ ስለ «ጌታ እራት» እና በራእይ 1፥10 ላይ ስለ «ጌታ ቀን» ብቻ ነው። ኩርያኮስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድም ቦታ ቤተ ክርስቲያንን ለመጥቀስ አልዋለም። «ቲውቶኒክ» የተባሉ ነገዶች የክርስትናን እምነት ከተቀበሉ በኋላ ኩርያኮን የሚለውን የግሪክ ቃል የመሰብሰቢያ ሕንፃዎቻቸውን ለማመልከት ተጠቅመውበታል። እንደዚሁም ጀርመኖች የመሰብሰቢያ ሕንፃዎቻቸውን ኪርኽ "Kirche" እያሉ ሲጠሩ፥ እስኮቲሾች ደግሞ ኪርክ "Kirk" ይላሉ። ምንም እንኳን በዚህ ዐይነት «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ለአምልኮ መሰብሰቢያ ቦታዎች የተጠቀሙ ቢኖሩም በግሪክኛው አዲስ ኪዳን ውስጥ አንድም ቦታ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ተጠቅሞ አያውቅም።

የቤተ ክርስቲያንን ማንነት በተመለከተ በመጀመሪያ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር፥ «ቤተ ክርስቲያን» የአምልኮ መሰብሰቢያ ሕንፃ ማለት እንዳልሆነ ነው። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በሕንፃ ውስጥ ለመሰብሰብ ትችላለች፤ ነገር ግን የመሰብሰቢያ ሕንፃ አይደለችም። የሚከተሉትን ጥቂት ጥቅሶች በማየት ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንፃው እንዳልሆነ እንመልከት ፦

ሀ) ሐ.ሥ. 12፥5 ፦ «ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።» በዚህ ቦታ ጸሎት ይደረግ የነበረው ታስሮ ለነበረው ጴጥሮስ ነበር። ‹ቤተ ክርስቲያን› ማለት ሕንፃ ከሆነ ሕንፃ ለመጸለይ ይችላል ወይ? መልሱ አይችልም ነው። ሰዎች እንጂ ግዑዝ ሕንፃ ጸሎት ማድረግ አይችልም።

ለ) ሐ.ሥ. 15፥4 ፦ «ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎችም ተቀበሏቸው።» ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጡ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተ ክርስቲያን ጋር



አቀባበል እንዳደረጉላቸው እናያለን። ሕንፃ አቀባበል ማድረግ ይችላልን? ሰዎች እንጂ ሕንፃ «እንኳን ደህና መጣችሁ» በማለት ለሰዎች አቀባበል ማድረግ አይችልም።

ሐ) ሐ.ሥ. 15፥31 ፦ «ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሣ ደስ አላቸው» ሕንፃ ደስ ሊለው ይችላልን? ከሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን የተጻፈው ደብዳቤ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሲነበብ ምእመኑን ደስ አሰኛቸው። ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንፃው ቢሆን ኖሮ ደስ መሰኘት ባልቻለም ነበር።

መ) ሮሜ 16፥16 ፦ «የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሠላምታ ያቀርቡላችኋል» ሕንፃ ሰላምታ መላክ ይችላል? አይችልም።

ሠ) 1ቆሮ. 15፥9 ፦ «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ...» ይህንን የተናገረው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ቤተ ክርስቲያንን አሳድጃለሁ ሲል ስለ ሕንፃ መናገሩ አይደለም። ሰዎች እንጂ ሕንፃ አይሰደድም።

ረ) 1ቆሮ. 16፥19 ፦ «የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ካለች ቤተ ክርስቲያን ጋር በጌታ እጅግ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል» እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቤቱን ቢሆን ኖሮ ቤቱ በቤቱ ውስጥ ይኖራል ማለት ይሆናል። ጳውሎስ ግን የሚናገረው በአቂላና ጵርስቅላ ቤት ውስጥ ስላለ ቤት ሳይሆን በዚያ ይሰበሰቡ ስለነበሩት ቅዱሳን ነው።

ሰ) ራእ. 2፥23 ፦ «አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደሆንሁ ያውቃሉ» ሕንፃ እግዚአብሔር ልብና ኵላሊትን እንደሚመረምር ሊያውቅ ይችላልን? መልሱ አይችልም ነው።

በ1ቆሮ. 3፥9 እና 1ጴጥ. 2፥5 በመሳሰሉት ጥቅሶች ላይ እንደምናነበው ቤተ ክርስቲያን በሕንፃ መልክ ቀርባለች። ነገር ግን ቀደም ብለን እንዳልነው በእነዚህ ቦታዎች ሕንፃ ተብለው የተጠሩት ሕይወት ያላቸው ነገሮች እንጂ ግዑዝ የሆነው ድንጋይና ሸክላ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ከሕያዋን ድንጋዮች የተሠራች የእግዚአብሔር ሕንፃ ናት። እያንዳንዱ አማኝ (ሕያው ድንጋይ) የዚህችን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አካል ይሠራል። ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ተቋም ቢኖራትም፥ ድርጅት (Organization) ግን አይደለችም። ሕይወት ካላቸው ክፍሎች የተገነባች አካል (An Organism) ናት።

## የቤተ ክርስቲያን ትርጉም

«ቤተ ክርስቲያን» (Church) የሚለው ቃል የመጣው «ኤክሌሲያ (EKKLESIA) ከሚለው ሁለት የግሪክ ጥምር ቃላት ሲሆን ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው :-

ኤክ (EK) ማለት የወጡ (out of),

ኪሲስ (KESIS) ማለት መጠራት (a calling/kaleo = to call) ማለት ነው።

ስለዚህ «ኤክሌሲያ» ማለት «ተጠርተው የወጡ» ወይም «የተጠሩና የወጡ» (Summoned assembly) ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን በባርነት ይኖሩበት ከነበረው አገርና ሁኔታ ተጠርተው እንደወጡ (ሐ.ሥ. 7፥38)፥ ቤተ ክርስቲያንም ከባርነት ዓለም ተጠርተው የወጡ ሰዎችን የያዘች አካል ናት። (ሮሜ 6፥20፤ ገላ. 5፥1) እስራኤላውያን ከግብጽ የተጠሩትና የወጡት ለመውጣት ያህል ብቻ አይደለም፤ እግዚአብሔር ወደሚመራቸው ምድር ገብተው በነፃነት እንዲያመልኩትና እንዲያገለግሉት ነው። እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያን (ክርስቲያኖች) 1ጴጥ. 2፥9 ላይ እንደምናነበው የተጠራነውና የወጣነው ከጨለማው ሲሆን፤ መድረሻውም ወደሚደነቀው ብርሃን ነው። ይህ መጠራትና መውጣት ዓላማ አለው። ጴጥሮስ «የእርሱን በጐነት እንድትነግሩ» ነው በማለት ተጠርተን የወጣንበትን ዓላማ ይገልጸዋል።

በማቴዎስ 16፥18፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ሲጠቀም፥ ቃሉ «ኩርያኮን» የሚለው ሳይሆን «ኤክሌሲያ» የሚለው የግሪክ ቃል ነበር። ጌታ የተጠቀመበት ይህ ቃል ቀድሞ ያልነበረ አዲስ ቃል አይደለም። ቃሉ በአይሁዶችም ሆነ በግሪኮች ዘንድ የታወቀና የተለመደ ቃል ነበር። በዚያን ዘመን ለሃይማኖት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ዐይነት ዓላማ ተጠርቶ የሚሰበሰብ ማንኛውም ዐይነት ጉባዔ ሁሉ «ኤክሌሲያ» ተብሎ ይጠራ ነበር። (ሐ.ሥ. 7፥38፤ 19፥32:39 ይመልከቱ)። ለምሳሌም ሐ.ሥ. 19፥32 ላይ በኤፌሶን ከተማ ድሜጥሮስ የተባለው አንጥረኛ ቅስቀሳ አድርጎ በጳውሎስ ላይ ያስነሣው የአመፅ ጉባኤ በግሪኩ አዲስ ኪዳን ኤክሌሲያ ተብሎ ተጠርቷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ትርጉሙ በጊዜው ለነበሩ ሰዎች ግልጽ የሆነና የሚገባ የነበረውን ይህን ቃል ወስዶ ለራሱ የሚሆን አዲስ ሕዝብ እንደሚጠራና እንደሚሰበሰብ ገለጸበት።



ከዚህ አኳያ፤ «ኤክሌሲያ» ወይም ‹ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሁለት መንገድ ጥቅም ላይ ውሏል።

ሀ) 99 ጊዜ ያህል ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተጠቅሷል።

ምሳሌ፤

- የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን (ሐ.ሥ. 8፥1)
- የገላትያ ቤተ ክርስቲያን (ገላ. 1፥2)
- የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን (ሐ.ሥ. 13፥1)
- የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን (1ቆሮ. 1፥2፤ 2ቆሮ. 1፥1) ወዘተ.

ለ) 23 ጊዜ ያህል ደግሞ ዳግም የተወለዱትን አማኞች ሁሉ ለምታቅፈው የክርስቶስ አካል ለሆነችው አንዲቷ ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ተጠቅሷል። (ማቴ. 16፥18፤ ሐ.ሥ. 8፥3፤ ኤፌ. 1፥22:23፤ ቈላ. 1፥18፤ ወዘተ)።

የክርስቶስ አካል የምንላት ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን የምታካትተው ከዘር፥ ከቋንቋ፥ ከነገድ ሁሉ የተውጣጡትን አማኞች ነው። እነርሱም፤

- አምነው የሞቱት ክርስቲያኖች ሁሉ (በድል እረፍት ላይ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን (The church triumphant)
- በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ የምትገኘውን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን፤
- ክርስቶስ ወደ ምድር እስኪመጣና ቤተ ክርስቲያንን እስኪወስድ ድረስ ገና ወደፊት የሚድኑት አማኞች ሁሉ ናቸው።

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (ኤክሌሲያ) ከላይ እንደገለጽነው፤ ያለፉትን፥ የአሁኖቹንና ወደፊት የሚድኑትን ሁሉ የምታቅፍ አንዲት አካል ናት። እውነተኛ ማንነትዋን ማወቅና መገንዘብ ስለ እርስዋ ያለን አመለካከት የተዛባ እንዳይሆን ይጠብቀናል።

## ምዕራፍ ሁለት

# የቤተ ክርስቲያን አጀማመር

ማንኛውም ተቋም ጅማሬና ጀማሪ አለው። ቤተ ክርስቲያንም በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተችበት ጊዜና የመሠረታት መሥራች አላት። ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱና የመጣበትንም ሥራ ከመፈጸሙ በፊት ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ አልነበረችም። ቤተ ክርስቲያን፥ ክርስትና፥ ክርስቲያንም በምድር ላይ መገኘት የቻሉት ከክርስቶስ የተነሣ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ይባሉ እንደነበር የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ይሠራ የነበረው ከመረጣቸውና «ሕዝቤ» ብሎ ከጠራቸው ከእነዚህ ሰዎች ጋር ነበር። ብሉይ ኪዳን ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ስለ መምጣቱ (ልደቱ)፥ ስለ ሞቱና ትንሣኤው፥ እንዲሁም ስለ አሕዛብም መዳን ይናገራል። ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያንና በእርሷም ውስጥ ስለሚሆኑት ነገሮች የሚናገረው ምንም የለም። ምክንያቱም ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ከዘላለም በፊት በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ የነበረ አሳብ ቢሆንም (ኤፌ. 3፥10-12)፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩት ቅዱሳን ግን ምሥጢር ሆኖ የቆየ ነገር ነበር። ምሥጢር ከሆነም የሚታወቅ ነገር አልነበረም ማለት ነው፤ (ሮሜ 16፥25-26፤ ኤፌ. 3፥1-12፤ 5፥25-32)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መስቀል ከማምራቱና ቤተ ክርስቲያንም በምድር ላይ ከመመሥረቷ በፊት በማቴዎስ 16፥18 ከጴጥሮስ ጋር ሲነጋገር «አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሀነም ደጆችም አይችሉአትም» በማለት ቤተ ክርስቲያኑን በምድር ላይ እንደሚመሠርት ተናገረ። «እመሠርታለሁ» ሲል በወደፊት ጊዜ የተናገረው ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው የመስቀሉን ሥራ ከጨረሰ በኋላ ስለሆነ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በዚህ ጥቅስ ላይ ተመርኲዘው ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በጴጥሮስ ላይ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን የግሪክኛውን አዲስ ኪዳን መመልከት፥ ቤተ ክርስቲያን በጴጥሮስ ላይ ነው ተመሠረተችው ከሚለው ስሕተት ይጠብቃል። ጴጥሮስ (Peter) የሚለው ስም በግሪክኛ የሚባለው Petros ነው። ደግሞም በግሪክኛ



«ፔትራ» (Petra) ማለት «ዓለት» ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ቢሆኑም የትርጉም ልዩነት አላቸው። «ጴጥሮስ»፥ «ትንሽ ድንጋይ» ማለት ሲሆን፥ «ፔትራ» ግን «ትልቅ ዓለት» ማለት ነው። ጌታ «ቤተ ክርስቲያኔን» እመሠርታለሁ ያለው በዐለቱ ላይ ነው። ስለሆነም ጌታ በትንሹ ድንጋይ በጴጥሮስ ላይ ቤተ ክርስቲያኑን መሠረተ ብሎ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። ጌታ «ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» ያለው በጴጥሮስ ላይ ሳይሆን ቀደም ብሎ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ማንነት፥ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» (ማቴ. 16፥16) ሲል በመሰከረለት ጽኑ ዐለት፥ በክርስቶስ ላይ ነው። በአጭሩ፥ ጌታ «ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» ያለው በራሱ ላይ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በጴጥሮስ ላይ ብትመሠረት ኖሮ፥ ማለትም ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ሆኖ ቢሆን፥ የክርስትና እምነት የሚናጋና የሚፈራርስ ይሆን ነበር። ምክንያቱም ጴጥሮስ በባሕርዩ ወላዋይ ስለነበር ጽኑ መሠረት ሊሆን አይችልም። በዚሁ በማቴዎስ ምዕራፍ 16 ላይ እንኳን ከቍጥር 22-23 የተጻፈውን ስንመለከት፥ ጌታ ለቤተ ክርስቲያን መመሥረት አስፈላጊ ስለሆነው የመስቀል ሞቱ ሲናገር ጴጥሮስ ጌታን ለብቻ ገለል አድርጎ «አይሁንብህ» እያለ ሲገሥጸው እናያለን። ጌታም ለጴጥሮስ «አንተ ሰይጣን ከአጠገቤ ዘወር በል የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብም» ሲል ይመልስለታል። በዚህ በጴጥሮስና በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መካከል በተደረገው የቃል ልውውጥ፥ ጴጥሮስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ለመለዋወጥ እንደቻለ እናያለን። በተጨማሪም ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ ጌታውን እንደ ካደና በሌላ ጊዜ ደግሞ የሙሴን ሕግ በተመለከተ ሲያመቻምች በመገኘቱ በሐዋርያው ጳውሎስ እንደተገሠጸ እናያለን፤ (ገላ. 2፥11-14)። ይህ ሁሉ፥ እንደዚህ ጽናት የሌለው ዋዣቂ ሰው የቤተ ክርስቲያን መሠረት ለመሆን እንደማይችል ማስረጃ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት መመሥረት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይላል (1ቆሮ. 3፥11)። ጴጥሮስ ራሱም ይህንን እውነት በመረዳቱ፤ «መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» ሲል ያውጃል (ሐ.ሥ. 4፥12)።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተመሠረተችው በክርስቶስ ሲሆን፥ የተመሠረተችውም ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከአረገ ከአሥር ቀን በኋላ ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን፥ «እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል

እስክትቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሲል አዟቸው ነበር (ሉቃ. 24፥49)። የሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደምናነበው «በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር (ሐ.ሥ. 2፥1-5)።

በዚህ በዓለ ሃምሳ (ጴንጤቆስጤ) በተባለው ቀን ጴጥሮስ ተነሥቶ በአዩትና በሰሙት ግራ ለተጋቡት ሰዎች በሰበከው ስብከት ሦስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በመጠመቅ በደቀ መዛሙርቱ ቊጥር ላይ ተጨመሩ። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተመሠረተችው መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር በወረደበት በዚህ እ.ኤ.አ. 30 ዓ.ም ላይ በዋለው የጴንጤቆስጤ ቀን ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር የወረደበት የጴንጤቆስጤ ዕለት «የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን» በመባል ይታወቃል።

ጴጥሮስና ሌሎቹ የክርስቶስ ተከታዮች ቀደም ሲል በክርስቶስ ቢያምኑም፤ እነርሱንና ከእነርሱ በኋላ የሚድኑትን ሁሉ የምታጠቃልለው አንዲቷ የክርስቶስ አካል ገና በምድር ላይ አልተመሠረተችም ነበር። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተመሠረተችውና በዓለም ሁሉ እየተስፋፋች የሄደችው፤ ዝርዝሩ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ጀምሮ እንደተተረከው ነው።



<u>*ምዕራፍ ሦስት*</u>

# ክብርት ቤተ ክርስቲያን
## (The Glorious Church)

*«ወዳጄ ሆይ! ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም፤» (መኃ.መኃ. 4፥7)*

ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ልዩ ችግሮች ሲከሰቱና ከቃሉ የወጣ እንግዳ ትምህርት ሲገባ ለማረምና ለማስተካከል ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መልእክት ጽፏል። ወደ ኤፌሶን ሰዎች የላከው መልእክት ግን ምንም ነገር ለማረምና ለማስተካከል ሳይሆን ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያንን ማንነትና በእግዚአብሔር ዘንድ ያላትን ቦታ እንዲያውቁ ለማስተማር የተጻፈ ነው። በዚህ መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ይዘታና በእግዚአብሔር ዐላማ ውስጥ ስላላት ልዩ ቦታ በሰፊው ገልጿል። ክብርት ቤተ ክርስቲያን የሚለው ሐረግ (ስያሜ) የወጣው ከዚህ ከኤፌሶን መልእክት ውስጥ ነው።

> «ባሎች ሆይ! ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቶቻችሁን ውደዱ። በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንበት
>
> ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን፤
>
> ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» (ኤፌ. 5፥25-27)።

ብዙ ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት የራሳቸው የሆነ የተለያየ አሳብ አላቸው። ዋናው ተፈላጊ ነገር ግን የሰዎች አሳብ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት ያለው አሳብ ነው። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የሚያያት እርሱ ራሱ ትሁን ብሎ ባሰባትና ባቀደላት መልኳ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ አምስት ላይ ስለ ባልና ሚስት፥ ስለ ወላጆችና ልጆች ግንኙነት ሲያስተምር ቈይቶ አሳቡን ከዚያ በማንሳት ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ስላለው ፍቅርና ዓላማ ላይ ያሳርፋል። ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብርትነት የገለጸው በዚህ ጊዜ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ «ክብርት ቤተ ክርስቲያን» ሲል ስለ አንድ ሕንፃ ወይም ስለ አንድ ክርስቲያናዊ ድርጅት መናገሩ አይደለም። «ክብርት ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ተጠርተው ስለወጡ፥ በደሙ ስለታጠቡና ዳግም ስለተወለዱ ሰዎች ነው። ቤተ ክርስቲያን ተጠርተው የወጡ ሰዎች ስብስብ ስለሆነች ሰብአዊ መልክ ቢኖራትም የክርስቶስ አካል ስለሆነች መለኮታዊነት አላት፤ ክብርትም ናት።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መናገር ለሰዎች አይከብዳቸውም፤ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ከሚታዩት ችግሮች የተነሣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር መናገር ይከብዳቸዋል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ተናግሮ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር ሳይናገሩ ዝም ማለት አይቻልም። የክብርዋ ሁሉ ምንጭ ክርስቶስ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ላይ ሌላ ምንም አቻ የሌላት ክብርት ናት።

ቤተ ክርስቲያንን ክብርት የሚያደርጓት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ) በአጀማመሯ ክብርት ናት

የቤተ ክርስቲያን ፅንሰ አሳብ የፈለቀው ከሰዎች አእምሮ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አእምሮ ነው። አሳቡ፥ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለመዋጀት በአቀደው እቅድ ውስጥ የተጠቃለለና በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም አሳብ ነው (ኤፌ. 3፥10-12)። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መለኮታዊ ፈቃዱ ውጤት ናት። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ እንዲህ ይላል :-

> «ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምስጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ» (ኤፌ. 3፥8-11)።

ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዓላማና አሳብ ውስጥ የነበረችና የተፈጠረች ናት። እግዚአብሔር ምንም ነገር ያለ ዐላማ ስለማይፈጥር ቤተ ክርስቲያንም ያለ ምክንያት ወደ መኖር የመጣች አይደለችም። ዓለም ሳይፈጠር በፊት እግዚአብሔር እርሷን ቅዱስና ነውር የሌላት እንድትሆን በክርስቶስ መረጣት (ኤፌ. 1፥4)። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር አሳብ ውስጥ ያለችና ለትልቅ ዘለዓለማዊ ዓላማ በምድር ላይ የተመሠረተች ሕያው የሆነች ክብርት ተቋም ናት።



### ለ) የመሠረታት መሥራችና የቆመችበት መሠረት ክብርት ያደርጋታል

ቤተ ክርስቲያን በሰው የተመሠረተች ተቋም አይደለችም። ስለዚህ በጴጥሮስ፥ በጳውሎስ፥ በሉተር፥ በዌስሊና በሌሎችም ሰዎች አልተመሠረተችም። ጴጥሮስ፥ ማቴዎስ 16፥16 ላይ እንደምናነበው «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ በመሰከረ ጊዜ፥ ስለሰጠው መልስ ጴጥሮስን ጌታ ከባረከው በኋላ «... በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ...» አለ (ማቴ. 16፥18)። ስለ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በተነገረው በዚህ ቃል ሦስት ነገሮች በማያሻማ መንገድ ቍልጭ ብለው ተቀምጠዋል። አንደኛ) ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ሌላ ማንም ሰው ሳይሆን ክርስቶስ ራሱ ነው። ሁለተኛ) «ቤተ ክርስቲያኔን» ስለሚል ቤተ ክርስቲያን የማንም ሳትሆን የክርስቶስ ብቻ ናት። ሦስተኛ) በምዕራፍ ሁለት በሰፊው እንዳብራራነው ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ጽኑ በሆነው ዐለት በራሱ በክርስቶስ ላይ ነው። በሰዎች ላይ ወይም በልዩ ልዩ አስተምህሮዎች (ዶክትሪን) ላይ አልተመሠረተችም፤ መሠረቷ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይላል (1ቆሮ. 3፥11)።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልና ሙሽራው ናት። የቆመችበት መሠረትና ራሷ እርሱ ነው። ቤተ ክርስቲያንን ራሷና መሠረቷ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ለይቶ መመልከት አይቻልም። የቤተ ክርስቲያን መሥራችና ራስ ክርስቶስ የከበረ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ስፍራዎች ያስተምረናል (ኤፌ. 1፥21-23፤ ፊልጵ. 2፥9-12፤ 1ጢሞ. 3፥16) ቤተ ክርስቲያን ክብርት የሆነችው ከዚህ መሥራችና መሠረቷም ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ክብር የተነሣ ነው።

### ሐ) የተገዛችበት ዋጋ ውድነት ክብርትነቷን ያሳያል

የቤተ ክርስቲያን ክብርትነት የሚታየው እሷን ለመግዛት የተከፈለውን ዋጋ ውድነት ስናጤን ነው። እሷን ለማግኘት ክርስቶስ ራሱን ሰጠ (ኤፌ. 5፥25)። በብርና በወርቅ ሳይሆን ሕይወቱን ለእርስዋ በማፍሰስ በከበረው ደሙ ገዛት (1ጴጥ. 1፥18፥ 19)። ቤተ ክርስቲያንን ለመግዛት በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈሰሰው ደም እጅግ ውድና ክቡር የሆነ መለኮታዊ ደም ነው (ሐ.ሥ. 20፥28)።

በኤደን ገነት እግዚአብሔር ለአዳም ከጎኑ አጥንት ምን የመሰለች ሙሽራ (ሔዋንን) ሠርቶ እንደሰጠው፤ በቀራንዮም እግዚአብሔር

ተመሳሳይ ተግባር ፈጸመ። ለሁለተኛው አዳም፥ ለተወደደው አንድያ ልጁ በመስቀል ላይ ከእጆቹ፥ ከእግሮቹ፥ ከጎኑና ከመላ አካሉ ከፈሰሰው ደም አካሉ የሆነችን ሙሽራ - ቤተ ክርስቲያንን ሠርቶ ሰጠው።

እቃ ለመግዛት ወደ ገበያ ስንወጣ የአንድ ነገር ክብር ከሚታይበትና ከሚለካበት መንገድ አንዱ ለእቃው የሚከፈለው ዋጋ እንደሆነ እናያለን። ውድ ነገር ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል። ቤተ ክርስቲያንንም ለመግዛት የተከፈለው ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው፤ የተከፈለው ወርቅና ብር ሳይሆን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ክቡር ደም ነው።

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ወደደ። ጌታ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ለመግለጽ አሥር ዓለማትን ፈጥሮ በወርቅና በአልማዝ አሸቈጥቁጦ ሊሰጣት ይችል ነበር። ቢፈልግ ራሱን ሳይሆን አሥር ሺህ መላእክትን መሥዋዕት ሊያደርግላት ይችል ነበር። ነገር ግን ሙሽራውና አካሉ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ፍቅሩን የገለጸው ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠት ነው።

ቤተ ክርስቲያንን ለመግዛት ክርስቶስ የከፈለው ዋጋ ብቻ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ክብርት እንደሆነች ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በማይለወጥ ፍቅር የሚወደው ለዚህ ነው። (ኤፌ. 5፥25፥29)። ለእርሷ ሕይወቱን ስለሰጠ ሲወዳት ለብቻ ነው! የፊት መጨማደድና ነውር እንዳይኖራትም ከፍተኛ እንክብካቤ ያደርግላታል (ኤፌ.5፥27)።

## መ) ከእግዚአብሔር አብና ከክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት ክብርት እንድትሆን አድርጓታል፤

ቤተ ክርስቲያን ስንል ስለ ሕንፃና ድርጅት መናገራችን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ተጠርተው የወጡና በክርስቶስ ደም ታጥበው ዳግም በመወለድ የጸደቁ ሰዎች ስብስብ ናት። በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር የመጡ ሁሉ ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አዲስ ግንኙነት ይመሠርታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ግንኙነት ሲገልጽ፥ ከላይ የገለጽነውን እርምጃ ያደረጉ ሁሉ «የእግዚአብሔር ልጆች» (ዮሐ. 2፥1:12፤ ገላ. 3፥26)፥ «የእግዚአብሔር ቤተሰብ» (1ጢሞ. 3፥15) ወዘተ እንደሚባሉ ይናገራል። ይህንን ግንኙነት የመሠረቱ ሁሉ ባለአገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰዎች ናቸው እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደሉም (ኤፌ. 2፥19)። የዓለም ፈጣሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ይህንን ዐይነት ግንኙነት ከመመሥረት ሌላ በዓለም ላይ የከበረ ነገር የለም።



ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ናት። ቤተ ክርስቲያንን ክብርት ከአደረጓት ምክንያቶች አንዱ ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋር ያላት ይህ የከበረው ግንኙነቷ ነው።

## ሠ) ባሕርይዋ ለማንነቷና ለክብርትነቷ ምስክር ነው፤

1) ቅድስት ናት ፦ «... በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ራሱን ሰጠ» (ኤፌ. 5፥26)።

ቤተ ክርስቲያን በቃሉ መታጠቧ ያላትን የቅድስና ባሕርይ ያንጸባርቃል። ቤተ ክርስቲያን ከርኩሰት የነጹና የታጠቡ ሰዎች ስብስብ ናት፤ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ ክብሯ ነው።

2) የተጎናጸፈችው ልብስ የቅድስና ባሕርይዋን ይገልጻል። የክርስቶስ ሙሽራ ፦

- ነውር የለባትም፥ (is without spot) ፥ እርኩሰት የለባትም፥ (no defilement) ፤
- የፊት መጨማደድ የላትም፥ is without wrinkle) ፥ መበስበስ (decay) የላትም።
- እድፈት የላትም (is without blemish) እንከን (defect) የላትም

## ረ) በወራሽነቷ ያገኘችው ውርስ ክብርትነቷን ያሳያል፤

የርስት ክብርና ባለጠግነት የተጎናጸፈች፥ የርስቷ መያዣ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ያገኘችና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች፥ የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ሁሉ ወራሽ ናት (ሮሜ 8፥17፤ ኤፌ. 1፥14፤ 18)። ቤተ ክርስቲያን የማይጠፋውን ሀብት ለመውረስ ተጠርተው የወጡ ሰዎች ስብስብ ናት። አንድ ቀን ሙሽራዋ በሚመጣበት ጊዜ በክርስቶስ ያገኘችውን ክብርና ውርስ ሁሉ ትቀበላለች።

## ሰ) ራስ የሆነላት የክርስቶስ ክብር ክብርት እንድትሆን ያደርጋታል፤

ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ክርስቶስ ከሁሉ በላይ የሆነ ጌታ ነው። ቤተ ክርስቲያን አካሉ ስለሆነች የዚህ ክብር ተካፋይ ናት (ኤፌ. 3፥19፤ 4፥15-16፤ 5፥29-30፤ ቈላ. 1፥15-19)።

### ሸ) ለእግዚአብሔር ያላት ቅርበትና ወደ ህልውናው ለመግባት የተሰጣት ነፃነት ክብርትነቷን ያንፀባርቃል፤

እግዚአብሔር ማንም በማይደርስበት ብርሃን ውስጥ ይኖራል። ቤተ ክርስቲያን ግን ክርስቶስ በፈጸመው የመስቀል ሥራ ምክንያት (በሥጋው፣ ማለት በመጋረጃው በኩል) ወደ እግዚአብሔር ህልውና ለመግባት ድፍረት አላት (ኤፌ. 2፥13፥18፤ 3፥12፤ ዕብ. 4፥16)። እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ መካከል አለ (ማቴ. 28፥20፤ 2ቆሮ. 6፥16፤ ኤፌ. 2፥22)።

### ቀ) በዕንቁ ተሸቈጥቁጦ የተዘጋጀላት የዘለዓለም መኖሪያ ክብርትነቷን ያሳያል፤

በአሁኑ ጊዜ ክርስቶስ ለሙሽራው የዘላለም መኖሪያ እያዘጋጀላት ነው። እርሱ ባለበት በዚህ ባዘጋጀላት ከተማ እንድትኖርም ተመልሶ መጥቶ እንደሚወስዳት የተባረከ ተስፋ ሰጥቶአታል። ስለዚህ አንድ ቀን ክርስቶስ መጥቶ ይወስዳትና ወደዚያች በወርቅና በዕንቁ ያሸቈጠቆጠች ከተማ ያስገባታል (ዮሐ. 14፥1-4፤ 1ተሰ. 4፥13-18፤ ቲቶ 2፥11-14፤ ራእ. 21፥1-27)።

ሥጋ ከለበሱ ሰዎች መካከል ከክርስቶስ ጋር ለመወዳደር የሚችል ማንም እንደሌለ ከክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ጋር ልናወዳድረው የምንችል ምንም ዐይነት ተቋም የለም። ክርስቶስ ክቡር እንደሆነ ቤተ ክርስቲያንም ክብርት ናት። ክርስቶስን አክብሮ የእርሱ አካል ያደረጋትን ቤተ ክርስቲያን መናቅ አይቻልም። ክብርት ቤተ ክርስቲያን የምንላት ለዚህ ነው።



<u>ምዕራፍ አራት</u>

## ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያንና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት

*«ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል ሁል ጊዜ «የጥቅል ስም» (collective noun) ነው። «ስም» አንድ ሰው፥ አንድ ነገር፥ ወይም አንድ ቦታ የሚጠራበት መለያ ነው። «የጥቅል ስም» ግን ከአንድ በላይ አባላት ስላሉት ስብስብ ያመለክታል። ለምሳሌ ሰራዊት፥ መንጋ፥ ቡድን፥ ቤተሰብ፥ ሕዝብ፥ ኮሚቴ ወዘተ. የሚሉት ቃላት የጥቅል ስሞች ናቸው።*

ቀደም ብለን «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚከተሉት ሁለት ዐይነት መንገዶች ጥቅም ላይ እንደዋለ ተነጋግረናል። እነዚህም፤

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - አማኞችን ሁሉ የምታጠቃልል አንዲት የክርስቶስ አካል ናት። ዓለም አቀፏ፥ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ስለምትገኝ ያለፉትን፥ የአሁኖቹንና የወደፊቶቹን ሁሉ አማኞች ታጠቃልላለች። ይሁንና ስለ እርስዋ ብናውቅም በገሐድ ባለመታየቷ «በዓይን የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን» በመባል ትታወቃለች። በዓይን የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ብቻ በመሆኗ «ቤተ ክርስቲያን» ትባላለች እንጂ «አብያተ ክርስቲያናት» ተብላ በብዙ ቊጥር አትጠራም። ነገር ግን ቀደም ሲል እንደገለጽነው «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል የጥቅል ስም በመሆኑ በዚህች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ እስከሚመጣና ቤተ ክርስቲያንን እስከሚወስድ ጊዜ ድረስ በክርስቶስ አምነው የዳኑት አማኞች ሁሉ ይጠቃለላሉ። ስለዚህ ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን፥ የምድር ኑሯቸው አብቅቶ ዛሬ በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ያሉትን፥ አሁን በሕይወት የሚገኙትንና እስከ ጌታ ዳግም ምፅአት ድረስ ገና የሚድኑትን አማኞች ሁሉ ታካትታለች።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ሁሉ መታየት የምትችለው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን» በሚል ሌላ ስም ትታወቃለች። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ሁሉ በየሰበካውና በየአጥቢያው ኅለምትገኝ «ቤተ ክርስቲያናት» ወይም «አብያተ ክርስቲያናት» በመባል በብዙ ቊጥር ትጠራለች።

ዓለም አቀፏን ቤተ ክርስቲያንና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን በማነፃፀር ስንመለከታቸው የሚከተለውን ልዩነት እናገኝባቸዋለን።

1. በአጀማመራቸው ልዩነት አለ፤

   ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - የጴንጤቆስጤ ቀን ተመሥርታለች (ሐ.ሥ. 2፥1-4፤ 11፥15)።

   ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - በማንኛውም ጊዜ መመሥረት ትችላለች። በአንድ ቦታ ብቻ ሳይሆን በየከተማውና በየአጥቢያው ስለምትመሠረት በሁሉም ቦታ በአንድ ቀን አትመሠረትም። ለዚህ ነው የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የተመሠረቱበት ጊዜ የተለያየ የሆነው። አንዳንድ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከተመሠረቱ ብዙ መቶ ዓመታት ሲያስቈጥሩ፥ ሌሎቹ ደግሞ ከተመሠረቱ ገና ጥቂት ዓመታት ብቻ አስቈጥረዋል።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የተመሠረተችው በኢየሩሳሌም ነው። ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ በይሁዳ፥ በአንጾኪያ፥ በሌሎችም ቦታዎች ሁሉ ተመሠረተች። ወደፊትም ወንጌል በሚስፋፋበት ስፍራ ሁሉ ገና ትመሠረታለች።

2. በመሥራቾቻቸው ልዩነት አላቸው

   ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - የክርስቶስ አካል የሆነችው ዓለም አቀፏና አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ቀደም ሲል እንደገለጽነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴ. 16፥18)።

   ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው በወንጌል መስፋፋት የተነሣ እግዚአብሔር በመንፈስ በመራቸው አገልጋዮች ነው (ሐ.ሥ. 14፥21-23)። የሐዋርያት ሥራን ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ በሚሲዮናዊ ጒዞው እንደ ቆሮንቶስ የመሳሰሉትን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንደመሠረተ እናያለን። (ሐ.ሥ. 18)። ዛሬም በዓለም ዙሪያ ያሉት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ እያንዳንዳቸው ታሪክና መሥራቾች አሏቸው።

3. አባል በመቀበያ መመዘኛቸው ይለያያሉ

   ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - የዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን በክርስቶስ አምኖ መዳንና ዳግም መወለድ ይጠይቃል። ዳግም ተወልደው የዳኑና ስሞቻቸው በሰማይ መዝገብ የተጻፉ ሁሉ የክርስቶስ አካል የሆነችው የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ይጨመራሉ (ሐ.ሥ. 2፥41-47፤ ዕብ.



12፥23)። ለምሳሌ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በአመነና በተጠመቀ ጊዜ ወዲያውኑ የዓለም አቀፍዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኗል። ይሁን እንጂ ገና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል አልሆነም ነበር (ሐ.ሥ. 8፥38-39)።

   ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የእግዚአብሔር ቃል በሚያስተምረው መሠረት ማንኛውም በክርስቶስ ያመነና የዳነ ክርስቲያን ወዲያው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊያድግ የሚችልበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፈልጎ አባል መሆን አለበት። የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን እንደሚገባቸው ያልተረዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያናቸው የት እንደሆነ ሲጠየቁ፥ «እኔ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ» ይላሉ። አንድ ሰው «ለአምልኮ የምትሰበሰበው የት ነው? የቤተ ክርስቲያንህን መጠሪያና አድራሻ፥ የመጋቢህንም ስም ስጠኝ» ቢላቸው ሊመልሱ የሚችሉት መልስ የለም።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የሚቻለው ያለ ፈቃድና ምርጫ አይደለም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን አንድ ሰው ራሱ ወዶ በፈቃዱ መጠየቅና መመዝገብ አለበት (ሐ.ሥ. 2፥26)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን መዳን አስፈላጊ ቢሆንም፥ ይህንን ሳያሟሉ አባል ለመሆን የሚቻልባቸው አያሌ አቋራጭ መንገዶች አሉ።

4. በአባላት መዝገብ አያያዝ ልዩነት አለ

   ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - አባላትን የምትመዘግብበት መዝገብ በምድር ላይ የላትም፤ በሰማይ ግን የዳኑት ሁሉ ስም ዝርዝር የተጻፈበት መዝገብ አለ። መዝገቡን የያዘና የራሱ የሆኑትን የሚያውቅ ጌታ ብቻ ነው (2ጢሞ. 2፥19፤ ዕብ. 12፥23)።

   ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የአባሎቿን ስም የምትመዘግብበት መዝገብ አላት።

5. በቍጥራቸው ብዛት ልዩነት አለ

   ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - አንዲት ብቻ ናት (1ቆሮ. 12፥13፤ ኤፌ. 1፥22፥23፤ 4፥4)፤ ከየስፍራው ወንጌልን ተቀብለው የታዘዙና የዳኑ ሁሉ የእርሷ አባላት ናቸው።

   ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ግን በቍጥር እጅግ ብዙ ስለሆኑ ማንም በትክክል አያውቃቸውም (ራእ. 2 እና 3)።

6. በምድራዊ ድርጅታቸው ልዩነት አላቸው

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - ምድራዊ ድርጅት የላትም። ራሷ ክርስቶስ ነው (ኤፌ. 1፥22)። ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናት፥ ኮሚቴ፥ ሰብሳቢ ወዘተ የሏትም። ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ምንም ዐይነት የተገለጠ አድራሻ፥ የስልክ ቊጥር፥ ወይም የፋክስ ቊጥር የመሳሰሉት መታወቂያዎች የሏትም።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - ዓለም አቀፏ የሌላት ምድራዊ ድርጅት ሁሉ አላት (ፊልጵ. 1፥1)። እንዲሁም ፓስተር፥ ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናት፥ የተደራጁ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፥ ስልክ፥ ፋክስና የታወቀ አድራሻም አላት። ለምሳሌ እኔ የማገለግላት ቤተ ክርስቲያን አድራሻ፤

E.C.F.C.
8526 Northern St.
Houston, TX 77071 ነው።

7. በእረኞቻቸው ቊጥር ይለያያሉ

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - አንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚመራት አንድ እረኛ ብቻ ሲሆን፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. 10፥10፤ ዕብ. 13፥20፤ 1ጴጥ. 2፥25)።

ለ) የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት - ብዙ እንደመሆናቸው፥ ከእረኞች አለቃ ከክርስቶስ ሥር ሆነው የሚያገለግሉ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰብአዊ እረኞች አሏቸው (የሐ.ሥ. 20፥17:18)።

8. በስብሰባ ጊዜዎቻቸው ልዩነት አለ

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - በምድር ላይ በየጊዜው የሚደረግ ስብሰባ የላትም። ነገር ግን አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ወደ ዓለም ሲመጣ ያንቀላፉ ክርስቲያኖችን ይዞ አሁን በሰማይ በእረፍት ላይ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን (the Church Triumphant) እንዲሁም ዛሬ በምድር ላይ በውጊያ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን (the Church Militant) ሁሉም በአንድ ላይ ክርስቶስን ለመቀበል በአየር ላይ በአንድነት ይሰበሰባሉ (1ቆሮ. 15፥24፤ 1ተሰ. 4፥13-18)።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - ሁል ጊዜ ስብሰባ አላት (ዕብ. 10፥23:25)።

9. አባላትን ከአባልነት በመሰረዝ ልዩነት አለ



ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - አንድ አባል በመሞቱ ከአባልነት አይሰረዝም። ይህች አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን በሕይወት ያሉትንና የሞቱትን ስለምታጠቃልል ሞት የአካሉ አባል መሆንን አይከለክልም።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የአንዲት የተወሰነች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኑ ይቀራል። ለምሳሌ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሲሞት የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኑ ቀርቷል (ሐ.ሥ. 8፥1-2)።

10. መከፋፈልን በተመለከተ ልዩነት አላቸው

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - በማንኛውም ምክንያት ፈጽሞ መከፋፈል አትችልም።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - ትልቅ የመከፋፈል ችግር በየጊዜው ያጋጥማታል (1ቆሮ. 3፥1-5)።

11. የጋራ አገልግሎትን በመስጠት ልዩነት አላቸው

ሀ) ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን - ምድራዊ ድርጅት ስለሌላት አማኞች የጋራ አገልግሎት የሚሰጡበት አሠራር አያስፈልጋትም።

ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - ድርጅታዊ መዋቅር ስላላት አባላት ሁሉ እንደ ጸጋ ስጦታቸው በአገልግሎት መሳተፍ ይችላሉ።

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የተቅል ስም ቢሆንም፤ የክርስቶስ አካል የሆነችው ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን የምትጠራው በነጠላ ነው። ቤተ ክርስቲያን እንላታለን እንጂ አብያተ ክርስቲያናት አንላትም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ግን ሁልጊዜ በብዙ ቊጥር መጠቀስ ይችላሉ። አንድ ስም ባለው ቤተ እምነት ሥር እንኳ ብዙ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ይኖራሉ። ስለዚህ እንደ ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን በነጠላ ቊጥር አይጠቀሱም።

## ምዕራፍ አምስት

# ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችባቸው ምሳሌዎች፤

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚገልጹ ልዩ ልዩ ምሳሌዎችና ስሞች አሉ። እነርሱም ከዚህ በታች የተገለጹት ናቸው፤

ሀ) የእግዚአብሔር መንግሥት :- ማቴ. 13፤ የሐ. 3፥1-5፤ ሮሜ 14፥17

ለ) የወይራ ዛፍ :- ሮሜ 11

ሐ) እውነተኛዋ እስራኤል :- ሮሜ 9፥1-11፥1-32፤ ገላ. 6፥16፤ 3፥16፥29

መ) የእግዚአብሔር ልጆች :- ዮሐ. 1፥12፤ ሮሜ 8፥1-19፤ 1ዮሐ. 3፥12

ሠ) የንጉሥ ካህናት :- 1ጴጥ. 2፥9፤ ራእ. 1፥6

ረ) የተቀደሰ ሕዝብ :- 1ጴጥ. 2፥9

ሰ) የወርቅ መቅረዝ :- ራእ. 1፤2 እና 3

ሸ) የዓለም ብርሃን :- ማቴ. 5

ቀ) የምድር ጨው :- ማቴ. 5

በ) ለርስቱ የተለየ ወገን :- 1ጴጥ. 2፥9

ተ) የበኵራት ማኅበር :- ዕብ. 12፥23

ቸ) የክርስቶስ መንጋ :- ዮሐ. 10፤ ሐ.ሥ. 20፥28፤ 1ጴጥ. 5፥2

ኀ) የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን :- ሮሜ 16፥16

ነ) የክርስቶስ አካል :- 1ቆሮ. 12፥27፤ ኤፌ. 1፥22-23

ኘ) የእግዚአብሔር መቅደስ :- 1ቆሮ. 3፥16-17

አ) የእግዚአብሔር ቤተሰብ :- 1ጢሞ. 3፥15

ከ) የክርስቶስ ሙሽራ :- ኤፌ. 5፥1-33

ወ) የበጉ ሚስት :- ራእ. 19፥7፤ 21፥9

ዘ) የእግዚአብሔር እርሻ :- 1ቆሮ. 3፥9

ዠ) የእግዚአብሔር ሕንፃ :- 1ቆሮ. 3፥9

የ) የእውነት ዐምድና መሠረት :- 1ጢሞ. 3፥15



ከእነዚህ መካከል ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን በሚያስተምርበትና በሚገልጽበት ጊዜ አበክሮ ይጠቀምባቸው ከነበሩት ስሞች መካከል ሦስቱን ብቻ በዝርዝር እንመለከታለን።

## የክርስቶስ አካል - (1ቆሮ. 12፥27)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችበት ልዩ ልዩ ምሳሌዎች ቢቈጠሩ ቍጥራቸው ከመቶ በላይ እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ። በዚህ ርእስ የምናተኵረው ግን ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከተጠቀመባቸው ምሳሌዎች በሦስቱ ብቻ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ አበክሮ የተጠቀመው «አካል» (Body) የሚለውን ነው። በመልእክቶቹ ሁሉ :-

- ቤተ ክርስቲያንን እንደ አካል (ኤፌ. 1፥22፥23፤ ቈላ. 1፥18፥24)፤
- ክርስቶስን እንደ ራስ (ኤፌ. 4፥15-16፤ ቈላ. 1፥18)፤
- ክርስቲያኖችን እንደ አካል ብልቶች (1ቆሮ. 12፥27)

በማድረግ አቅርቧል። ይህንንም ሲያደርግ አንድም ቦታ «አካል» (Body) የሚለውን ቃል በብዙ ቍጥር (Plural) አልተጠቀመም። በመልእክቱ ሁሉ «አካል» የሚለውን ቃል የተጠቀመው በነጠላ ቍጥር (Singular) ነው። የዚህ ምክንያት የክርስቶስ አካል አንድ ብቻ እንጂ ብዙ መሆን ስለማይችል ነው። ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ስለዚህ ጕዳይ ሲጽፍ፤

«በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ» ይላል (ኤፌ. 4፥4)።

አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንና በሚድንበት ጊዜ፥ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው የክርስቶስ አካል ክፍል (ብልት) እንዲሆን ያጠምቀዋል (1ቆሮ. 12፥13)። አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉት ሁሉ የክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያንም ከልዩ ልዩ የአካል ክፍሎች (ብልቶች/አማኞች) የተገነባች ናት (1ቆሮ. 12፥27)። የአካል ብልቶች ልዩ ልዩና ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን አካል አንድ ነው፥ ያለውም ራስ አንድ ብቻ ነው።

«አካልም አንድ እንደሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው» (1ቆሮ. 12፥12)።

አንድ አካል ሁለት ራስ ቢኖረው በጣም አስፈሪ «ጭራቅ» (Monster) ይሆናል እንጂ ሰው መሆን አይችልም። ቤተ ክርስቲያንም

ከክርስቶስ ሌላ ራስ የላትም፤ ቢኖራት የክርስቶስ አካል ልትሆን አትችልም። እንደዚሁ ደግሞ አንድ ራስ አብረውት የተያያዙ ሁለት አካላት የሉትም፤ ቢኖሩት ይህ የተለመደ የሰው አካል አይሆንም። ቀደም ሲል እንዳልነው አስፈሪ ጭራቅ የሆነ ፍጡር ነው። ቤተ ክርስቲያንን ሁለት አካል ልናደርጋት ወይም ሁለት ራስ ልንሰጣት ብንሞክር በጣም አስፈሪና አስደንጋጭ እናደርጋታለን።

ከአካል ብልቶች መካከል ደግሞ አንድ ብልት በራሱ ብቻውን አካል መሆን አይችልም። አካል ማለት አፍንጫ ቢሆን ማየት፥ መስማትና፥ መራመድ ... የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም (1ቆሮ. 12፥17)። የአካል ብልቶች ልዩ ልዩ ናቸው፤ ነገር ግን በአንዱ አካል ውስጥ የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በመተባበር ይፈጽማሉ። አንዳቸው ያለ ሌላው ፍጹም መሆን አይችሉም (1ቆሮ. 12፥16)።

አንድ ሙሉ ሰው (Adult) 200 የሚሆኑ የተለያዩና የተጋጠሙ አጥንቶች አሉት። በአጥንት ውስጥ ደግሞ የደም ሕዋሳት (Cells) የሚሠሩበት አስደናቂ «ፋብሪካ» አለ። እንደዚሁም አንድ ሙሉ ሰው ሰውነቱን ለማንቀሳቀስ የሚረዱት 600 ጡንቻዎች (Muscles) አሉት። በተጨማሪም በርካታ ልዩ ልዩ ብልቶችና እንደ ስልክ መስመሮች የተዘረጉና የሚሠሩ ሽቦዎች፥ መልእክቶችን በአእምሮና በብልቶች መካከል ያመላልሳሉ። የሰው አካል ሰው ሠራሽ ከሆነው ኮምፒዩተር ይልቅ እጅግ አስደናቂ ሆኖ የተበጀ ነው። ይህንን አስደናቂ አካል ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ራሷ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ያላትን ግንኙነት ለመጥቀስና በምድር የምትኖርበትንም የሥራ ዓላማ ለማሳየት በምሳሌነት የተጠቀመው።

ሐዋርያው ጳውሎስ «አካል» የሚለውን ቃል ለማትታየዋና ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ለሁለቱም ተጠቅሞበታል።

ሀ) ለማትታየዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (ኤፌ. 1፥22-23)

ለ) ለምትታየዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (1ቆሮ. 12፥27)። ነገር ግን ለምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን ስንጠቀምበት እያንዳንዱ አጥቢያ የአካሉ አንድ ክፍል እንጂ በራሱ አንድ ሙሉ አካል እንዳልሆነ ማስተዋል ይገባናል። በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያሉት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በሰማይ በድል አረፍት ላይ ያሉትን ጨምሮ የተሟላውን አንዱን የክርስቶስን አካል ይሠራሉ።

ቤተ ክርስቲያንን በአካል መልክ የሚያቀርበው ምሳሌ በአማኝና በክርስቶስ እንደዚሁም በአማኞች መካከል (እርስ በርስ) ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት በትክክል የሚገልጽ ነው።



ስለዚህ «አካል» የሚለው ቃል የሚከተሉትን እውነቶች ሁሉ ያሳየናል፤

ሀ) ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ ያላት አንድ ራስ ብቻ ነው (ቈላ. 1፥18)።

1. በቤተ ክርስቲያን ላይ ሥልጣን ያለው ክርስቶስ ብቻ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የምትገዛው ለክርስቶስ ብቻ ነው (ኤፌ. 5፥24)። ሁሉ ነገር በርሱ ለእርሱ ተፈጥሮአል (ቈላ. 1፥16)፤ ያለ ክርስቶስ ሁሉ ነገር፥ ቤተ ክርስቲያንም ጭምር፥ ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእርሱን ድምፅ መስማትና ለእርሱ መገዛት አለባት።

2. ቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ የምታገኘውና የምትኖረው በእርሱ ነው (ኤፌ. 4፥16)።

ለ) ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ ብዙ ብልቶች አሏት (1ቆሮ. 12፥20)።

1. እያንዳንዱ ብልት ከሌላው ብልት ጋር የተያያዘ ነው (1ቆሮ. 12፥13)።

2. በአካል ውስጥ ለብቻዬ የሚባል ነገር የለም። ለአንዱ ብልት ሌላው ብልት ያስፈልገዋል (1ቆሮ. 12፥21-26)።

3. እያንዳንዱ ብልት ለአካሉ አስፈላጊ ነው (1ቆሮ. 12፥27)።

ሐ) በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች አንድነትን መጠበቅ አለባቸው (ሮሜ 15፥5-6)።

መ) አካል ዓለም አቀፋዊ ነው።

የዚህ አካል ክፍል ለመሆን የሚጠይቀው «ኑ» የሚለውን የክርስቶስን ጥሪ ተቀብሎ መምጣት ነው። ስለዚህ ከመላው ዓለም፥ ከሕዝብ፥ ከነገድ፥ ከቋንቋ ሁሉ ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ የአካሉ ክፍል ይሆናሉ። ክርስቶስ ወደዚህች ዓለም ከመምጣቱና ከመሞቱ ቀደም ብሎ የነበሩት ልዩ ልዩ የመለያያ ግድግዳዎች በሙሉ ፈርሰዋል (ቈላ. 3፥11)።

ሠ) ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ክርስቶስ በምድር ላይ ሥራውን የሚሠራባት የአገልግሎቱ ቅጥያ ናት።

ሐዋርያው ጳውሎስ «አካል» የሚለውን ቃል ለምን መጠቀም እንደ ጀመረ ሰዎች የተለያየ አሳብ ይሰጣሉ። ከጥንት አባቶች አንዱ የሆነው ቅዱስ አውግስቲን ግን፥ ሐዋርያት ሥራ 9፥4 ላይ እንደምናነበው፥ ክርስቶስ ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ ላይ ተገናኝቶት «ሳውል ሳውል ስለ ምን ታሳድደኛለህ?» ብሎ ስለጠየቀው እንደሆነ ይናገራል። ጥያቄው

«ለምን ታሳድዳቸዋለህ?» መሆን ሲገባው «ለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ነበር። ቤተ ክርስቲያን አካሉ በመሆንዋ እርሷን ማሳደድ ክርስቶስን ማሳደድ ነው። እንደ አውግስቲን አባባል ጳውሎስ «አካል»ን ለቤተ ክርስቲያን ምሳሌነት መጠቀም የቻለው ከዚህ ልምምዱ የተነሣ ነው።

ጌታ ከሞት ተነሥቶና ዐርጐ ዛሬ በአባቱ ቀኝ ቢቀመጥም፥ በምድር ላይ የጀመረውን ሥራ ግን አላቋረጠም። አካሉ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ዛሬም ሥራውን ይሠራል። ይህንን እውነት የአካሉ ክፍል የሆኑ አማኞች (ብልቶች) ሁሉ ሊያውቁት የተገባና አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የሚከተሉትን ነገሮች ማስተዋል ይገባል።

## 1) እያንዳንዱ ብልት ሕያው መሆን አለበት

የሰው አካል ሕያው የሆኑ ሕዋሳት (Cells) ሕያው ስብስብ (Living Organism) ነው። በአንድ ሰውና በየሱቁ ለማስታወቂያ በሚቆመው የሰው ቅርጽ ምስል ያለው ልዩነት ሕያው የመሆንና ያለመሆን ጉዳይ ነው። ምስሉ፤ እጅ፥ እግር፥ ዓይን፥ ወዘተ ቢኖሩትም ሕያው ስላይደለ ምንም ስሜት የለውም። እያንዳንዳችን ከምስሉ የምንለየው ሕያው ሰው በመሆናችን ነው። «... ልጁ ያለው ሕይወት አለው። ልጁ የሌለው ሕይወት የለውም» (1ዮሐ. 5፥12)። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ በመንፈሳዊ አነጋገር ሰዎችን «ሕያው» ወይም «ሙታን» ብለን ለሁለት መክፈል እንችላለን (ኤፌ. 2፥1-5፤ 1ዮሐ. 5፥12)።

ስለዚህ ሁላችንም የክርስቶስን ሥራ ለመሥራት፥ አባል ሆነን በምንገኝበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቀረው የአካሉ ክፍል ጋር አብረን የምንንቀሳቀስ ሕያው ብልት መሆን አለብን። አንድ ሰባኪ እንዳለው «አባል» በመሆንና «የአካል ብልት» በመሆን መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ለምሳሌ አንድ እጁ የተቈረጠበት ሰው ለጐደለው አካሉ አርቲፊሻል እጅ መቀጠል ይችላል። ያ አርቲፊሻል እጅ ለዚያ ሰው እንደ አካሉ ክፍል ሆኖ ማገልገል ይችላል። የዚያ ሰው ብልቶች አባል ነው። አብሮ ይገኛል፤ ነገር ግን የአካል ክፍል አይደለም። እኛም በምንገኝበት አጥቢያ ሕያው ካልሆንን ከአርቲፊሻሉ አካል ያልተለየ ‹አብሮ ያለ ተለጣፊ› ብቻ እንሆናለን። ከዚህ ለመዳን ነው ሰውነት ጤናማ ሆኖ እንዲኖርና እንዲሠራ ልዩ ልዩ እንክብካቤና ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠይቀው። መንፈሳዊ ጤንነታችንን ለመጠበቅ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ሁሉ መፈጸምና መከታተል አለብን። አንድ ሰው የአካሉን ጤንነት ባይጠብቅ ተጠያቂው እሱ ነው። መንፈሳዊ ጤንነትንም መጠበቅ የእያንዳንዱ አማኝ ሃላፊነት ነው።



## 2) የእውነት ዓምድና መሠረት - (1ጢሞ. 3፥15)

ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ቤተ ክርስቲያንን የእውነት ዓምድና መሠረት ሲል ጠርቷታል (1ጢሞ. 3፥15)። ዓምድ (ምሰሶ) አንድ ሕንፃ እንዲቆም የሚደግፍና የሚሸከም ቋሚ ነው። ሕንፃውን የተሸከመውና የደገፈው ምሰሶ (ዓምድ) ቢወድቅ ሕንፃውም ይወድቃል። መሳፍንት 16፥19-30 ላይ በምናነበው የሳምሶን ታሪክ የዚህን እውነትነት እናያለን። ሳምሶን ምሰሶውን ገፍቶ ሲጥል ሕንጻው ወደቀና ራሱን ጨምሮ በሕንጻው ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ጠፉ።

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ከምትኖርበት ዓላማ አንዱ እውነትን ለመደገፍና ለመጠበቅ ነው። ሕንፃን የሚደግፉ ምሰሶዎች ሊፈርሱ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን በምድር ላይ ስትመሠረት «የገሀነም ደጆች እንኳን አይችሏትም» (ማቴ. 16፥18) የሚል ተስፋ በመሥራቿ ስለተሰጣት፤ የእውነት ዓምድና መሠረት ከመሆን የሚነቀንቃት ምንም ነገር የለም።

ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድ መሆን የምትችለው እንዴት ነው? የሚከተሉትን መንገዶች እንመልከት፤

ሀ) በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር እውነት ለሰዎች የተገለጸው በእርሷ አማካይነት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጸ ‹እውነት› ነው (ዮሐ. 14፥6)። ከዚህም ሌላ በ66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የተጻፉት ሁሉ የእግዚአብሔር እውነት ይባላሉ። ከእነዚህ መካከል በአዲስ ኪዳን የሚገኙት 27 መጻሕፍት የተጻፉት በቤተ ክርስቲያን ነው። ወንጌሎች፥ የሐዋርያት ሥራ፥ መልእክቶችና የራእይ መጻሕፍት የተጻፉት የክርስቶስ አካል (የቤተ ክርስቲያን) ክፍል በሆኑ ቅዱሳን ሰዎች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉት የእግዚአብሔር እውነት ነው (2ጴጥ. 1፥21)። እግዚአብሔር፥ በአዲስ ኪዳን ቃሉን ለሰዎች ለመግለጽና ለመስጠት መሣሪያ አድርጐ ቤተ ክርስቲያንን በመጠቀሙ የእውነት ዓምድና መሠረት ሆናለች።

ለ) የወንጌሉን ምሥራች ታውጃለች፤ ቃሉን ታስተምራለች።

በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ቃሉን የጻፉትና መሠረት የጣሉት ሐዋርያት ከሞቱ በኋላ የእግዚአብሔር እውነት ሁሉ ተገልጾ አብቅቷል። ዛሬ ከዚያ ቀጥሎ 67ኛውን ወይም ሌላ አዲስ መጽሐፍ በተገለጸው ቃል ላይ ማንም ጨምሮ መጻፍ አይችልም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ ያለባት ሃላፊነት የሚከተሉት ናቸው፤

(1) የወንጌሉን የምሥራች ላልሰሙት ሁሉ ታሰማለች። ሰዎች በክርስቶስ የተፈጸመውን የመስቀል ሥራ አምነውና ተቀብለው ወደ ደኅንነት እንዲመጡ ታደርጋለች።

«እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፥17)።

ሰዎች የምሥራቹን ቃል ካልሰሙ መዳን አይችሉም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በመሥራቿ የተሰጣትን ታላቁን ተልዕኮ (ማቴ. 28፥18-20) በመፈጸም የእውነት ዓምድና መሠረትነቷን በተግባር ታሳያለች። ቤተ ክርስቲያን ባትኖር ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ አይችሉም።

(2) በመጀመሪያይቱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት አማኞች በአንድ ላይ በየጊዜው ይሰበሰቡ ከነበሩበት ዓላማ አንዱ ቃሉን ለመማር ነበር (ሐ.ሥ. 2፥42)። ቤተ ክርስቲያን ላልዳኑ ወንጌልን ማወጅ ብቻ ሳይሆን፥ አማኞችም የእግዚአብሔርን ቃል በየጊዜው እንዲመገቡና እንዲያድጉ ትረዳለች። እግዚአብሔር የእረኝነትና የማስተማር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ለዚህ ዓላማ ነው (ኤፌ. 4፥11)።

ሐ) የእግዚአብሔር እውነት እንዳይበረዝ ትጠብቃለች።

እውነት ብዙ ጠላቶች አሏት። አንዳንዶች እንደ ሳውል በአለማወቅ ይቃወሟታል (ገላ.1፥23፤ 1ጢሞ. 1፥13)። እንዲሁም የጽድቅ ጠላት ዲያብሎስ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን እንደሚለውጥ፥ እውነት የሚያስተምሩ መስለው ሐሰት የሚያስተምሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ከቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ ይነሣሉ። (ማቴ. 7፥15፤ ሐ.ሥ. 20፥28-30፤ 2ቆሮ. 11፥13-15፤ 1ጢሞ. 4፥1-2)። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለእውነት በመቆም በምእመኑ መካከል ሾልከው የገቡትን ሐሰተኛ አስተማሪዎች ታጋልጣለች፤ የሳቱትን ትመልሳለች።

እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የእውነት ዓምድና መሠረትነቷ የሚገለጸው ከላይ በጠቀስናቸው መንገዶች ነው። እውነትን ሳትደግፍና ሳትጠብቅ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ሕንፃ፥ ያማረ ምስባክ (ፑልፒት)፥ ብዙ ሰባኪያን ቢኖሯት እንኳን፤ እውነተኛ፥ የእውነት ዓምድና መሠረት መሆን አትችልም። እውነተኛውን ወንጌል መስበክ ካቆመች እውነተኛነቷ ይቀራል። ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ቆማ የቃሉ እውነት እንዳይበረዝ መጠበቅ ያለባት።



## 3. የክርስቶስ ሙሽራ - (ኤፌ. 5፥22-23)

ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰለበት መንገድ ሌላው እንደ ክርስቶስ ሙሽራ ነው። በባልና በሚስት መካከል ያለውን ግንኙነት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ላለው ግንኙነት ምሳሌ አድርጐታል።

ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት፥ በእርሱ የወንጌል አገልግሎት የዳኑትን ሁሉ ለአንድ ወንድ ብቻ እንደታጨችና የሠርግ ቀኗ ደርሶ ወደ ባሏ ቤት ለመሄድ ራሷን በንጽሕና በምትጠብቅ ሴት ይመስላቸዋል።

«በእግዚአብሔር ቅንአት እቀናላችኋለሁና፤ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና» (2ቆሮ. 11፥2)።

እንደዚሁም ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክት፥ ባሎች ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ፤ ሚስቶችም ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ለባሎቻቸው እንዲገዙ ስለ ትዳር ግንኙነት መሠረታዊ አሳብ በዝርዝር አስተምሮአል። (ኤፌ. 5፥22-23) በተለይ ደግሞ ቍጥር 32 ላይ የባልና የሚስት አንድነት ትልቅ ምሥጢር እንደሆነ በመግለጽ «... እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ» ይላል።

አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን «የክርስቶስ ሙሽራ ናት» የሚለው አሳብ ይከብዳቸዋል። በመሠረታዊ አሳቡም ላይ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ወገኖች አሉ። ቤተ ክርስቲያን ሙሽራ ናት ስንል ቃሉን የምንጠቀመው በጥሬ ትርጕሙ አይደለም። «ሙሽራ»፥ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነትና ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር የሚገልጽ እንጂ፥ በወንድና በሴት መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ምንም ተመሳሳይነት የለውም።

በእግዚአብሔር ሰዎች፥ በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት በባልና ሚስት ግንኙነት ምሳሌነት መመልከት በብሉይ ኪዳንም የነበረ አሳብ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን በሚስት መልክ ይመለከት እንደነበር ሙሽራውም እንደነበረች እናነባለን (ኢሳ. 54፥5-6፤ ኤር. 3፥14)። እስራኤል ግን ለእግዚአብሔር እንደ ታማኝ ሚስት መሆን እንዳልቻለችና ኃጢአት እንዳደረገች እናያለን (ኤር. 2፥13)። ይህም የእስራኤል ኃጢአት ሁለት ዐይነት ነበር :-

ሀ) እግዚአብሔርን መተው፤

ለ) ሌሎች አማልክቶችን (ጣዖታት) ማምለክ። ይህም ቢሆን እግዚአብሔር ምሕረተኛ ስለሆነ ንስሐ እንድትገባና ወደ እርሱ

እንድትመለስ ለእስራኤል ብዙ ጊዜና ዕድል ሰጣት (ኤር. 3፥12-14)፤ ይሁንና የእግዚአብሔርን ምሕረት ተቀብላ ወደ እርሱ መመለስ አልፈለገችም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የመረጠው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው።

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን አዳም እንዲያንቀላፋ አድርጐ ከጐኑ አጥንት በመውሰድ ሔዋንን እንዳቀረበለት፥ ልጁንም በመስቀል ላይ እንዲሞት (እንዲያንቀላፋ) አድርጐ ከጐኑ፥ ከእጆቹና ከእግሮቹ የፈሰሰውን ደም በመውሰድ ቤተ ክርስቲያንን ለእርሱ የተገባች ቆንጆ ሙሽራ አድርጐ አቀረበለት። መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መምጣታቸውን ሲያውቅ «ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው» ያለው ቤተ ክርስቲያን ጌታ ዋጋ ከፍሎ ንብረቱ ያደረጋት በመሆኗ ነው (ዮሐ.3፥29)።

ቤተ ክርስቲያን ሙሽራ ናት ስንል የሚከተሉት ነገሮች ወደ አሳባችን ይመጣሉ፤

ሀ) ባልና ሚስት አንድ እንደሆኑ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን አንድ ናቸው።

በዚህ አንድነቷ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መከራ ተካፋይ ናት (2ጢሞ. 2፥12)፤ እንደዚሁ የክብሩም ደግሞ ተካፋይ ናት (ሮሜ 8፥17)።

ለ) ሚስቶች ለባሎቻቸው እንደሚገዙ (እንደሚታዘዙ) ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ትታዘዛለች (ኤፌ. 5፥22-23)።

ሐ) ሙሽራ ለባሏ ታማኝ እንደሆነች ቤተ ክርስቲያንም ለክርስቶስ ታማኝ ናት (2ቆሮ. 11፥2)።

ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ብቻ የተሰጠች ናት። ከእርሱ ሌላ የምትወደው ነገር ሁሉ መንፈሳዊ ምንዝርና ነው (ያዕ. 4፥4)።

መ) ሚስት ስትታጭ ጥሎሽ እንደሚከፈል ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ እርሷን ለማግኘት ዋጋ ከፍሎአል።

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የገዛት በከበረው ደሙ ነው (1ጴጥ. 1፥18፥19)።

ሠ) ከመተጫጨት በኋላ ሠርግ እንዳለ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም የሠርግ ቀን ተቀጥሮላታል (ራእ. 19፥7-9)።

በራእይ 19 ላይ የተጻፈው ቃል የበጉና የቤተ ክርስቲያን የሠርግ ቀን እንዳለ መግለጽ ብቻ ሳይሆን፤ ሀ) የሠርጉ ቀን በጣም መቃረቡን፤ ለ) ሙሽራይቱም ዝግጅት እያደረገች መሆኗን ይነግረናል።



ረ) በሠርግ ቀን ሙሽራ ወደ ሙሽሪት መኖሪያ መጥቶ ወደ እርሱ ቤት እንደሚወስዳት ጌታ ኢየሱስም ወደ ምድር መጥቶ ቤተ ክርስቲያንን ይወስዳታል (ዮሐ. 14፥1-4)።

የተባረከው የቤተ ክርስቲያን ተስፋ የምንለው ይህችን ቀን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚዘጋው ቤተ ክርስቲያን ያችን ቀን በናፍቆት ስትጠባበቅና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆና ሙሽራዋን «ና» በማለት በምትጣራበት ምዕራፍ ነው።

«መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል። የተጠማም ይምጣ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ» (ራእ. 22፥17)

«አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!» (ራእ. 22፥20)

# ምዕራፍ ስድስት

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና አባሎችዋ

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማንነት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን :- ዳግም በመወለድና ደኅንነትን በመቀበል የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ፥ በአንድ አጥቢያ በመገኘታቸው የክርስቶስን ትእዛዝ ለመፈጸም፥ ለአምልኮ፥ ለኅብረት፥ ለትምህርትና የጌታን እራት አብሮ ለመካፈል፥ እግዚአብሔር ለአጥቢያው በሾማቸው መሪዎች በመመራት የእግዚአብሔርን ሥራ አብሮ ለመሥራት፥ በፈቃዳቸው ቃል ኪዳን ያደረጉና በየጊዜው አብረው የሚገናኙ አማኞች ስብስብ ማለት ነው።

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ለአካባቢው የምትታየው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ስለሆነ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ትንሽ ምስል ናት።

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ በምድር ላይ የተመሠረተችው በጴንጤቆስጤ ቀን እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ጽርሐ ጽዮን በሚባለው ስፍራ በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ 120 የሚሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች በአንድ ላይ ሆነው በጸሎት በሚተጉበት ጊዜ ይጠብቁት የነበረው የአብ ተስፋ በመፈጸሙ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ተመሠረተች (ሐ.ሥ. 2)። የኢየሩሳሌም ከተማ፥ ቤተ ክርስቲያን በምድር የተመሠረተችባት የመጀመሪያዋ ቦታ ብቻ ሳትሆን፥ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም የመጀመሪያዋ ቦታ ናት። የተመሠረተችውም ቀደም ሲል በጠቀስናቸው 120 በሚሆኑት የክርስቶስ ተከታዮችና የጴንጤቆስጤ ቀን የጴጥሮስን መልእክት ሰምተው በመዳን ተጠምቀው ወደ እነርሱ በተጨመሩት 3000 አማኞች ነው። የኢየሩሳሌም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ዕለት 3120 አባሎች እንደነበሯት የሐዋርያት ሥራን በማንበብ መረዳት እንችላለን (ሐ.ሥ. 2)።

ወንጌል በየስፍራው ለመሠራጨቱና አዳዲስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ለመከፈታቸው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መነሻ ናት።



ምክንያቱም ወዲያው በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ስለተነሣ ከሐዋርያት በቀር የቀሩት አማኞች ወደ ይሁዳና ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። እነዚህ አማኞች በሄዱበት ሁሉ ወንጌልን እየሰበኩ ስለዞሩ፥ ሰዎች በክርስቶስ እያመኑ ተጠመቁ (ሐ.ሥ. 8፥1-8)። በዚህ ዐይነት መንገድ ወንጌል ተስፋፋ፤ አዳዲስ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ተመሠረቱ። አንዳንዶች፥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን «እናት ቤተ ክርስቲያን» እንደሆነች የሚናገሩት ለዚህ ነው። ሌሎቹን ሁሉ የምታስተዳድር እርሷ ነበረች ለማለት ሳይሆን፥ ወንጌል የተስፋፋውና የተሠራጨው ከእርሷ ወጥቶ መሆኑን ለመግለጽ ብቻ ነው።

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች፥ ከቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጀምሮ ባሉት አርባ ዓመታት ውስጥ በጊዜው ይታወቅ የነበረውን ዓለም ሁሉ (መካከለኛው ምሥራቅ፥ ኤስያ፥ የሜድትራንያን አካባቢ አገሮች አፍሪካና አውሮፓ) በወንጌል አጥለቅልቀውታል። በዚህም ምክንያት በየቦታው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ። ለምሳሌ፥ አንጾኪያ (ሐ.ሥ. 13፥1)፥ ኤፌሶን (ሐ.ሥ. 20፥28)፥ ቆሮንቶስ (1ቆሮ. 1፥2)፥ ሮም (ሮሜ 1፥7) ወዘተ።

በሐዋርያት ሥራ፥ ስለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት የምናገኘው ሞዴል፥ ወንጌልን ማሠራጨትና መስፋፋት ብቻ ነው። ጥሪ ያላቸው ሰዎች በግላቸው ወይም በቤተ ክርስቲያን ተልከው ምንም አማኝ ወደሌለበት አካባቢ ይሄዱና ወንጌልን ይሰብካሉ፤ ሰዎች ቃሉን ተቀብለው በሚያምኑና በሚጠመቁበት ጊዜ በዚያ ስፍራ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይመሠረታል።

የአዲስ ኪዳን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አጀማመር ሞዴልና የእግዚአብሔር ቃል፥ በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን የአንዳንዶቹን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አመሠራረት አይደግፍም። ዛሬ ከሰዎች ግላዊ ምክንያቶች የተነሣ ብዙ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እንደ አሜባ ከሁለትም ሆነ ከሦስት ቦታ ይሰነጠቃሉ።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አመሠራረት በአራቱ የሒሳብ መደብ ምልክቶች መግለጽ ብንፈልግ፥ መጠቀም የምንችለው ምልክት የማባዛት (X) ብቻ እንጂ ፈጽሞ የማካፈል (÷) አይደለም። አንድን አጥቢያ ለምንም ምክንያት መክፈል የእግዚአብሔርን መንግሥት አያሰፋም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በየስፍራው ወንጌልን በሚያሠራጭና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን በሚመሠርትበት ዘመን ስሕተት እንዳይሠራ ይከተል የነበረውን መመሪያ እንዲህ የሚነግረን፤

«እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ» (ሮሜ 15፥20)።

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት

የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ሁሉ የተጻፉት ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ እንደሆነች ከምናይባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ከክርስቶስ የተላኩት ሰባት ልዩ ልዩ መልእክቶች የተጻፉት ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ነው (ምዕራፍ 2 እና 3)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የቃሉ ተቀባይ ለመሆን በእግዚአብሔር ተመርጣለች። ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር እርሱ የሚለውን ለመስማት እንዲችሉ ሕዝቦቹ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰበሰቡ እንደሚፈልግ ነው።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ካሉት ተቋሞች (Institutions) ሁሉ በጣም አስፈላጊዋ ናት። ምክንያቱም እርሷ በምድር ላይ እግዚአብሔርንና በጎ ሥራውን የምትወክልና የምትገልጽ ብቸኛ የእግዚአብሔር ተወካይ ናት። ከእግዚአብሔር የሚመጣውን መንፈሳዊ ሀብትና በረከት ሁሉ በምድር ለሚኖሩ ለማካፈል ውክልናና ሥልጣን አላት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም» (ማቴ. 5፥13-14) ያለው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። በዘመናት ሁሉ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልትሰወር እንደማትችል በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ ለዓለም ብርሃን አሳይታለች። እንደ ጨውም ሆና ክፋትንና መበላሸትን ተዋግታለች። ለሰው ልጆች መልካምን ለማበርከት በመሳተፍ የቀደማት ማንም የለም፤ ለዓለምም ሥልጣኔ ያበረከተችው አስተዋጽኦ ወደር አይገኝለትም።

አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበትና በሚድንበት ጊዜ ወዲያው የክርስቶስ አካል ክፍል (ብልት) ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሰው አዲስ አድርጎ ይለውጠውና ወደ ክርስቶስ አካል አባልነት ያጠምቀዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ፥ «አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና» ይላል (1ቆሮ። 12፥13)።



## የአንዲቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን በመጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መካከል ልዩነት አለን?

1ቆሮንቶስ 12፥13ን በመመርኮዝ፥ አንድ የጠፋ ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው እንደሚለውጠውና የክርስቶስ አካል ክፍል እንዲሆን እንደሚያጠምቀው ቀደም ሲል ተመልክተናል። ነገር ግን ይህ ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር አንድ ዐይነት ልምምድ አይደለም።

አዲስ ኪዳንን ስናነብ «ጥምቀት » የሚለው ቃል ሰባት ጊዜ ያህል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተዛምዶ እናገኛለን።

1ኛ) ማቴዎስ 3፥11 - መጥምቁ ዮሐንስ «እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል» ብሏል።

2ኛ) ማርቆስ 1፥8 - በዚህም ከላይ የጠቀስነው የመጥምቁ ዮሐንስ ቃል ሰፍሯል።

3ኛ) ዮሐንስ 1፥33 - መጥምቁ ዮሐንስ፥ «እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ ፦ መንፈስ ሲወርድበትና ሲያርፍበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ» ይላል።

4ኛ) የሐዋርያት ሥራ 1፥5 - ከትንሣኤ በኋላ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» ብሏቸዋል።

5ኛ) የሐዋርያት ሥራ 11፥15-16 - ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ስለሆነው ሁኔታ ሲያስረዳ፥ «ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው። ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ»።

6ኛ) ሉቃስ 3፥16 - በዚህም ክፍል መጥምቁ ዮሐንስ፥ እርሱ ለንስሐ በውኃ እንደሚያጠምቅ፥ ጌታ ግን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ የተናገረው ቃል ተጠቅሷል።

7ኛ) 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 - ጳውሎስ፥ «አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና» ይላል።

ከ1-6 ባሉት ዝርዝሮች የተጻፈው ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። በ7ኛው ተራ ከ1ቆሮ. 12፥13 የተጠቀሰው ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሳይሆን፥ በደኅንነት ጊዜ ሁሉንም የአንዱ የክርስቶስ አካል ስለሚያደርገው ጥምቀት ነው። በአዲስ ኪዳን «ጥምቀት» የሚለው ቃል የሰፈረበትን ለመጠቆም ሰባት ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል ተባለ እንጂ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተጻፈው በእነዚህ ክፍሎች ብቻ አይደለም። በተለይ በስድስቱ ቦታ የተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ በሌሎች መንገዶችም ተገልጿል። ለምሳሌ፥ ሐዋርያት ሥራ 2 እና 10 ላይ «በመንፈስ ተሞሉ» ወይም «መንፈስ ሞላባቸው» በሚል ሀረግ የተገለጸው ያው አንዱ ልምምድ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 12፥13 የጠቀሰው፥ በደኅንነት ጊዜ የአካሉ ብልት ለመሆን ስላስቻለ ልምምድ እንጂ፥ ከደኅንነት በኋላ ስለሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ አይደለም።

እነዚህ ሁለት ዐይነት ጥምቀቶች በብዙ ረገድ ልዩነት አላቸው። ለምሳሌ አጥማቂውን ብንመለከት፥ የክርስቶስ አካል ክፍል ወደ መሆን የሚያጠምቀው መንፈስ ቅዱስ ነው። በቀሩት ስድስት ቦታዎች በመንፈስ ያጠምቃል የተባለው ግን ኢየሱስ ነው። የጥምቀቱ ዓላማ ደግሞ፥ በሁለቱ መሐል ያለውን ልዩነት የበለጠ አጉልቶ ያሳያል። የጠፋ ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው የሚያጠምቀው ደኅንነትን እንዲቀበል፥ አዲስ ፍጥረት እንዲሆንና ተለውጦ በክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) አንድ ብልት እንዲሆን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅበት ዓላማ ግን ኃይልን እንድንቀበልና እንድናገለግለው ነው። ስለዚህ በርእሱ ለተነሣው ጥያቄ አጭሩ መልስ፥ ሁለቱ አንድ ዐይነት ልምምድ አይደሉም ነው። ጥምቀት በሚለው ቃል ስለተገለጹት ስለ እነዚህ ሁለት አሳቦች ልዩነትና አንዳንድ ሰዎች በጥቅሶቹ ላይ ስላላቸው አመለካከት በቂ መልስ መስጠት ይቻላል። ይህን ብናደርግ ግን ርእስ ለቅቆ መሄድ ይሆንብናል።

ከዚህ በታች ያለው ሥዕላዊ መግለጫ የሚያሳየው አንድ የጠፋ ሰው አምኖ ወደ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው በማጥመቅ እንዴት የክርስቶስ አካል እንደሚያደርገው ነው።






እርስ በርስና ከክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይመሠረታል

የክርስቶስ አካል ክፍል (የዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን አባል) የሆነ ሰው፥ በዳነበት ወይም በሚኖርበት ከተማ በሚገኝ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወዲያው አባል መሆን ይኖርበታል። የዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆን ማንም መኖር አይችልም። ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገትና እንክብካቤ ከሌሎች አማኞች ጋር በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። የአንድ አማኝ እምነቱ (ሃይማኖቱ) ወደ ቤተ ክርስቲያን ካልወሰደው፥ ወደ መንግሥተ ሰማይም አይወስደውም።

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ በተመሠረተችበት ቀን (የጴንጤቆስጤ ዕለት) ጴጥሮስ ተነሥቶ በሰበከው ስብከት ካዳመጡት ሰዎች መካከል ሦስት ሺህ የሚያህሉት ቃሉን በደስታ ተቀብለው አመኑና ተጠመቁ። አምነው በተጠመቁ ጊዜ የዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን አባል ብቻ ሆነው አልቁዩም፤ ወዲያው በኢየሩሳሌም በነበረችው አንጋፋ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ወደ ኅብረቱ ተጨምረዋል (ሐ.ሥ. 2፥41-42)። በተለይ ቍጥር 42ን ስንመለከት፥ በመጀመሪያይቱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት አባላት በየጊዜው በአንድነት ይሰበሰቡ የነበሩት ለሚከተሉት አራት ዐላማዎች እንደነበር እንረዳለን።

ሀ) ለትምህርት - ሐዋርያት የሚያስተምሩትን ትምህርት ለመማር ይሰበሰቡ ነበር። ያለ ቃሉ መኖርም ሆነ ማደግ ስለማይቻል፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ታስፈልጋለች።

ለ) ለኅብረት - አማኞች ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት ከሌሎች አማኞች ጋር በኅብረት እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው። አማኝ ከኅብረት ውጭ ፍጹም መሆን አይችልም። ማንም ከሌላው ጋር ሳይያያዝ እንደ ደሴት ለብቻው መኖር አይችልም።

ሐ) እንጀራን አብሮ ለመቍረስ - መታሰቢያው እንዲሆን ጌታ የሰጠውን ቅዱስ ቍርባን አብሮ ለመካፈል ይሰበሰቡ ነበር።

መ) ለጸሎት - አማኝ የግል ጸሎት ቢያደርግም በኅብረት ለማምለክና ለመጸለይ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ውስጥ መገኘት አለበት።

የሐዋርያት ሥራን ስናጠና ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ የበዙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እንደተመሠረቱ እናያለን። ለምሳሌ፥ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን፥ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፥ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ።



በየትኛውም ቦታ አንድ ሰው ሲድን ወዲያውኑ የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል። ከዚያ ቀጥሎ ነው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም አባል መሆን የሚገባው።

አንዲት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ሙሉው የክርስቶስ አካል መሆን ባትችልም፥ የአካሉ አንድ ክፍል ናት። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የሚገኙ አማኞች በአንድ የተወሰነ ስፍራ ብቻ ቢገኙም፥ የክርስቶስ አካል ክፍል ናቸው። ይህንን ለመረዳት ከሁለት የተለያዩ አጥቢያዎች የሆኑና ጌታን የተቀበሉ ሰዎች ታሪክ እንመልከት።

በሐዋርያት ሥራ 16፥27-31፥ የፊልጵስዩስ እስር ቤት ጠባቂ በክርስቶስ ሲያምን እናያለን። እንደዚሁ ደግሞ ወደ ፊልጵስዩስ ለንግድ ሥራ የመጣች በትያጥሮን ከተማ ነዋሪ የሆነች ሊድያ የምትባል ሴት ነበረች። ሊድያ በፊልጵስዩስ እያለች ጳውሎስ ሲያስተምር ወንጌል ሰምታ ትድናለች። የእስር ቤቱ ጠባቂና ሊድያ በዳኑ ጊዜ ወዲያው የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነዋል። እንደዚሁም ደግሞ ሁለቱም በሚኖሩበት ከተማዎች ባሉ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በአባልነት ይመዘገባሉ። ሊድያ ከትያጥሮን ስለሆነች ተመልሳ ስትሄድ የትያጥሮን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ትሆናለች። በፊልጵስዩስ ከተማ ከቈየች ግን በዚያ የምትገኘው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ትሆናለች። (በሚቀጥለው ገጽ የሚገኘውን ሥዕል ይመልከቱ)

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነፍሳት የሚማረኩባት ደግሞም የሚታነጹባት ጣቢያ ናት። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ወንጌል ይታወጃል። ወንጌልን ሰምተው ለዳኑት ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉበት መሠረታዊ ትምህርት ይሰጥባታል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ ሆስፒታል ናት። መንፈሳዊ በሽታ የያዛቸው ሕክምና ያገኙባታል። በዚያ መድኃኒት አለ፤ ፈዋሽና ታላቅ ሐኪም ይገኛል። ስለዚህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሰው ሁሉ አስፈላጊ ናት።






ምዕራፍ ሰባት

## ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

### 1) የእግዚአብሔር ቤተሰብነት - (ዮሐ. 1፥12-13)

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው በክርስቶስ አምነው በመዳን የአካሉ ክፍል በሆኑ አማኞች ነው። እነርሱ ክርስቶስን በግል ሕይወታቸው ስለተቀበሉ የእግዚአብሔር ልጆችና የቤተሰቡ አባል ይሆናሉ። ለጸሎት፥ ለአምልኮ፥ ለትምህርትና በኅብረት እንጀራ ለመቍረስ በአንድ አጥቢያ በየጊዜው ሲሰበሰቡ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ይመሠርታሉ።

### 2) የውኃ ጥምቀት

መጠመቅ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅ ትእዛዝ ማሟላት ነው (ማቴ. 28፥18-20፤ ማር. 16፥15-17)። በአዲስ ኪዳን እንደምናነበው፥ አባላት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጨመሩት የውኃ ጥምቀት በመውሰድ ነበር (ሐ.ሥ. 2፥41፤ 8፥12-13)። ዛሬም ሰዎች ወንጌልን ሰምተው ድነው የክርስቶስን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲጠመቁና በአንድነት መሰብሰብ ሲጀምሩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይሆናሉ። ነገር ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ የሚገኙት ሁሉ የተጠመቁ መሆን አለባቸው ማለት አይደለም። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች መሐል ገና ያልዳኑና ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የመስጠት ውሳኔን በተመለከተ የተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችም ለመገኘት ይችላሉ።

### 3) ቋሚ ሳምንታዊ ስብሰባዎች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን አባላት ቋሚ ሳምንታዊ ስብሰባዎች ማድረግ አለባቸው። በአንድ አጥቢያ የሚገኙ ሰዎች የሚሰበሰቡት በዓመት አንድ ቀን ብቻ ከሆነ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመባል አይችሉም (ይህ አባባል በየግል አማኞች መሆናቸውን አይከለክልም)። በየጊዜው አብረው ካልተሰበሰቡ በአንድነት ሊያደርጓቸው የሚገቡት :- ኅብረት፥ ጸሎት፥ ቃሉን መማርና የጌታ እራት መውሰድ ... ትርጒም የሚሰጡ ተግባሮች ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ ማንኛዋም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ዋና ጉዳዮች የምታከናውንበት ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ሊኖሯት ይገባል።

የእግዚአብሔር ቃል አማኞች በየጊዜው መሰብሰብን ቸል እንዳይሉ የሚጠይቀው ለዚህ ነው።

ቤተ ክርስቲያን የተጠራችውና አስቀድሞ የተወሰነችው እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ በማድረግና በማክበር ለመኖር ነው (ሐ.ሥ. 2፥42፤ ኤፌ. 1፥6:12:14)። ዳግም በቃሉ ከተወለድን በኋላ (1ጴጥ. 1፥23)፥ በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት የሚያድገው፥ የሚፋፋውና የሚጠበቀው በእንጀራ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ጭምር ነው (ማቴ. 4፥4)። ይህን ምግብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድናገኝ እግዚአብሔር መጋቢዎችን ሰጥቷል (ኤፌ. 4፥11)። ቃሉ በሌለበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የለም። በተጨማሪም አብረን ስንሰበሰብ የጌታን እራት በአንድነት እንካፈላለን። እነዚህ ድርጊቶች ከጐደሉ ልክ ከሰው አካል አስፈላጊ የሆኑ ብልቶችን እንደመቍረጥ ይቈጠራል። ከአካላችን አስፈላጊ ብልቶች ቢቈረጡ ደም ፈስሶ መሞት እንዳለ፥ ቤተ ክርስቲያንም ያለ እነዚህ ልምምዶች ቤተ ክርስቲያን ሆና መቆም አትችልም።

## 4) የመሰብሰቢያ ቦታ

የመሰብሰቢያ ቦታ ሊኖር ይገባል ሲባል፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን የግድ ሕንፃ መኖር አለበት ማለት አይደለም። በእድገት ደረጃ ላይ እያሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የመሰብሰቢያ ሕንፃ አልነበራቸውም። መጥቀስ የተፈለገው፥ በየጊዜው ለመሰብሰብ አንድ የመሰብሰቢያ ስፍራ (አድራሻ) ሊኖር እንደሚገባ ብቻ ነው።

## 5) የተመዘገቡ አባሎች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን አባሎች ያስፈልጋሉ። አባል ሳይኖር አንድ ሰው ብቻውን አማኝ እንጂ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆን አይችልም።

## 6) መሪዎች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን ከአባላት ሌላ መንፈሳዊ ምሪት የሚሰጡ መሪዎች :- እንደ ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናት፥ እረኛ የመሳሰሉት መኖር አለባቸው (በቅድሚያ የትኞቹ እንደሚሾሙ ለማወቅ የአጥቢያው ሁኔታ ይወስናል)።



## 7) ራስን ለማስተዳደር መቻል

በጀመርነው ርእስ ያለንን አሳብ ከመቋጨታችን በፊት ሳንጠቅሰው ማለፍ የማይገባን ነገር አለ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምናነበው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ አስተዳደር (Autonomy) አላት። "Autonomy" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘው ከሁለት የግሪክ ቃላት ነው።

"Autos" ማለት ‹ራስ› ("Self")፥

"Nomos" ማለት ‹ሕግ› ("Law") ማለት ነው።

"Autonomy" የሚለው ቃል የሚያሳየው የራስ ሕግ ወይም የራስ አስተዳደር እንዳላት ነው። አባሎቿን ለማስተዳደርና ‹ዲስፕሊን› ለማድረግ፥ የሚጠበቅባትንም መንፈሳዊ ሃላፊነት ለመወጣት ፍጹም ነፃነት አላት (ሐ.ሥ. 6፤ 15፤ 1ቆሮ. 6)። ይህ ፍጹም ነፃነቷ ለማደግ፥ ለመስፋፋት፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ያስችላታል። በዛሬው ጊዜ እንደ ቤተ እምነቱ የሥልጣን ተዋረድና መዋቅር አጥቢያውን በሚመለከቱ ጉዳዮች የራሳቸውን ውሳኔ ለመስጠት የሚችሉና የማይችሉም ቤተ ክርስቲያናት አሉ።

ከላይ ከ1-7 የጠቀስናቸው ሁኔታዎች መሟላት፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን ቢያንስ ቢያንስ መኖር አለባቸው የምንላቸው መለኪያዎች ናቸው። በተጨማሪም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከጠቀስናቸው ነገሮች ውጭ እንደ እድገትና ድርጅቷ ሌሎች ዘርፎች ሊኖሯት ይችላሉ።

በማገልገል እርሱን እንዲያገለግሉት እግዚአብሔር የሾማቸው አገልጋዮች መገኘት እንደሆነ ጠቅሰናል። በተጨማሪም እነዚህ አገልግሎቶች :-

1ኛ) ልዩ ጥሪ የሚያስፈልጋቸው አገልጋዮችች (ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ አስተማሪዎች፥ እረኞች (ፓስተሮች) እና ወንጌላውያን)፤

2ኛ) ልዩ ጥሪ የማያስፈልጋቸው አገልጋዮች፤ (እንደ ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናትና ሌሎችም አገልግሎቶች) እንደሆኑ ገልጸናል። ድቁናም ሆነ ሽምግልና በቃሉ ውስጥ የተጠቀሰ የከበረ አገልግሎት ነው። በዚህ ዐይነት ሁለት ቦታ የመደብናቸው አንዱን አገልግሎት ከሌላው ለማሳነስ ሳይሆን፥ በሁለቱ መካከል ግልጽና የሚታይ ልዩነት ስላለ በልዩነቱ ላይ የተመረኰዘ መደብ ለመስጠት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳየሁትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን በቈየሁባቸው ጊዜያት እንዳስተዋልኩት፥ እስከ ዛሬ ድረስ፥ «ጌታ በዲያቆንነት ወይም በሽማግሌነት በሙሉ ጊዜዬ ለማገልገል ተጠርቼአለሁ» የሚል አገልጋይ አጋጥሞኝ አያውቅም። ጌታ ግን ከፈለገ ለዲያቆኑ ወይም ለሽማግሌው ከአምስቱ ስጦታዎች አንዱን ሊሰጠው አይችልም ለማለት ማንም የሚደፍር የለም። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከተመረጡት ሰባት ዲያቆናት መካከል አንዱ የሆነው ፊልጶስ የወንጌላዊነትም ቅባት እንደነበረውና በወንጌላዊነት እንዳገለገለ እናያለን (ሐ.ሥ. 6፥5፤ 8፥4-13)።

## አምስቱ ጥንድ ስጦታዎች

‹ልዩ ጥሪ የሚጠይቁ› በሚለው መደብ ውስጥ ያስቀመጥናቸው አገልግሎቶች፥ «የአገልግሎት ስጦታዎች» ወይም «የትንሣኤ ስጦታዎች» በመባል ይታወቃሉ። እንደገናም እነዚሁ ስጦታዎች «አምስቱ ጥንድ ስጦታዎች» በሚል መለያም ይታወቃሉ። «አምስቱ ጥንድ ስጦታዎች» የተባሉበትም ምክንያት፥ ጌታ እነዚህን የሐዋርያነትን፥ የነቢይነትን፥ የአስተማሪነትን፥ የእረኝነትንና የወንጌላዊነትን ቅባት (ስጦታዎች) ለሰዎች ከሰጠ በኋላ ሰዎቹን መልሶ ከነስጦታቸው ለቤተ ክርስቲያን በመስጠቱ ነው።

> «እርሱም አንዳንዶች ሐዋርያት ሌሎችም ነቢያት ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ» (ኤፌ. 4፥11)።

ጥሪውና ሹመቱ (ስጦታው) ሳይሰጠው ማንም እኔ ሐዋርያ፥ ነቢይ፥ አስተማሪ፥ እረኛ ወይም ወንጌላዊ ነኝ ማለትና ራሱን መሾም አይችልም። ስለ እነዚህ ስጦታዎች ምንነት ስለ ጥሪያቸውና ስለ አገልግሎት ዝርዝራቸው ለማስረዳት ሌላ ራሱን የቻለ መጽሐፍ መጻፍ ይጠይቃል።



በዚህ ምዕራፍ ለመግለጽ የተፈለገው ከአምስቱ ስጦታዎች አንዱ ስለሆነውና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ዋና ሚና ስላለው የፓስተርነት (መጋቢነት) አገልግሎት ነው። ስለዚህ አገልግሎት ሙሉ ገለጻ ለማድረግ አሁንም ሌላ መጽሐፍ መጻፍ የሚጠይቅ ሰፊ አሳብ ስለሆነ፥ በዚህ መጽሐፍ የሚቀርበው በመጠኑ ነው።

## የፓስተርነት አገልግሎት

አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች በተዘረዘሩበት ኤፌሶን 4፥11 ላይ ፓስተር (እረኛ) የሚለው ቃል፥ በግሪኩ አዲስ ኪዳን የተጠቀሰው «ፖይሜን» (poimen) በሚለው ቃል ነው። ትርጒሙም «የበጎች ጠባቂና ተንከባካቢ» ማለት ነው። ፖይሜን (ፓስተር)፥ በግሪኩ አዲስ ኪዳን 18 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ነገር ግን በእንግሊዝኛው ትርጒሞች ይህንን ቃል እንዳለ ተጽፎ የምናገኘው በኤፌሶን 4፥11 ብቻ ነው። በቀሩት ቦታዎች ሁሉ የተጠቀሙት ፓስተር የሚለውን ቃል ሳይሆን «ሸፐርድ» (Shephered) ወይም «እረኛ» የሚለውን ነው። ‹ፓስተር› የአማርኛ ቃል ባይሆንም የተለመደ ሆኖአል። በአማርኛ ፓስተር፥ መጋቢ፥ እረኛ የሚለው ቃል ምንም ልዩነት የለውም። የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ግን ፓስተር የሚለው ቃል አንድ ጊዜ በመጠቀሱ ወደ ግሪኩ አዲስ ኪዳን ሄደው ቃሉ እንዳለ የተጻፈበትን መጥቀስ ይወዳሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፓስተር አገልግሎት የሚከተለውን እውነት ያስተምረናል።

### ሀ) ፓስተር የበጐች መጋቢ፥ ጠባቂና አስማሪ ነው

የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ዋና ሥራ መመገብ፥ መጠበቅና ማስማራት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ የሰጠው ሦስት ትእዛዛት እነዚህን ሦስት ተግባሮች የሚያካትቱ ነበሩ (ዮሐ. 21፥15-19)። ጴጥሮስ እንዲመግብ፥ እንዲጠብቅና እንዲያስማራ ታዘዘ።

መብላት፥ መጠበቅና መሰማራት ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ፍላጐት ነው። ያልበላ አይኖርም፥ አያድግም፤ ተወልዶ ወላጆቹ ከክፉና ከአደጋ ያልጠበቁት ደህና ሆኖ መኖር አይችልም። የሚጠቅመውንና የሚረባውን ያልመረጡለት ሕፃን አሰማሪ እንደሌለው መንጋ መጐዳቱ አይቀርም። መወለድ አንድ ነገር ነው፤ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን እነዚህን ሦስት እንክብካቤዎች ማግኘት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። መውለዱን ማንም ይወልዳል፤ እነዚህን ሦስት እንክብካቤ አግኝቶ ማደግ ግን በጥሩ ወላጆችና አሳዳጊዎች መባረክ ነው። እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በማይሟሉበት

ትልቅ ጉዳት ይደርሳል። የፓስተር አገልግሎት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እነዚህንየሚያሟላ ስለሆነ፤ መጋቢ፥ ጠባቂና አስተማሪ ያለው ቤተ ክርስቲያን የታደለ ነው።

ጊዜአቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው፥ የተከፈተ መጽሐፍ ዘርግተው፥ በጉልበታቸው ተንበርክከው ሰማይን በመዳሰስ ለመንጋው የሚሰጡትን ምግብ ከእግዚአብሔር የሙቀበሉ ፓስተሮች ባሉበት ስፍራ ትልቅ ለውጥ አለ። መጋቢ በሌለበት ቤተ ክርስቲያን፥ በምእመኑ ላይ ክሳት፥ ግርጣትና የጉድን መቈጠር መታየት ይችላል። በዚህ ዐይነት ከዘለቀም ከፍተኛ ችግር መከሰቱ የማይቀር ነው።

የፓስተር አገልግሎት ከመመገብ አልፎ የመንጋውን ደኅንነት ተግቶ መጠበቅ ነው። በጎች ተኩላን የመሰሉ ጠላቶች እንዳሏቸው፥ ቤተ ክርስቲያንም ነቅቶ የሚጠብቅ እረኛ ከሌላት፥ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሊቀራመቷት ሰይጣን ስብዕናቸውን ተውሶ የሚጠቀምባቸው ብዙዎች ናቸው። «ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች» ከመካከልም መነሣት እንደሚችሉ በቃሉ የተገለጸና (ሐ.ሥ. 20፥26-31) በቤተ ክርስቲያንም ታሪክ የተከሰተ ጉዳይ ነው።

ማስማራትን በተመለከተ ደግሞ የፓስተር አገልግሎት መንጋው የሚመገበውን ምግብና የሚጠጣውን ውኃ መምረጥ ነው። መልካም እረኛ በጎቹን በለመለመ መስክ እንዲሰማሩ እንደሚያደርግ፥ ፓስተርም መንጋውን ወደ ለመለመ መስክ ይመራል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤ ያሰማራል። ለእነርሱ የሚጠቅመውን በመምረጥና ደኅንነታቸውን በመጠበቅ ተግቶ የተጣለበትን አደራ ይፈጽማል።

## ለ) ፓስተር የመንጋው አስታጣቂና አሳዳጊ ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ስለተሰጡት አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ባስረዳበት ምዕራፍ እንደገለጸው፥ የፓስተርነትን አገልግሎት ጨምሮ የስጦታዎቹ ዓላማ ቅዱሳንን ማስታጠቅና ማሳደግ ነው (ኤፌ. 4፥7-11)። በዚህ ቃል መሠረት ከአምስቱ ስጦታዎች አንዱ የሆነው ፓስተር፥ ተግባሩ ምእመናኑን ማስታጠቅና ማሳደግ ነው። አማኞች አማኝ ብቻ ሳይሆኑ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ያደርጋል። ያለ አገልግሎት የቆመን መኪና መሪ ማንቀሳቀስ ከባድ ነው። ክርስቲያኖች ዝም ብለው፥ አገልጋይ ሳይሆኑ እንዳይኖሩ ስይፋቸውን በመሳልና በማስታጠቅ በአገልግሎት ላይ ያሰልፋል። ይህንንም ተግቶ ሲያደርግ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው አካሉ ሁሉ ይታነፃል፤ በፍቅርም እያደገ ፍጹም ወደ መሆን ይደርሳል (ኤፌ. 4፥12-15)።



## ሐ) ፓስተር መሪና አስተዳዳሪ ነው

ሌላው የፓስተር አገልግሎት፥ እንደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱ የውስጥ ደንብ መሠረት፥ ከተመረጡ ሽማግሌዎች ጋር በመመካከር ለመንጋው አቅጣጫ በመስጠት መምራትና ማስተዳደር ነው (ዕብ. 13፥7:17:24)። «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በሐዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ» (ዕብ. 13፥17)።

አገዛዝ (rule) ፥ ሦስት ነገሮችን ያካትታል። እነርሱም፤

1ኛ/ አስተዳደር (Administration)

2ኛ/ ጥበቃ (Protection)

3ኛ/ አገልግሎት (Ministration) ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን ራስ ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር ሌላ ሰብዓዊ ራስ ሊኖራት አይችልም። ፓስተር የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰብዓዊ መሪ ነው። አለቃ አለው፤ አለቃውም የእረኞች አለቃ የሆነው ጌታ ነው። ፓስተር እንደ አለቃው ዝቅ ብሎ ሕዝብን በማገልገል ጌታውን የሚያገለግል ሎሌ ነው።

የፓስተር አስተዳደራዊ አገልግሎት ለምእመኑ አቅጣጫ መስጠትና መምራት ነው። የማንኛውም ድርጅት ስኬት ሆነ ውድቀት በመሪው የአመራር ችሎታ ላይ ይመካል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ይኸው ሐቅ ሲከሰት ይታያል። ጠንካራና በሳል መሪዎች ባሉበትና ደካማ መሪዎች ባሉበት አብያተ ክርስቲያናት አንዳንድ ልዩነቶች መታየታቸው አይቀርም።

አገልግሎትን (Ministration) በተመለከተ ደግሞ፥ ፓስተር ተቈጥረው የማያልቁ አገልግሎቶችንና ሥርዓቶችን ያከናውናል፤ ምክርንና ሌሎችን አገልግሎቶች ሁሉ ይፈጽማል/ያስፈጽማል። ሎሌያዊ አገልግሎት መስጠት ዓላማው ነው።

የፓስተርነት ጥሪ ጸጋው እንዲኖር ይጠይቃል። ጥሪው ካለ ጸጋው መኖሩ አጠራጣሪ አይደለም። ሆኖም ግን፥ አንድ ሰው ጥሪው እንዳለውና እንደሌለው ሊያውቅ የሚችልበትን መፈተኛዎች ሁሉ በማድረግ ለፓስተርነት መጠራቱን ማረጋገጥ አለበት። አንድ ጊዜ አንድ ገበሬ በማረስ ላይ እያለ ወደ ሰማይ ቀና ሲል ደመና ያያል። ደመናዎቹን ትኩር ብሎ ሲመለከት "G.P.C." የሚባሉትን የእንግሊዘኛ ፊደሎች ያየ መሰለው። ከዚያም ለፊደሎቹ የሚከተለውን ትርጉም ሰጣቸው፤

G ማለት go - ሂድ

P ማለት preach - ስበክ

C ማለት Christ - ክርስቶስ።

ስለዚህ ጌታ ሄደህ ክርስቶስን ስበክ (go preach Christ) ብሎኛል አለና ሥራውን ለቆ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት መውጣት ፈለገ። ሆኖም ጉዳዩን ለልብ ወዳጁ ሲያማክር ያ ወዳጁ 'g.p.c.' ማለት አንተ እንደተረጐምከው ለመሆኑ እርግጠኛ ነህን? ምናልባትስ፤

g ማለት go - ሂድ

p ማለት plow እረስ

c ማለት corn በቆሎ ቢሆንስ? ጌታ ያለህ ገበሬ ስለሆንክ ሄደህ በቆሎ አምርት (go plow corn) ቢሆንስ አለው።

ልዩ ጥሪ በሚጠይቁ አገልግሎቶች ዘለን ራሳችንን ከመሰየማችን በፊት ጥሪው ለመኖሩ ማረጋገጥ፤ እንዲሁ በእኛ ጸጋው እንደሚታይ ከሌሎች ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ሰዎችን በመስጠቱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ደስ ሊለን ይገባል። የክርስትና መሥራችና ራስ የሆነው ክርስቶስ የከበረውን እውነት በተመለከተ ሦስት ነገሮች አድርጓል፤ ሀ) የከበረውን እውነት (ቃሉን) ለማጥፋት በዘመናት ሁሉ የተነሡ ሰዎች ነበሩ፤ ነገር ግን አልተሳካላቸውም። ዛሬም የከበረው እውነት አለ፤ አልጠፋም። «የከበረው እውነት እንዳይጠፋ ማን ጠበቀው?» ብለን ስንጠይቅ፡ መልሱ «እግዚአብሔር ነው» የሚል ነው። በከበረው እውነት ላይ የተነሡት ብዙዎች ቢሆኑም፥ ጌታ ይህ እውነት እንዳይጠፋ ራሱ ጠብቆ ለእኛ እንዲደርሰን አደረገው። ለ) የከበረውን እውነት በኃይል ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን፥ በመበረዝ፥ መልኩን በመቀየርና በመለወጥ ቀስ በቀስ እንዲጠፋ ለማድረግ ኑፋቄያዊ ትምህርቶች በዘመናት ሁሉ ተነሥተዋል። ነገር ግን በኑፋቄያዊ ትምህርቶች እንዳይበከልና እንዳይበላሽ ይህን የከበረ እውነት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአማኞች ልብ ውስጥ እንዲጠበቅ አደረገው። ሐ) ቤተ ክርስቲያን በዚህ በከበረ እውነት እንድትታነጽና እንድትበለጽግ ይህንን የከበረ እውነት በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኖረው።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ስለሰጣቸው አገልጋዮች የተመሰገነ ይሁን።



## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ተልእኮ እንደሚከተለው ነው፤

### ሀ) የተጀመረውን መቀጠል

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ተልእኮ በሙሉ፥ «የተጀመረውን መቀጠል» (Continuation) በሚለው አጭር ሀረግ ማጠቃለል ይቻላል። የተጀመረውን መቀጠል ማለት ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር የመጣበትን ዋና ተልእኮ መቀጠል ማለት ነው። ጌታ ክርስቶስ ለምን ወደዚህ ዓለም እንደመጣ ራሱ ሲናገር፥ «የሰው ልጅ የጠፋትን ለመፈለግና ለማዳን መጥቶአል» ብሏል (ማቴ. 18፥11)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሳለ ያስተማራቸው ትምህርቶች፥ ያደረጋቸው ተአምራቶችና ያሳያቸው የርኅራኄ ሥራዎች ሁሉ በአራቱም ወንጌሎች ውስጥ በዝርዝር ተካተዋል። የሉቃስ ወንጌልን በምሳሌነት ብንመለከት፥ ክርስቶስ በምድር ሳለ ያስተማራቸውና ያደረጋቸው ነገሮች በስፋት ተጽፈዋል። ነገር ግን ሉቃስ በጻፈው ሌላው መጽሐፉ፥ በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ላይ ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ይነግረናል።

> «ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ፥ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ» (ሐ.ሥ. 1፥1-2)።

ከዚህ ቃል የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች እንረዳለን፤

1) ክርስቶስ በምድር ሳለ ያስተማረውና ያደረገው ነገር ተጀመረ እንጂ ገና ከመጨረሻው ግብ አልደረሰም። ክርስቶስ የመጣበትን የመስቀል ሥራውን ፈጽሞ ለሰው ልጆች የደኅንነት በር ከፍቷል። ነገር ግን ወደ ሰማይ የዐረገው በመሥዋዕትነቱ የተገኘው ደኅንነት ለሰዎች ሁሉ ሳይዳረስ ነው። ወደ ምድር መጥቶ በመስቀል የሞተው፥ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ ነው (ዮሐ. 3፥16)። ነገር ግን በጴንጤቆስጤ ቀን በአንድ ላይ የነበሩትን

- የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ እንዲታጠቁ ታደርጋለች (ኤፌ. 6፥10-18)፤
- በእውነተኛ አምልኮ የምእመናን ሕይወት እንዲታነጽ ትተጋለች (ዮሐ. 4፥10፤ 1ቆሮ. 14፥26)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ስጦታዎችን ሰጥቶ ሰዎቹን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበት ምክንያት ይህ ነው (ኤፌ. 4፥11-13)። ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችም የተሰጡት ሥራው እንዲሠራና የአማኞች ሕይወት እየታነጸ ክርስቶስን ወደመምሰል እንዲያድግ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ስለ አማኞች መመረጥ ባሰበ ጊዜ ሁሉም «የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰኖአል» (ሮሜ 8፥29)።

### መ) ምእመናንን ማስታጠቅና በአገልግሎት ላይ ማሠማራት

ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማስታጠቅና ማሰለፍ (equipping the Saints)፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሃላፊነት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጠራን የዘላለም ሕይወት ሊሰጠን ብቻ ሳይሆን እንድናገለግለውም ነው። ደኅንነትና አገልግሎት በአንድ ጥቅል የሚመጡ ነገሮች ናቸው። ሁላችንም ለመስበክ አልተጠራን ይሆናል፤ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ምስክር መሆንና ለታላቁ ተልእኮ የበኩላችንን አስተዋጽኦ በተለያየ መንገድ መስጠት እንችላለን። ከጨለማው ወደሚደነቀው ብርሃን የተጠራነው የእርሱን በጎነት ለመናገር ነው (1ጴጥ. 2፥9)።

ቤተ ክርስቲያን የምእመናን ሕይወት እንዲታነጽ ካደረገች በኋላ በአገልግሎት እንዲሰማሩ ደግሞ ታስታጥቃለች። በየጊዜው በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ሥልጠናዎች የሚሰጡበት ምክንያት ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ያለው ዓላማ አማኝ ብቻ ሆነን እንድንቀመጥ ሳይሆን፥ እንድናገለግለው ጭምር ነው (ሮሜ 12፥6፤ 1ቆሮ. 12፥14-21)።

### ሠ) የተቸገሩትን መርዳት

የተቸገሩትን መርዳት (Benevolence)፥ ቤተ ክርስቲያን ክርስትናን በተግባር የምታሳይበት ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እስራኤልን ከነቀፈበት ነገሮች አንዱ ችግረኞችን፥ መበለቶችን፥ እርዳታ የሚፈልጉትን ሁሉ ቸል በማለቷ ነው (ኢሳ. 1፥17፥23፤ ኤር. 5፥25-31፤ 7፥5-7፤ ዘካ. 7፥8-14)። በአዲስ ኪዳን ውስጥም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዐይነት ሃላፊነት እንዳለባት በግልጽ ተጽፎአል (ገላ.



6፥9-10፤ ያዕ. 1፥26-27)። ከመጀመሪያዎቹ አማኞችም መካከል እንደ ዶርቃ ያሉ በመልካም ምግባር የተሞሉ ሰዎች ነበሩ (ሐ.ሥ. 9፥36-43)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግረኞችን ትረዳ እንደነበር ተጽፏል (ሐ.ሥ. 2፥44-45፤ 2ቆሮ. 9፥12-13፤ 1ጢሞ. 5፥1-16፤ ያዕ. 1፥27)።

ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ በግሉ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ጊዜው ሁኔታና እንደ አቅሟ የተቸገሩትን መርዳት አለባት።

አንዳንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ዋና ተልእኮአቸውን ትተው ተልእኮአቸው ያልሆነውን ነገር በመሥራት ይደክማሉ። እርግጥ ነው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አቅሟ በፈቀደው መጠን ለአካባቢዋ ጠቃሚ በሆነ ነገር ሁሉ መሰለፍ ይገባታል። ነገር ግን መጠንቀቅና ማወቅ የሚገባት ነገር ቢኖር ትኩረት የምታደርግበት ማናቸውም ዐይነት ተግባር ዋና ተልእኮዋን ከመፈጸም እንዳያግዳት ነው።

## ምዕራፍ አሥር

# የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት

በምዕራፍ ሰባት ትምህርታችን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን እንደሆነ የሚከተለውን ትርጉም ሰጥተን ነበር።

«የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለት ዳግም በመወለድና ደኅንነትን በመቀበል የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑና በአንድ አጥቢያ በመገኘታቸው የክርስቶስን ትእዛዝ ለመፈጸም፤ ለአምልኮ፥ ለኅብረት፥ ለትምህርትና የጌታን ራት አብሮ ለመካፈል እግዚአብሔር ለአጥቢያው በሾማቸው አገልጋዮች መሪነት የእግዚአብሔርን ሥራ አብሮ ለመሥራት፥ በፈቃዳቸው ቃል ኪዳን ያደረጉና በየጊዜው አብረው የሚገናኙ አማኞች ስብስብ ማለት ነው»።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለት በፈቃዳቸው ቃል ኪዳን ያደረጉና በየጊዜው አብረው የሚገናኙ አማኞች ስብስብ ከሆነ፥ አብረው የሚሰበሰቡት አማኞች ደግሞ የዚያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ይባላሉ።

አያሌ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የአባላት ቃል ኪዳን አላቸው። ከዚህ በታች የሚገኘው ቃል ኪዳን በሂውስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን የአባልነት ቃል ኪዳን ነው።

### ለቤተ ክርስቲያኔ እድገት የምገባው የአባልነት ቃል ኪዳን :-

1. የቤተ ክርስቲያኔን አንድነትና ኅብረት ለመጠበቅ፤

ከአባላት ሁሉ ጋር ያለኝን ግንኙነት በፍቅር ላይ የተመሠረተ አደርጋለሁ።

«... እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ» (1ጴጥ. 1፥22)።

ሃሜትን ለማስወገድ በማንኛውም ዐይነት ሃሜት ባለመሳተፍ እቃወማለሁ።

«ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፤ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ» (ኤፌ. 4፥24)።



መሪዎች የሚያወጡትን መመሪያ አከብራለሁ።

«ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ... ለነፍሳችሁ ይተጋሉ» (ዕብ. 13፥17)።

2. በቤተ ክርስቲያን አባልነቴ የሚጠበቅብኝን ሃላፊነት ለመወጣት፤

ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት እጸልያለሁ።

«ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ተሰ. 5፥16)።

ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያኔ እጋብዛለሁ።

«ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጡና ይገቡ ዘንድ ግድ በሉዋቸው» (ሉቃ. 14፥23)።

እንግዶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ መልካም አቀባበል አደርጋለሁ።

«ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ» (ሮሜ 15፥7)።

3. በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቶች ውስጥ ለመሳተፍ፤

ዝንባሌዬንና ስጦታዬን ለማወቅ እተጋለሁ፤

«... እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ» (ሮሜ 15፥7)።

በመጋቢዬና በአስተማሪዎቼ እታነጻለሁ፤

«... ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ» (ኤፌ. 4፥13)።

የአገልጋይ ልብ እንዲኖረኝ እተጋለሁ፤

«... ከእኔ ጋር በጸጋ ተካፋዮች ስለሆናችሁ በልቤ ትኖራላችሁና ስለ ሁላችሁ ይህን ላስብ ይገባኛል»።

4. የቤተ ክርስቲያኔን አገልግሎት ለመደገፍ፤

ስብሰባዎችን በታማኝነት እሳተፋለሁ፤

«በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው ...» (ዕብ. 10፥25)።

የክርስትናን ኑሮ በመኖር እግዚአብሔርን በሕይወቴ አሳያለሁ።

«... በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12፥2)።

አሥራቴንና መባዬን በታማኝነት እሰጣለሁ።

«የምድርም አሥራት ወይም የምድር ዘር ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው» (ዘሌዋ. 27፥30)።

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ትርጉም፤

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ማለት፥ ስለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ትርጉም የዘረዘርናቸውን ዓላማዎችና የእግዚአብሔር ቃል የሚያዘውን ሁሉ ከሌሎች አማኞች ጋር አብሮ ለመፈጸም ራሱን በክርስቶስ ሥልጣን ሥርና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አመራር ሥር ለማድረግ በፈቃዱ የወሰነ አማኝ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ሁሉ በምድር ላይ የሚከናወንባት ጣቢያ ናት (ሐ.ሥ. 5፥11፤ 8፥1:9-31፤ 13፥1-3፤ 14፥23-27፤ 15፥41፤ ሮሜ 16፥1፤ 1ቆሮ. 1፥2፤ ገላ. 1፥2፤ ኤፌ. 1፥1፤ ቈላ. 1፥2፤ 1ተሰ. 1፥1፤ 1ጴጥ. 5፥13)። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ የምትወክልና ሥራውን የምትሠራ ተቋም ናት። እንደ እርስዋ ሕያውነት የሌላቸው ሌሎች ተቋማት እንኳን ለጋራ ግብ የሚሠሩ አባላት አሏቸው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ሥራ አብሮ ለመሥራት በአንድ አጥቢያ ለመሰብሰብ የወሰኑ አባላት አሏት።

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የሚቻልበት መንገድ፤

1) *መዳንና መጠመቅ* - በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምናየው ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አባልነት የሚጨመሩት ወንጌልን ሰምተው በሚድኑበትና በሚጠመቁበት ጊዜ ነው። ከዚህ በፊት በዝርዝር እንዳየነው፥ አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከመሆኑ በፊት ወንጌልን ሰምቶ በመዳን የክርስቶስ አካል የሆነችው (የማትታየዋ) ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለበት። የክርስቶስ አካል አባል ሳይሆኑ የውሃ ጥምቀት በመውሰድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ይቻላል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም መዳናችንን እስከመሰከርንና አስፈላጊውን ሁሉ እስካሟላን እንዳንጠመቅ አይከለክሉንም። ነገር ግን በዚህ ዐይነት መንገድ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መዝገብ ላይ ስማችንን ብናስመዘግብም ክርስቶስ በያዘው የሕይወት መዝገብ ላይ ስማችን አይኖርም። በክርስቶስ መዝገብ ያልታወቀ ማንም፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ቢሆንም የክርስቶስ አካል ብልት አይደለም። በመሠረቱ ግን አንድ ሰው የውሃ ጥምቀት ከወሰደ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ይችላል።



2) በዝውውር ምክንያት - አንድ አማኝ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚዘዋወርበት ጊዜ በሄደበት አዲስ ቦታ በሚገኘው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠይቆ በአባልነት መመዝገብ ይችላል። የዚህ ዐይነቱ ልምምድ በመጀመሪያው መቶ ዓመታት አብያተ ክርስቲያናትም መካከል የተለመደ ነበር። ሆኖም በአሁኑ ዘመን አንድ ሰው ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ በሚሄድበት ጊዜ፥ ከነበረበት ቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱና ስለ አገልግሎቱ የሚገልጽ መሸኚ ደብዳቤ ይዞ ቢመጣ ይመረጣል። ምክንያቱም ለእርሱም ሆነ በአባልነት ለሚመዘገብባት ቤተ ክርስቲያን ይህን የመሰለው ጤናማ ልምምድ እጅግ ጠቃሚ ነው።

3) በፈቃደኝነት

ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት በሰጠነው ትርጉም፥ «በፈቃዱ የወሰነ» የሚለውን ቃል ልናሰምርበት ይገባል። ምክንያቱም ከላይ በጠቀስናቸው ሁለት መንገዶችም ሆነ በሌላ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል የምንሆነው ተገደን ሳይሆን በራሳችን ምርጫና ፈቃድ ስለሆነ ነው። ደኅንነት የግል ምርጫና ውሳኔ እንደሆነ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አባልነትም በግል ምርጫና ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ምንም ዐይነት ግዴታ የለበትም።

የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ግን የእኛ ፈቃድና ምርጫ አይጠየቅም። ደኅንነትን በተመለከተ ጉዳይ የእሺታ ውሳኔ ያደረገ ሁሉ ወዲያው (ያለ ፈቃዱ) የክርስቶስ አካል ብልት (አባል) ነው። ምርጫው በክርስቶስ አምኖ ለመዳን ወይም ላለመዳን ብቻ ነው። በራሱ ምርጫና ውሳኔ ክርስቶስን የተቀበለ ሰው ሁሉ ወዲያው የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ግን የግል ምርጫና ውሳኔ ጉዳይ ነው፤ አባል ለመሆን ካልፈለግህ አትገደድም። ከሆንክም በኋላ ደግሞ ስምህን ከአባልነት መዝገብ ለማውጣት ከፈለግህ ፍጹም የሆነ መብትና ነፃነት አለህ። እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ የዲሲፕሊን ምክንያቶች የተነሣ፥ የእግዚአብሔር ቃል የሚጠይቀውን ሁሉ ከአሟላች በኋላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድን አማኝ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ለመሰረዝ መብት አላት። በዚህ ነጥብ ላይ በመጽሐፉ መጨረሻ በሰፊው እንነጋገርበታለን።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስትመርጥ መመልከት የሚገባህ መመዘኛዎች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስንመርጥ የሚከተሉትን ሁኔታዎች መመልከት ይገባል።

### ሀ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኗ ለእግዚአብሔር ቃል ያላት አመለካከት፤

የእግዚአብሔርን ቃል እንዳለ የሚቀበሉና መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ስሕተት የሌለበት፥ በእምነት ጉዳዮች የመጨረሻው ባለሥልጣን እንደሆነ መቀበላቸውን ማረጋገጥ (2ጢሞ. 3፥16፤ 2ጴጥ. 1፥20-21)።

### ለ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኗ የእምነት አንቀጽና አስተምህሮ፤

የሚያስተምሩት መሠረታዊ ትምህርት (አስተምህሮ) (Basic doctrines) የሚለማመዱት ልምምድ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሆኑን ማረጋገጥ።

### ሐ) የሚሰጡት አገልግሎትና የሚለማመዱት ልምምድ፤

ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን አመለካከትና የሚያስተምሩትን አስተምህሮ (ዶክትሪን) ማወቅ፤ እንደዚሁም የሚለማመዱት ልምምድ ሁሉ ከቃሉ ያልወጣ መሆኑን ማረጋገጥ አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲመርጥ ሊመለከት የሚገባውን ነገር ሁሉ ያጠቃልላል።

በመጀመሪያዎቹ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ታደርጋቸው የነበሩ ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፤

1. ኬሪግማ (Kerygma)፤ ማስተማርና የምሥራቹን መስበክ፤
2. ኮይኖኒያ (Koinonia)፤ ኅብረትና መረዳዳት፤
3. ማርትሪያ (Martyria)፤ ምስክር መሆንና መመስከር፤
4. ዲያኮንያ (Diakonia)፤ አገልግሎት መስጠት (ለሚያምኑና ለማያምኑ)።



እነዚህ ሁሉ ተግባሮች በትክክሉ የሚፈጸሙት የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ትክክል የሆነ አቋም ሲኖራት ነው። ለዚህ ነው በመጀመሪያይቱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን (የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን) ይሰበሰቡ የነበሩት አማኞች ይተጉበት ከነበሩት ነገሮች ውስጥ የሐዋርያት ትምህርት በቅድሚያ የተጠቀሰው (ሐ.ሥ. 2፥42)። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ከሐዋርያት ትምህርት ውጤት የተነሣ ነው (ሐ.ሥ. 2፥14-42)። በቍጥር 42 ላይ በሐዋርያት ትምህርት ስለ መትጋት የተጠቀሰው ቃል በግሪክ የሚለው "Proskarterounters" ነው። ትርጕሙ «በቃሉ ጠንካራ መሆን» ማለት ነው። ቃሉን በመማር ጠንካራ መሆን ቤተ ክርስቲያን ታደርግና ትለማመድ ለነበሩት ነገሮች ሁሉ ዋናና አስፈላጊ ነገር ነው። ስለሆነም አባል የምንሆንበትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስንመርጥ ከሁሉ በፊት ትኩረት ልንሰጥ የሚገባው ለዚህ ጉዳይ ነው።

### መ) ሌሎች መመዘኛዎች

እንደየግለሰቡ ምርጫ ሌሎችም የተለያዩ መመዘኛዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፤ የቤተ ክርስቲያኑ አባሎች ብዛት ወዘተ.

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆኑ ክርስቲያን መሆን ይቻላልን?

አንድ አማኝ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሌለበት አካባቢ ከኖረ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አይችልም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ባለበት አካባቢም ቢኖር አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆን ክርስቲያን መሆን ይችላል።

ነገር ግን፥ የቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆኑ ክርስቲያን መሆን ማለት ፦

ሀ) ትምህርት ቤት ሳይሄዱ ተማሪ እንደመሆን፥

ለ) ሰራዊት ውስጥ ሳይገቡ ወታደር እንደመሆን፥

ሐ) ታክስ ሳይከፍሉ ወይም በመምረጥ መብት ሳይጠቀሙ እንደሚኖሩ የአንድ አገር ዜጋ መሆን፥

መ) ያለምንም ደንበኞች ነጋዴ እንደመሆን፥

ሠ) ሰው በማይኖርበት ደሴት ሥራ (Business) እንደመክፈት፥

ረ) አንባቢ እንደሌለው ደራሲ መሆን፥

ሰ) አጨብጫቢና አድማቂ በሌለበት ከበሮ እንደመምታት፥

ሸ) ልጆች ሳይኖሩ ወላጅ እንደመባል፥

ቀ) ቡድን ሳይገቡ የኳስ ተጫዋች ነኝ እንደማለት፥

በ) ምናኔ ላይ ሆኖ የፖለቲካ ሰው ነኝ እንደማለት እና

ተ) ቀፎ እንደሌለው ንብ መሆን ነው።

በአጭሩ የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ለማንኛውም አማኝ አስፈላጊና አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት አስፈላጊነት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የሚያስፈልግበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ) ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ለማድረግና ግንኙነት ለመመሥረት ይረዳል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ እንዲህ ይላል፥ «ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው» (ሮሜ 1፥12)።

የክርስትናን ሕይወት ለብቻ በመኖር ሊወጡት ያስቸግራል። አብሮ መጽናናት የሚቻለው ሐዋርያው እንዳለው አንዱ ከሌላው ከሚያገኘው እርዳታና ድጋፍ ነው። እምነት ባላቸው ሰዎች መካከል መገኘት የእኛንም እምነት ያሳድጋል። በሚበረታቱ መካከል መገኘትም ያበረታታል። ሁሉም አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችልበት ኅብረት ውስጥ ሁሉም ይጠቀማል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን ሁላችንም እንጽናናለን ያለው ለዚህ ነው። ታዲያ እንዲህ ያለው ነገር የሚቻለው በብቸኝነት በመኖር ሳይሆን፥ ኅብረት ባለበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ስንመሠርት ነው።

### ለ) ለሕይወታችን ተጠያቂነት እናበጃለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ፥ «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ» (ዕብ. 10፥24) ካለ በኋላ፥ «በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው» ይላል (ቍ. 25)።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ስንሆንና በሳምንታዊ ቋሚ ስብሰባዎች ስንገናኝ፥ እርስ በርስ እንተያያለን። ሁል ጊዜ በመተያየታችንና በመገናኘታችን ስለምንገኝበት መንፈሳዊ ሁኔታ እንጠያየቃለን። ስንደክም «አይዞህ በርታ» እንባባላለን። አንዳችን ለሌላው በየጊዜው እንጸልያለን። ይህ ሁሉ መተሳሰብና መጠያየቅ ወደር የማይገኝለት ጥቅም ይሰጠናል።



በተጨማሪም አንዳችን ለሌላው ተጠያቂነት እንዲኖረን ያደርጋል። ስለዚህ ስለ እኛ የሚያስቡና የሚጠይቁን ከመኖራቸው የተነሣ ለብቻ ብንሆን ሊሆን እንደሚችለው ግዴለሾች አንሆንም።

### ሐ) መከራና ችግር በገጠመን ጊዜ የሚረዱን ወገኖች እናገኛለን።

ሕይወት ብዙ ችግርና መከራ አለባት። አማኝም ከዚህ ችግርና መከራ ነፃ አይደለም፤ የድርሻውን ይቀበላል። በመከራና በችግር ላይ ስንሆን የሚያስቡንና የሚረዱን ወንድሞችና እኅቶች ማግኘት የምንችለው አባልነት በመሠረትንበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ቤተሰብነትን መመሥረት ነው። እንደ አንድ ቤተሰብ አባልነታችን የአንዱ ደስታ የሌላው ደስታ፥ የአንዱም ሐዘን የሌላው ሐዘን ይሆናል (ሮሜ 12፥15)። አንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከማል (ገላ. 6፥2)፤ በወንድማማችና እኅትማማች መንፈስ እርስ በእርስ እንረዳዳለን።

> «አንዱም ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል» (1ቆሮ. 12፥26)።

### መ) በመንፈሳዊ ሕይወት እናድጋለን።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ስንሆን ለእድገታችን የሚጠቅመውን አስፈላጊ እንክብካቤ ሁሉ ስለምናገኝ ሕይወታችን መንፈሳዊ ብስለት (Maturity) ያገኛል (ኤፌ. 4፥11-16)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኘው እንክብካቤ ውጭ እንዲህ ካለው እድገት መድረስ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አንድ አማኝ አባል ለመሆን የሚያደርገው ውሳኔ በአማኞች መካከል ተገኝቶ በቃሉ እየተኰተኰተ ክርስቶስን ወደ መምሰል ለማደግ ያለውን ፍላጎት ይገልጻል።

### ሠ) ሌሎችን ለማገልገል እድል ይሰጣል።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት እንደስጦታችንና ችሎታችን ሰዎችን በማገልገል እግዚአብሔርን እንድናገለግል ዕድል ይሰጣል።

### ረ) ልጆቻችን በእግዚአብሔር ቃል ተኰትኵተው እንዲያድጉ ያደርጋል።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ስንሆንና ወደ ቋሚ ስብሰባዎች ስንመጣ ቤተሰባችንንም ይዘን ልንመጣለን። ቤተ ክርስቲያን ለልጆች እንደ

ዕድሜያቸው የተዘጋጀ የሰንበት ትምህርት ትሰጣለች። ስለዚህ ልጆቻችን በእግዚአብሔር ቃል ተኰትኩተው ያድጋሉ።

ከሁ-ረ ባሉት ነጥቦች የተመለከትናቸው አሳቦች ሁሉ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ለአንድ አማኝ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ክርስቲያን ሆኖ ለብቻዬ የሚባል ነገር የለም። አንድ ጊዜ አንድ ፓስተር «ለብቻዬ መሆን እችላለሁ» ብሎ በቤቱ የቀረ አባል ለመጠየቅ ሄደ። ከዚያ ሰው ቤት ሲደርስ ሰውዬው በቤቱ ቁጭ ብሎ እሳት ሲሞቅ አገኘው። ፓስተሩም ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ይነድ ከነበረው እሳት ውስጥ አንድ ፍም በመቈንጠጫ አወጣና ለብቻው ቁጭ አድርጐት ተቀመጠ። ለብዙ ደቂቃ በመካከላቸው ንግግር አልነበረም። ሁለቱም ፀጥ ብለው የሚነደውን እሳትና ፓስተሩ በመቈንጠጫ አውጥቶ ለብቻ ያደረገውን ፍም ይመለከቱ ነበር። ያ ለብቻ የነበረው ፍም እየከሰመና አመድ እየለበሰ መጣ። ፓስተሩ ቃል ሳይናገር ሰውየው መልእክቱ ስለገባው ተጸጽቶ ተነሳና ፓስተሩን፥ «ፓስተር! በስሕተቴ ተጸጽቻለሁ፤ ለብቻዬ ክርስቲያን ሆኜ መኖር እንደማልችል ተገንዝቤአለሁ። ከዛሬ ጀምሮ ወደ ስብሰባዎች እየመጣሁ ከቅዱሳን ጋር ኅብረት አደርጋለሁ» አለ። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ለማንኛውም ክርስቲያን አስፈላጊ ነገር ነው።



## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሃላፊነት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት ለምን እንደሆነ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆኑ መኖርም በጣም ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን አይተናል። አንዳንድ ቲኬቶች ሲዘጋጁ የሚጻፍባቸው አንድ ማስጠንቀቂያ አለ :- «ተለይቶ ከተገነጠለ ዋጋ የለውም» (not good if detached) የሚል። አማኝም ከሌሎች አማኞች ኅብረት ከተለየና ተገልሎ ከኖረ ጥሩ የክርስትና ሕይወት ሊኖረው አይችልም። ጠላት አማኝን ከኅብረት አውጥቶ ለብቻው እንዲሆን የሚገፋፋው ይህንን ስለሚያውቅና ተለይቶ የሚያገኘውን አፍኖ መግደል ቀላል ስለሚሆንለት ነው።

ስለዚህ ዳግም የተወለደና የዳነ ማንም አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ የሚችልበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፈልጎ በፈቃዱ አባል መሆን አለበት። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ሁለት ክፍሎችን ያካትታል። 1ኛ) መንፈሳዊ ጥቅምና በረከት አለው። «የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት» በሚለው ርእስ ሥር ስለ ጥቅሞቹ ከሞላ ጐደል ተገልጿል። 2ኛ) በአማኙ ላይ የሚጥለው ትልቅ ሃላፊነት አለ። ከዚህ በታች የምናተኩረው፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል በሚኖሩት ሃላፊነቶች ላይ ነው።

### 1. በፕሮግራሞች ላይ በታማኝነት መገኘት

አንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ከአንድ ሱቅ ደጃፍ ቆመው በሩ እስኪከፈት ሲጠብቁ ሳለ፥ አንደኛው ራሱን ያስተዋውቅና፥ «ወንድሜ ሆይ፥ ጌታን እንደ ግል መድሃኒትህ አድርገህ ተቀብለሃል?» ሲል ይጠይቀዋል። ሁለተኛውም «አዎን! ክርስቲያን ነኝ» ብሎ ይመልስለታል። ከዚያ ሁለቱም ተራ በተራ ስለ ክርስትና ሕይወት በሰፊው መጫወት ይጀምራሉ። በመካከሉ የመጀመሪያው ሰው «የት ቤተ ክርስቲያን ነው የምትሄደው?» ሲል ይጠይቀዋል። ሁለተኛውም ሰው «አሁን ላለፉት አሥር ወራት ቤተ ክርስቲያን ሄጄ አላውቅም፤ አባልነቴ ግን በ.... ቤተ ክርስቲያን ነው» ይለዋል። የመጀመሪያውም ሰው ተገርሞ «ወንድሜ ሆይ፥ የጌታ ሥራ ሃላፊነት በአንተ ላይ ብቻ ቢደገፍ ኖሮ፥ በእነዚህ ቤተ ክርስቲያን ባልሄድክባቸው ወራት ምን ይሆን ነበር?» ሲል ጠየቀው። ሁለተኛው ሰው ለዚህ ፡ ..ጋቢ መልስ መስጠት ስላልቻለ ዝም አለ።

ክርስቲያን የምንመጣው ለራሳችን ጥቅምና መባረክ ብቻ ይመስለናል። ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት ነው፤ እግዚአብሔርን መባረክ ነው (መዝ. 134፥2)።

መ) ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንመጣው መንፈሳዊ ምግብ ለመመገብ ነው።

ፈረንጆች፥ «የምትበላውን ነህ» (You are what you eat) ይላሉ። ይህንን አባባል ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ማየትና ከመንፈሳዊው ሕይወት ጋር ማነፃፀር ይቻላል። ይህንን አባባል የጠቀስኩበት ምክንያት ሰው ምግብ ካልበላ :- ክሳት፥ በሽታ፥ ኍስቍልናና ሞት ብቻ እንደሚጠብቀው፥ ያለ መንፈሳዊ መብል ውጤቱ ተመሳሳይ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ መንፈሳዊ ምግብ የምንመገብበት ቦታ ናት። ፕሮግራሞቿና አገልጋዮቿ ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መሠራትና መታነጽ የተሰጡ ናቸው። ነገር ግን ካልመጣን እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀልንን ድግስ መመገብ አንችልም።

ቤተ ክርስቲያን የማይመጣ አማኝና ቤንዚን የማይቀዳ ሹፌር አንድ ናቸው፤ የቱንም ያህል ቢበሩና ቢከንፉ መቆማቸው የማይቀር ነው። በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ መገኘትን ሊተካ የሚችል ምንም ነገር የለም። በቢ ታችን ቀርተን ክርስቲያናዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ብንመለከት እንኳን ቤተ ክርስቲያንን ሊተካ አይችልም። በእውነት ዳግም የተወለደ ሰው ከሁሉ ነገር ይልቅ የሚጓጓው ለኅብረት፥ ለቃሉ፥ ለጸሎትና በአንድነት እንጀራን ለመቍረስ ነው (ሐ.ሥ. 2፥42)። ይህ ፍላጐት በውስጣችን ከሌለ ዳግም አልተወለድን ይሆናል። ዳግም የተወለደ ሰው መንፈሳዊ መብል ስለሚርበውና ስለሚጠማው ለመመገብ ወደ ቤተ ክርስቲያን አዘውትሮ ይሄዳል።

ሠ) የጌታ ልዩ ጕብኝት በቤተ ክርስቲያን ስለሚመጣ ነው።

ጌታ በገባው ቃል ምክንያት (ማቴ. 18፥20)፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚደረጉት የአምልኮ፥ የጸሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችና ሌሎችም ስብሰባዎች ኢየሱስን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። ሁሉ ነገር የሚደረገው ለእርሱና ለክብሩ ነው። ስለዚህ ምንም እንኳ ጌታ በመንፈሱ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ቢኖርም፥ ልጆቹ በስሙ በሚሰበሰቡበት ጊዜ የህልውናው ልዩ መገኘት (special visitation of the Lord's presence) በመካከላቸው እንዲኖር ያደርጋል። የአንተ አለመገኘት፥ እንዲመለክ በመካከል የሚገኘውን ጌታ እንዳይደሰት ያደርገዋል። ለአለመገኘትህ በቂ ምክንያት ከሌለህ ቸልተኝነትህን ስለሚያውቀው እርሱን አለማክበር ይሆናል። ይዞት የመጣው ልዩ በረከትም ይቀርብሃል። መገኘትህ ግን ጌታን፥ መጋቢህን፥ ወንድሞችህንና



እኅቶችህን ሁሉ ያስደስታል። ምሳሌነትም ይኖርሃል፤ አንተን ያየ የማያምን ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሳባል። ከቤተ ክርስቲያን ቀርተህ አብረህ የምትውለው ከማያምኑ ጋር ከሆነም ለጌታ ያለህን አለመሰጠት ስለሚያስተውሉ በምስክርነትህ ይንቁሃል።

ረ) የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አይተገኍሉም።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የደነገጋቸው ሥርዓቶች፥ በተለይም የሞቱ መታሰቢያ የሆነው የጌታ እራት ሥርዓት የሚፈጸመው አባላት ወደ ስብሰባዎች ሲመጡ ነው። ካልመጣህና ካልተካፈልክ የሥርዓቱን አስፈላጊነት ታቃልላለህ።

ሰ) ከአማኞች ጋር ኅብረት ይኖራል

እግዚአብሔር በአንተና በእርሱ መካከል ስላለው ብቻ ሳይሆን፥ ከሌሎች ጋር ስላለህ ግንኙነትም ይገደዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን ከምንመጣበት ምክንያቶች አንዱ ከወንድሞችና ከእኅቶች ጋር ኅብረት ለማድረግና ለመቀራረብ ነው።

ሸ) የጌታን ቀን ማክበር ነው።

አራተኛው ሕግ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው ...» ይላል (ዘጸ. 20፥8-11)። በብሉይ የተሰጡ የእግዚአብሔር ሕጎች በአዲስ ኪዳን አልተለወጡም። ሰንበትን የሚመለከተው ትእዛዝ ግን በአዲስ ኪዳን፥ ክርስቶስ በሰጠው መመሪያ ተሻሽሎአል። ቤተ ክርስቲያንም የተሰበሰበችው ጌታ ከሞት በተነሣበት በእሁድ እንጂ በቅዳሜ አልነበረም። ስለዚህ፥ ለእግዚአብሔር ቀን የመለየቱና ከእርሱ ጋር ተገናኝተን በአምልኮት የምናሳልፍበት ጊዜ አስፈላጊነት መመሪያው አሁንም አለ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ይህንን መመሪያ እናከብራለን።

ከላይ እንደተመለከትነው የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን በታማኝነት መካፈል አንዱ ሃላፊነት ነው። ይህ የአባልነት ግዴታ አባል በሆንበት ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ባለ ጊዜ ወደ ሌላ የስብሰባ ቦታ መዞርንም ይከለክላል። የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ካለ ከዚያ ሊያስቀረን የሚችለው በቂ የሆነ አስገዳጅ ምክንያት እንጂ ወደ ሌላ ስብሰባ መሄድ አይደለም። የራሱ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ በሌለበት ጊዜ ግን አንድ ሰው ወደፈለገበት ቦታ መሄድ ይችላል።

ያበጀውን እግዚአብሔርን መቃወም እንደሆነ የማያስተውሉ አሉ (ሮሜ 13፥2)።

በሚያደርገው ሁሉ ስሕተት የማይገኝበት እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነው ሥልጣኑ ሥር ሆነው የእርሱን ዓላማና ፈቃድ እንዲፈጽሙ ሦስት ተቋማትን (Institutions) በምድር ላይ መሥርቷል። እነዚህም፤

ሀ) ቤተሰብ

ለ) መንግሥት እና

ሐ) ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

እግዚአብሔር በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የእርሱ አሳብና ዓላማ ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲፈጸም ሥራውን የሚሠሩ ግለሰቦችን መርጦ በመሾም ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሁሉ እርሱ ለአበጀው ሥልጣንና ሥርዓት እንዲታዘዙ የጠየቀው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይህንን አሳብ በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሰፊ መመሪያ አለ።

## ሀ) ቤተሰብ

እግዚአብሔር በምድር ላይ በመጀመሪያ የመሠረተው ተቋም ቤተሰብ ነው (ዘፍ. 1፥27-28፤ 2፥18-25፤ 9፥1፤ መዝ. 127፥3-5)። ቤተሰብ ስንል ስለ ባል፥ ሚስት፥ እና ልጆች መናገራችን ነው።

ቤተሰብ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር የተመሠረተ ተቋም ከመሆኑም በላይ የሁሉ ነገር መሠረት ነው። ቤተሰብ ከተናወጠ ሁሉ ነገር ይናወጣል። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ እንደተከሰተው ታላላቅ ሥልጣኔዎች የተናወጡትና የወደቁት የኅብረተሰብ ምሰሶ የሆነው ቤተሰብ ሲናወጥ ነው። ቤተሰብ እንዳይናወጥ እግዚአብሔር በቤተሰብ መካከል ሥልጣንን ከማበጀቱም በላይ በቃሉ ውስጥ ስለ ቤተሰብ አስተዳደርና አመራር ሰፊ መመሪያ ሰጥቷል።

እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ለቤተሰብ በሰጠው መመሪያ መሠረት ወንድ (ባል) የሴት (የሚስት) ራስ ነው (1ቆሮ. 1፥3፥8-12፤ ኤፌ. 5፥22-24)። ወንድ፥ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቱን እንዲወድ፥ ቤተሰቡን ሳያስቈጣና ሳያስመርር በመልካም እንዲያስተዳድር ታዟል። ሚስትም ባሏን እንድታከብርና እንድትታዘዝ (ኤፌ. 5፥22-23፤ 1ጴጥ. 3፥1-7) ታዛለች። ልጆችም ዕድሜያቸው እንዲረዝም ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ (ዘጸ. 20፥12፤ ኤፌ. 6፥1-4) ታዘዋል። ይህ ሥርዓት በተሻረበት ቤተሰብ ሁሉ ትልቅ ነውጥ አለ።



የዚህ ትምህርት ዓላማ ስለ ቤተሰብ ለማስተማር ሳይሆን እግዚአብሔር በመሠረተው በዚህ ተቋም ውስጥ ሥልጣንና ሥርዓት እንደተመሠረተ ለመግለጽ ነው። ስለዚህ ከዚህ በላይ በዚህ ርእስ ላይ አንቈይም።

## ለ. መንግሥት

እግዚአብሔር በምድር ላይ ቤተሰብን የመሠረተው በአንድ ቤተሰብ (በአዳምና ሔዋን) ብቻ ነው። ነገር ግን የአዳምና የሔዋን ልጆች የራሳቸውን ቤተሰብ ሲመሠርቱና ሲወልዱ፥ እንደገናም እነዚያ ልጆች አድገው ሲያገቡና ሲወልዱ የሰው ልጅ በምድር ላይ እየበዛ መጣ። በዚህ ጊዜ እነዚህ ሁሉ ብዙ ቤተሰቦች በአንድ ላይ አብረው በሰላም እንዲኖሩ እግዚአብሔር ሁለተኛውን ተቋም መንግሥትን በምድር ላይ መመሥረት ነበረበት።

በዘፍጥረት 9፥1-6 ላይ የምናነበው የዚህን የሁለተኛውን ተቋም መቋቋም ነው። እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን ሰው መግደል የእርሱን አሳብ መጣስ እንደሆነ ነገራቸው፤ በሰላም አብረው እንዲኖሩም መመሪያ ሰጣቸው። ኖኅ፥ ታራ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ሌሎቹ ሁሉ እያንዳንዳቸው ሰፊ ለሆነው ዘሮቻቸው ራስ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። የእነርሱ ወገን የሆነ ሁሉ ራስ የነበሩትን የእነዚህን ሰዎች ሥልጣን ያከብር፥ የሚሰጡትንም መመሪያ ይከተል ነበር።

በኋላም እግዚአብሔር ነገሥታትን፥ ካህናትን፥ ነቢያትን፥ ልዩ ልዩ መሪዎችን በመቀባትና በመሾም ሕዝቡን እንዲያስተዳድሩ ሥልጣን እንደሰጣቸው በብሉይ ኪዳን ውስጥ እናነባለን። ብሉይ ሆነ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሥልጣንን ማክበርና መታዘዝ እንደሚጠበቅባቸው ቍልጭ ያለ መመሪያ ይሰጣል (ምሳ. 8፥15-16፤ ሮሜ 13፥1-8፤ 1ጴጥ. 2፥13-18)።

## ሐ. ቤተ ክርስቲያን

እግዚአብሔር በምድር ላይ የመሠረታት ሦስተኛዋ ተቋም፥ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የገዛት ቤተ ክርስቲያን ናት (ማቴ. 18፥16-19)። የቤተ ክርስቲያን ራስና የበላይ ባለሥልጣን ክርስቶስ ነው (ኤፌ. 1፥22-23፤ ቈላ. 1፥18)። ቤተ ክርስቲያን ያላት አንድ ራስ ብቻ ነው። ስለዚህ ሌላ ሁለተኛ ራስ ሊኖራት ፈጽሞ አይችልም። ነገር ግን በክርስቶስ ሥልጣን ሥር ሆነው እንደ ቃሉ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስተዳድሩና እንዲመሩ እግዚአብሔር ግለሰቦችን መርጦ በመሾም ሥልጣንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አድርጓል (ሐ.ሥ. 20፥17፥28፤ ኤፌ. 4፥11፤

1ጢሞ. 3፥1-14)። ሥልጣንን አለማክበርና መጋፋት ሥልጣን ሰጭውን መጋፋትና አለማክበር ነው። ቤቱን እንዲያስተዳድሩ እግዚአብሔር ራሱ ሥልጣንና ሹመት የሰጣቸውን መሪዎች ሥልጣን እየናቁ ሳይታዘዙ እግዚአብሔርን አስደስታለሁ ብሎ ማሰብ ትልቅ ስሕተት ውስጥ ይጨምራል።

ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሃላፊነት ውስጥ አንዱ፥ የቤተ ክርስቲያንን መሪዎችና አገልጋዮች ሥልጣን ማክበርና መታዘዝ ነው። አንዳንድ አማኞች መሪዎቻቸውን መቀበልና ማክበር ይከብዳቸዋል። ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሎሌያዊ አገልግሎት ስለሆነ፥ መሪዎች ዝቅ ብሎ ከማገልገል በቀር ክብርን ከሰው የግድ መጠበቅ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን አማኞችን ክብር ለሚገባው ክብር እንድንሰጥ ያዝናል። ስለዚህ እረኛው እንደ እረኝነቱ፥ ሽማግሌው እንደ ሽማግሌነቱ፥ ዲያቆኑ እንደ ዲያቆንነቱ፥ የኳየር መሪው እንደ ኳየር መሪነቱ ሌሎቹም መሪዎች እንደዚሁ መከበር አለባቸው። «አወቅሁሽ ናቅሁሽ» እግዚአብሔርን ከማይፈራ ሰው እንጂ ከእውነተኛ ክርስቲያን የሚጠበቅ ባሕርይ አይደለም።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሚስት ካገባ በኋላ፥ የሚስቱን አባት «አንቱ» እንዳይላቸው ይንቃቸዋል፤ «አንተ» እንዳይላቸውም አፈረ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ሲገናኙ አንቱም አንተም እንዳይል እየተጨነቀ በቃላት ወዲህና ወዲህ ይላል። የሚስቱ አባት ነገሩ ስለገባቸው አንድ ቀን «ልጄ፥ ና እባክህ አጥር አስተጣጥረኝ» ሲሉ ይጠይቁታል። እርሱም ምንተፍረቱን «እሺ» ይላቸውና አብረው አጥር ማጠር ይጀምራሉ። አጥሩ የሚታጠረው ብዙ ስንጥር ባለው ፍልጥ በገመድ እየታሰረ ነበር። ከወዲያና ከወዲህ ቆመው ሲሠሩ ሰውየው ድንገት ሳያውቁ አስመስለው የልጁን ጣት ስንጥር ብቻ ከሆነው ፍልጥ ጋር በገመዱ ጥፍር አድርገው አሰሩት። ልጁም ስንጥሩ ስለወጋው ጣቴ ተይዟል ብሎ እንዳይነግራቸው አንቱ ወይም አንተ ማለት ስላልፈለገ ዝም ብሎ «አአአአ ጣቴ!» አለ። እርሳቸውም እንዳላወቀ ወደ ጣቱ ሳይመለከቱ «አይ የዛሬ ልጅ! ሥራ ሲሠሩ በርትቶ መሥራት እንጂ» አሉና ገመዱን የበለጠ በመሸምቀቅ አጠበቁት። ልጁም እንደገና «ላላ፥ ላላ፥ ላላ!» ሲል ጮኸ። እሳቸውም ነገሩ እንዳልገባቸው ሆነው «አይ የዛሬ ልጅ! ሥራ መሥራት ትተህ መዝፈን ጀመርክ?» አሉት። በመጨረሻም ልጁ ጭንቅ ሲበዛበት «አባቴ፥ እጄን በገመዱ ከፍልጡ ጋር ወጥረው ይዘውታል፤ እባክዎን ያላሉልኝ» ሲል ጮኸ። ሰውየውም «አይ ልጄ፥ እንደዚህ ቀድሞውኑ ቢለይልህ አይሻልም ነበር!» በማለት ገመዱን በማላላት እጁን አስለቀቁለት። ክብር ለሚገባው ክብር መንፈግ ኢክርስቲያናዊ ባሕርይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሚለው «እርስ



በእርሳችሁ ተከባበሩ» ነው። ለመከባበር የግድ ሥልጣን መኖር እንኳን የለበትም።

የሚከተሉት ጥቅሶች እግዚአብሔር በቤቱ ውስጥ ለሾማቸው መሪዎች ሥልጣን እንዴት መገዛትና መታዘዝ እንደሚገባን የሚያሳስቡ ናቸው። ማንኛውም አማኝ በቃሉ ከተሰጠው ትእዛዝ ነፃ ሊሆን የሚችልበት መንገድ የለም።

ሐ.ሥ. 20፥17:28፤ 1ቆሮ. 16፥15-18፤ 1ተሰ. 5፥12:13፤ 1ጢሞ. 5፥17፤ ቲቶ 2፥15፤ ዕብ. 13፥7:17:24፤ 1ጴጥ. 5፥1-2።

«በእስራኤል ውስጥ መሪዎች ስለመሩ፥ ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ስለሰጡ እግዚአብሔርን አመስግኑ» (መሳ. 5፥2)።

«የቀባኋቸውን አትዳስሱ፥ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ብሎ፥ ሰው ክፉ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፤ ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ» (1ዜና. 16፥22)።

በ1ዜና 16 ላይ ያየነውን ጥቅስ እግዚአብሔር የተናገረው ሕዝቡ (እስራኤላውያን) በነበሩበት አካባቢ ይኖሩ ለነበሩት አሕዛብ ነበር። ነገር ግን ራሳቸው የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተባሉት፥ እግዚአብሔር በሾመላቸውና በቀባላቸው መሪዎች ላይ ስለተነሡና ሥልጣናቸውን ከመጋፋት አልፈው ጉዳት ስላደረሱባቸው እግዚአብሔር ለጠላት አሳልፎ እንደሰጣቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን (ነህ. 9፥26-27)።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በልዩ ልዩ የግል ፍላጎት የተነሣ ሥልጣንን በመናቅና በመጋፋት ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣሉ ይታያሉ። የእግዚአብሔር ቃል «ለዋኖቻችሁ (መሪዎቻችሁ) ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው ይህንን በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ (ዕብ. 13፥17) ይላል። ከዚህ ጥቅስ የሚከተሉትን እውነቶች መመልከት እንችላለን።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል እግዚአብሔር ለሾማቸውና ሥልጣን ለሰጣቸው መሪዎች መገዛት ይገባዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር በቤቱ ውስጥ ለሾማቸው ቀርቶ ነፍስ ሁሉ ለበላይ ባለሥልጣናት እንዲገዛ ያዛል (ሮሜ 14፥1)። እንደዚሁም እያንዳንዳችን ለሌላው በክርስቶስ ፍርሃት እንድንገዛ ያዝናል (ኤፌ. 5፥21)። ለዚህ ነው በአዲስ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር አሳብና ዓላማ በመካከላችን እንዲፈጸም «እርስ በርሳችሁ ...» የሚሉ ብዙ ትእዛዞች የተሰጡን።

አንዳንድ አማኞች፥ እግዚአብሔር ለሥልጣን ተገዙ ያለው ለምንወዳቸውና በእኛ ግምት «መልካም ናቸው» ለምንላቸው መሪዎች ብቻ እንደሆነ ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር ልጆችን «ወላጆቻችሁ ክርስቲያን ከሆኑና መልካም ከሆኑ ብቻ ታዘዙ» አላለም። ለመንግሥት የምንታዘዘውና የምንገዛው እኛን የሚስማማ መንግሥት ሲሆን ብቻ አይደለም። በየመሥሪያ ቤታችን ላሉት አለቆች ሥልጣን የምናሳየው መገዛት መልካም ሲሆኑ ብቻ አይደለም። ሰዎች ላልወደዱትና ላልፈለጉት ሰው ሥልጣን አለመገዛት የተፈቀደ ቢሆን ኖሮ ከቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በሁሉም ዐይነት ተቋማት ውስጥ ሥርዓተ አልበኝነት (Anarchy) እና አመፅ ይነግሥ ነበር።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ባለሥልጣናት ሲያዟቸው እምቢ አሻፈረኝ ያሉበት ጊዜ አለ (ሐ.ሥ. 4፥15-21)። እነርሱ ግን እምቢ ያሉት በኢየሱስ ስም አትናገሩ የሚለውን ትእዛዝ እንጂ ሥልጣንን በአጠቃላይ አይደለም። እነርሱ ሲያስሩአቸው ራሳቸውን ለእስር፤ ሲገርፏቸው ጀርባቸውን ለጅራፍ ያለ አንዳች ማቅማማት እንደሰጡ እንመለከታለን። አንድም ቦታ «ለምን ታሰርን? ለምን እንዲህና እንዲህ ሆነብን?» ብለው ሥልጣንን ሲጋፉ አንመለከትም። አንታዘዝም ያሉት በክርስቶስ ስም እንዳይሰብኩ በተጠየቁ ጊዜ ብቻ ነው።

ዛሬም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ከእግዚአብሔር ቃል በወጣ መንገድ እንደ ጂም ጆንስ ወደ ገደል ለሚመሯቸው መሪዎች ሥልጣን እንዲገዙ የሚያስገድዳቸው አንድም ጥቅስ የለም።

ልብ ብለን ብናስተውል «ተገዙ» የሚለው ቃል በመሠረቱ የምንገዛለት ሥልጣን የማንወደውና የማንፈልገው መሆኑን ያንፀባርቃል። የምንገዛው በቦታው ላለው ግለሰብ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ላስቀመጠው ሥልጣን ነው። በሥልጣን ላይ ካለው ሰው ጋር አለመጣጣም ሲያጋጥመንም፥ እግዚአብሔር ላስቀመጠው ሥልጣን ስንል የራሳችንን ስሜት ትተን ለሥልጣን መታዘዝና መገዛት ይኖርብናል። ስለዚህ መገዛት በእኛ ፍላጎትና ምርጫ ላይ አያተኩርም፤ ወደድንም ጠላንም እግዚአብሔር ለሰጠው ሥልጣን መታዘዝ ይጠበቅብናል።

ከላይ እንደጠቀስነው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሥልጣን በአግባቡ የማይጠቀሙ መሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን አማኞች ሊወስዱት የሚገባው እርምጃ ጥንቃቄ የሞላው መሆን አለበት። እግዚአብሔር ለቤቱ ስለሚጠነቀቅ እንዲህ ያሉትን መሪዎች እርሱ ራሱ በጊዜው ያስወግዳቸዋል። እግዚአብሔርን እንዳንቀድምና እንዳናሳዝነው ጥንቃቄ መውሰድ ተገቢያችን ነው።



በኮርያ ጦርነት ጊዜ ጥቂት የአሜሪካ ወታደሮች በአንዲት ከተማ በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። እነርሱም ምግብ እንዲያበስልላቸውና የቤት ሥራ እንዲሠራላቸው አንድ ትንሽ ኮሪያዊ ልጅ ቀጠሩ። ኮሪያዊው ልጅ በፊቱ ሁል ጊዜ ደስታና መልካም አመለካከት (Attitude) ይታይበታል። ነገር ግን ወታደሮቹ ተማክሩና በዚህ ልጅ ላይ አንዳንድ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች ማድረግ ጀመሩ። ልጁ ተኝቶ ጥዋት ሲነሣ ጫማው ከመሬት ጋር በሚስማር ተጣብቆ ያገኛል። ምንም ሳያጕረመርም ሚስማሩን ታግሎ ያወጣና የተለመደ ሥራውን ይቀጥላል። የሚሠራበትን ምድጃ እጀታውን በግራሶ ይለቀልቁበታል። እርሱ ግን ጨርቅ ፈልጐ ይጠራርግና ሥራውን ይሠራል። ውሃ በባልዲ ከመግቢያው በር ላይ ያደርጉና ልጁ በር ሲከፍት የባልዲው ውሃ ይከለበሰበታል፤ ልብሱም ይበሰብሳል። አሁንም ምንም ሳያጕረመርም ሥራውን ይሠራል። ወታደሮቹ ልጁ ፍጹም ታዛዥና መልካም መሆኑን ስላዩ አንድ ቀን ጠዋት ይጠሩትና «ሁለተኛ የምናደርግብህ ነገር የለም» ይሉታል። ኮሪያዊውም ልጅ «ይህ ማለት ከእንግዲህ ጫማ ከመሬት ማጣበቅ የለም ማለት ነው? በምድጃው እጀታ ሁለተኛ ግራሶ መለቅለቅ የለም ማለት ነው? ውሃ በላዩ ላይ ማፍሰስ የለም ማለት ነው?» ሲል ጠየቀ። እነርሱም «አዎ!» ሲሉ መለሱለት። እርሱም «በቃ እኔ ደግሞ ከእንግዲህ በምሠራላችሁ ሾርባ ውስጥ ምራቄን ሁለተኛ አልተፋም» አላቸው።

ብዙ ጊዜ ለሌላው የተገዛን የሚመስለን እንደዚህ ኮሪያዊ ልጅ በማታለል ከሆነ ትክክለኛ መገዛትና መታዘዝ አይደለም። መገዛት፥ በምላሹ የምናደርገው ምንም ዐይነት ተንኰል ሳይኖር ነው። ስሜታችን በተጐዳበት ጊዜ እንኳ ለጌታ ስንል ትክክለኛውን ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መጋቢው ከእግዚአብሔር ቃል ለሚሰጠው ትምህርትና መመሪያ መታዘዝ አለበት።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል፥ ፓስተሩ የሚያስተምረውን ትምህርትና የሚሰጠውን ምክርና አቅጣጫ በደስታ ተቀብሎ በተግባር ላይ ማዋል ይገባዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ፥ «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» ይላል (13፥7)። ዋኖቻችን እንደ ቃሉ ትክክለኛውን አቅጣጫ ሲያሳዩን አንታዘዝም ባዮች መሆን የለብንም።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል እረኛውና ሌሎቹ መሪዎች በሥራቸው እንዲያዝኑ ከማድረግ መጠንቀቅ ይገባዋል።

አሁንም ሐዋርያው ጳውሎስ ለዕብራውያን መልእክት ተቀባዮች «ለዋናቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ» ይላል (13፥17)።

እረኞች ደስ የሚላቸው፥ በጌታ ስንበረታና በመንፈሳዊ ሕይወታችን አድገን ስንጠነክር ነው። ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች «ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና» ይላል (1ኛ ተሰ. 2፥19-20)። አገልጋይ ጌታ ሲመጣ ደስ የሚለው፥ የሚያገለግላቸው ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አድገውና ፍሬያማ ሆነው የድካሙን ዋጋ (ሽልማቱን) ከእርሱ እጅ ስለሚቀበል ነው። ይህ ሲጐድል እረኞቻችንን እናሳዝናለን፤ ተስፋም እናስቈርጣለን።

እረኞቻችን :-

- ለእግዚአብሔር ቃል ስንታዘዝ ሲያዩ ደስ ይላቸዋል። (1ዮሐ. 3-4)፤ ለቃሉ ግዴለሽ ስንሆን ያዝናሉ።
- የመንፈስን አንድነት ስንጠብቅ እናስደስታቸዋለን፤ ስናፈርስ ግን ያሳዝናቸዋል።
- እንደምንጸልይላቸው፥ እንደምናስባቸው ሲያውቁ ደስ ይላቸዋል። ያለ መረጃ ስሞተኞችና ሐሜተኞች የሚያወሩትን ሁሉ ስንሰማ ያሳዝናቸዋል (1ጢሞ. 5፥19)።
- አለማደጋችን፥ የእግዚአብሔርን ቤት የመጠበቅ ሃላፊነታችንን መርሳታችን ያሳዝናቸዋል። ለዚህ ነው ሥራቸውን በኃዘን እንዳያደርጉ አባላት ሁሉ መጠንቀቅ የሚገባቸው።

ሥልጣንን መቃወም ወይም በሥልጣን ላይ ማመፅ እግዚአብሔርን መቃወምና በእርሱ ላይ ማመፅ ነው። ይህ ፈጽሞ ከክርስቶስ መንፈስ አይመነጭም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን አመጽ የሰይጣን ኃጢአት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አመፅ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

«አመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ (Witchcraft) እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው» ይላል (1ሳሙ. 15፥23)።

ይህ ቃል የሚያስፈራና የሚያንቀጠቅጥ ነው። ምክንያቱም አመፀኝነትና ምዋርተኝነት አንድ እንደሆኑ ይናገራል። ቃሉ በመጀመሪያ



የተነገረው የእግዚአብሔርን ቃል (ትእዛዝ) ለናቀውና ትእዛዙን ጥሶ ለአመፀው ለሳዖል ነው።

ምዋርተኝነት፥ መንፈሳዊነትን በመሰለ መንገድ እግዚአብሔር የገለጸውን አሳብ ተቃውሞ የራስን አሳብና ፍላጐት ለማሟላት መነሣትና የሌሎችንም አእምሮ ተቈጣጥሮ ወደ ክፉ መግፋት ነው። በዚህ መንፈስ መቀጠል ለጣዖት አምልኮና ለበርካታ ክፉ ነገሮች ክፍት ያደርጋል። አንድ ሰው በዚህ በቃየል መንገድ ሲሄድ፥ በስሕተት ጎዳና እየሄደ መሆኑ የሚታወቅበት ብዙ ምልክቶች አሉ። ነገር ግን በዚህ ትምህርት ልንጠቅሳቸውና ልንወያይባቸው አንችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ ቆሬ የሙሴንና የአሮንን ሥልጣን በመቃወሙ ምን እንደደረሰበት ያሳየናል (ዘኁ. 16፥1-35፤ ይሁዳ 11)። ሥልጣንን ማክበር የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና መታዘዝ ነው።

በተጨማሪም ሥልጣን ማክበርና መታዘዝ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ባሕርይ ነው። ሥልጣንን ማክበርና መገዛት በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤት እንደሆነ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለአበጀው ሥልጣን ሁሉ መገዛት እንደሚገባ ባስተማረበት ክፍል፥ በኤፌሶን 5፥18-24 ባለው ክፍል ግልጽ ያደርገዋል። በዚህ ክፍል ላይ እያንዳንዱ አማኝ ለሌላው እንዲገዛ ይናገራል (ቊ. 21)። እንዲሁም ወንድ የሴት ራስ እንደሆነና ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ ይናገራል (ቊ. 22-24)። ቤተ ክርስቲያን (አማኞች) ለክርስቶስ እንዲገዙ ይላል (ቊ. 24)። ነገር ግን ይህን ሁሉ ቃል የተናገረው ቊጥር 18 እና 19 ላይ በመንፈስ ተሞሉ የሚለውን ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ነው። በመንፈስ መሞላት በቃሉ የታዘዘውን ለማድረግ ትክክለኛ አመለካከት (Attitude) እንዲኖር ያደርጋል።

«ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፥ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ» (1ተሰ. 5፥12-13)።

በዚህ ጥቅስ መሠረት እረኞቻችንን መቅረብና ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። እረኞቻችንን ልናውቃቸው፥ ልንቀርባቸው፥ ልናፈቅርና ልናከብራቸውም የሚገባው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

ሀ) ለአገልግሎቱ ቢሮ (Office) ስንል (ቊጥር 13)፤

ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 4፥1 ላይ «እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቍጠረን» ይላል። የእረኝነት አገልግሎት የተከበረ አገልግሎት ነው። የእረኛ አገልግሎት

ሐዋርያው ጳውሎስ «አንድነትን ጠብቁ» በማለት ፈንታ «የመንፈስን አንድነት ጠብቁ» ያለበት ምክንያት፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአማኞች መካከል አንድነትን የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ነው። አንድነትን መስጠት የእርሱ ሥራ ነው።

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበትና በሚድንበት ጊዜ ወዲያው መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሰው አዲስ አድርጎ ይለውጠውና ወደ ክርስቶስ አካል አባልነት ያጠምቀዋል። ስለዚህ ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ :-

> «አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል» ይላል (1ቆሮ. 12፥13)።

ሐዋርያው ጳውሎስ «አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ...» ማለቱ፥ በክርስቶስ አምነን የዳንነው ሁሉ የመጣነው ከልዩ ልዩ ዐይነት ዘር ከመሆኑም በላይ፥ ወደ ክርስቶስ ስንመጣ አያሌ ልዩነቶች በመካከላችን እንደነበሩ ሲገልጽ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አምነን የዳንነውን ሁሉ የአንዱ የክርስቶስ አካል እንድንሆን አብቅቶናል። ሰውነት ብዙ ልዩ ልዩ ብልቶች ቢኖሩትም በአንድ ራስ እየታዘዘ አንዱን አካል እንደሚያገለግል፥ አማኞች ልዩ ልዩ ብንሆንም፥ የክርስቶስ አካል ብልቶች ስለሆንን አንድነት አለን። ወደ አካሉ በማጥመቅ አንድነቱን የፈጠረው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን አንድነት «የመንፈስ አንድነት» ሲል ይጠራዋል።

ውኃና ዘይት መዋሃድ አይችሉም። ውኃና ዘይት መዋሃድ የሚችሉት ሁለቱን የሚያዋህድ ሦስተኛ ነገር ሲኖር ብቻ ነው። ማዮኒዝን (Mayonnaise) እንደ ምሳሌ ብንወስድ ማዮኒዝ የሚሠራው ከውኃ፥ ከዘይትና ከሶያቢን (Soybean) ነው። ውኃና ዘይቱን በማዋሃድ አንድ የሚያደርጋቸውና ወደ ማዮኒዝነት የሚለውጣቸው ሶያቢን የተባለ የጥራጥሬ ዘር ዱቄት ነው። ሶያቢን ውኃና ዘይትን አዋህዶ ማዮኒዝ የተሰኘ አዲስ ነገር እንዳስገኘ፥ መንፈስ ቅዱስም የማይዋሃዱትንና የማይደባለቁትን ልዩነት ያላቸውን ሰዎች ወስዶ በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድ ያደርጋቸዋል።

አንድነት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስለሆነ አንድነትን አለመጠበቅ ወይም መለያየትንና መከፋፈልን መዝራት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መቃወምና ማበላሸት ነው። ማንም ይህንን እያወቀ በዚህ ጉዳይ ላይ በቃሉ የተጠየቀውን ጥንቃቄ ካላደረገ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናል። በአማኞች



መካከል የሚገኝ አንድነት፥ አማኞች በግል ሆነ በኅብረት ደረጃ ለሚቀበሉት በረከት ሁሉ ዋና ቍልፍ ነው። አገልግሎትም ስኬት የሚኖረው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዳይበላሽ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ሲያደርጉ ነው።

በአንደበቱ ሆነ በአመለካከቱ (Attitiude) አንድነትን የሚያናጋ ተግባር የሚፈጽም ሰው በረከትን ለመቀበል የሚያደርገው ጸሎት እንኳን አይሰማለትም። መንፈስ ቅዱስ ከሰዎች ጋር በሰላም መኖር ባቃተውና ለቤተ ክርስቲያን ውጋት በሚሆን ሰው ደስ አይሰኝም። ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ከሚስቶቻቸው ጋር ስምምነት የሌላቸውንና ሚስቶቻቸውን የማያከብሩትን ባሎች፥ «እንዲሁ እናንተ ባሎች ሆይ! ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ። ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው» ይላቸዋል (1ጴጥ. 5፥7)። ጴጥሮስ ይህንን ምክር የሰጠው ባሎች ሚስቶቻቸውን ሳያከብሩ እያሳዘኑአቸው ለጸሎት ቢንበረከኩ የጸሎታቸው መልስ እንደሚከለከል ለማስጠንቀቅ ነው። በባልና በሚስት መካከል ያለውን አንድነት ያልጠበቀ ሰው ለጸሎቱ መልስ የማያገኝ ከሆነ፥ በክርስቶስ አካል ብልቶች መካከል ያለውን አንድነት ለመጠበቅ ጥንቃቄ የማያደርግም ሰው እግዚአብሔር ስለማይደሰትበት ለጸሎቱ መልስ መጠበቅ የለበትም።

«አንድነት» ማለት «ተመሳሳይነት» ማለት አይደለም። እኛ አማኞች በመልክ፥ በቁመት፥ በዘር፥ በስጦታዎቻችንና በችሎታችን ልዩ ልዩ ነን። ልዩ ልዩ መሆናችን የብርታታችን እንጂ የድካማችን ምክንያት አይደለም። እንዲያውም «አንድነት» የሚለው ቃል ትርጉም የሚኖረው ልዩ ልዩ የሚያደርጉን ነገሮች በመኖራቸው ነው። ሁላችንም አንድ ዐይነት ብንሆን አንድነት የሚለው ቃል ምንም ትርጉም የለውም። አንድነት የሚያስፈልገው ለተለያዩ ነገሮች ነው።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች መካከል ሊኖር ለሚገባው አንድነት ጥሩ ምሳሌና መሠረት የሚሆነው የሥላሴ አንድነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጸለየው «ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ (ሥላሴ) አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው» ሲል ነው (ዮሐ. 17፥11)። አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም የየራሳቸው ህልውና Personality) አላቸው። ነገር ግን በአሳብ፥ በፈቃድ፥ በሥራ ፈጽሞ አይለያዩም። ስለ ሥላሴ አንድነት ለማስረዳት ሰፊ ጊዜ ከመውሰዱም በላይ ከርእሳችን ውጭ ስለሆነ እዚያ ውስጥ አንገባም። ሥላሴን በዚህ ስፍራ መጥቀስ ያስፈለገው በአካል ሦስት ቢሆኑም «አንድ አምላክ» (አሀዱ

አምላክ) ብለን እንደምናምን ለማስታወስ ነው። የሥላሴ አንድነት ልንደርስበት ለምንመኘው አንድነት ምሳሌ ነው።

**መንፈስ ቅዱስ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ይህንን የመንፈስ አንድነት መጠበቅ የሁላችንም ከፍተኛ ሃላፊነት ሊሆን ይገባል።**

## ሀ. የአንድነት መሠረት

በኤፌሶን 4፥1-6 ባለው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈው «የመንፈስን አንድነት ጠብቁ» ሲል ብቻ አይደለም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ለምን አንድነትን መጠበቅ እንደሚገባውና ይህንን አንድነት በምን መሠረት ላይ መመሥረት እንዳለበት ጭምር በዝርዝር አስረድቷል። ቊጥር 4 እና 6 ላይ እንዲህ ጽፏል፤

> «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።»

ከላይ የጠቀስነው ጥቅስ የክርስቶስን አካል (ቤተ ክርስቲያንን) አንድ እንድትሆን የሚያደርጓት ሰባት ምክንያቶች እንዳሉና እነርሱም ለአንድነታችን መሠረት እንደሆኑ ይዘረዝራል። ሰባት የፍጹምነት ቊጥር ነው።

(1) አንድ አካል፤ ከዚህ በፊት ሐዋርያው ጳውሎስ አካል የሚለውን ቃል ለዓለም አቀፏና ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሁለቱም እንደተጠቀመባቸው እናውቃለን። አንድነት መኖር ያለበት፥ ቤተ ክርስቲያን ያላት አንድ አካልና አንድ ራስ ብቻ በመሆኑ፥ የአካሉ ብልቶች ልዩ ልዩ ቢሆኑም በክርስቶስ አንድ በመሆናቸው ነው።

(2) አንድ መንፈስ፤ አንድ ብቻ ለሆነው አካል ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ አንድ ነው። ሁላችንም የጠጣነው ይህንን አንዱን መንፈስ ነው (1ቆሮ. 12፥13)።

(3) አንድ ተስፋ፤ የአማኞች ሁሉ ተስፋ አንድ ነው።

(4) አንድ ጌታ፤ እያንዳንዳችን የተለያየ ጌቶች የሉንም፤ የሁላችንም ጌታ አንድ ነው።

(5) አንድ እምነት፤ ሁላችንም የዳንነው በአንድ ዐይነት የሚያድን እምነት ነው።

(6) አንድ ጥምቀት፤ ሁላችንም በአንዲት ጥምቀት ተጠምቀናል።

(7) አንድ አምላክ፤ ከሁሉ በላይ የሆነ፥ በሁሉም የሚኖርና የሚሠራ፤ ለሁላችንም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለን።



እነዚህ ነገሮች ሁሉ አንድ እንድንሆን አድርገውናል። አንድነቱ ተሰጥቷል ነገር ግን ይህንን አንድነት እንደ ዓይን ብሌን መጠበቁ የእያንዳንዱ አማኝ ሃላፊነት ነው።

## ለ. አንድነትን ለመጠበቅ የሚቻልበት መንገድ

በቊጥር 2 እና 3 ላይ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል የተሰጠውን የመንፈስ አንድነት መጠበቅ ስለሚችልበት መንገድ ይገልጻል።

> «በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤ በሰላም ማሠሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ»

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ አንድነት ከውስጥ ሕይወት የሚወጣ አመለካከት ነው። ከላይ ከተመለከትነው ጥቅስ እንደምንረዳው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት በመካከላቸው ያለውን አንድነት ለመጠበቅ የሚችሉባቸው ሰባት የውስጥ አመለካከቶች አሉ። እነርሱም፤

1) ትሕትና፤ የትዕቢት ተቃራኒ ነው። ትዕቢት እግዚአብሔር የሚጠላው ኃጢአት ነው። ትዕቢት የብዙ ኃጢአቶችም ወላጅ ነው። ንቀትን፥ አለመከባበርን፥ መንፈሳዊ ዕውርነትን ያመጣል። ለአንድነት መጥፎ ጠንቅ ነው። ትሑት ሰው ግን ከሌሎች የሚያጋጭና የሚያጣላ ነገር የለውም። ሰይጣን አማኞችን በትዕቢት ፈተና እንዲወድቁ የሚፈልገው ውጤቱን ስለሚያውቅ ነው። ትዕቢት ካለ አንድነትን ለማጥፋትና ለመከፋፈል እንደሚያመቸው ያውቃል። ትሕትና ግን ለአንድነት መድኃኒት ነው።

2) የዋህነት፤ ደካማነት ማለት አይደለም። ሙሴና ኢየሱስ የዋህ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ነገር ግን ሙሴ ሰዎች ጥጃ ሠርተው ሲሰግዱለት ሲያይ፥ ኢየሱስም ቤተ መቅደሱ የንግድ ሥፍራ ሆኖ ሲያይ ሁለቱም ተቈጥተዋል፤ ለእውነትም ቆመዋል። የዋህነት ለሌሎች የሚኰሰኩስና የሚቈጠቁጥ ከመሆን ስለሚጠብቅ ለአንድነት ጠቃሚ አመለካከት ነው።

3) ትዕግሥት፤ በወንድማማች መካከል ያለውን አንድነት ለመጠበቅ ጠቃሚ መሆኑ ከማንም ሰው የማይሰወር ሐቅ ነው።

4) መሸካከም፤ በትዕግሥት መሸካከም አንድነትን ለመጠበቅ አስፈላጊ ነገር ነው።

5) ፍቅር፤ ፍቅር ለአንድነት ጠቃሚ መሆኑን ሁሉም ሰው የሚያውቀው ነው።

6) ትጋት፤ መልካም ነገርን ለማግኘት ትጋት ይጠይቃል። አንድነትንም ለመጠበቅ አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረው የራሱን ሕይወት እየመረመረ በትጋት ለአንድነት መሥራት ይገባዋል።

7) ሰላም፤ የመንፈስ አንድነትን ለመጠበቅ የሁሉ ነገር ማሰሪያ ሆኖ የምናየው ሰላም ነው። ሰላም ማለት በሰውና በሰው መካከል ያለ ትክክለኛ ግንኙነት ነው። እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከሌሎቹ ወንድሞቹና እኅቶቹ ጋር በሰላም መኖር እስከመረጠ ድረስ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን የሚያናጋና ፍቅርን የሚያቀዘቅዝ ምንም ዐይነት ሁከትና ረብሻ አይፈጠርም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰላምን የሁሉ ነገር ማሰሪያ አድርጐ ነው የተጠቀመው። «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ጠብቁ» ይላል። በሌላ ቦታም ቢቻላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ሲል ይመክረናል። በሰላም መኖር ማለት አንድነትን ለመጠበቅ ያለብንን ኃላፊነት ተገንዝቦ በጥንቃቄ መመላለስ ነው። ባብዛኛው አንድነት የሚናጋው ግንኙነትን በተመለከተ በጥንቃቄ በማይመላለሱ፥ ያለባቸውን ኃላፊነት በማያስተውሉ ሰዎች ምክንያት ነው። ከሌሎች አማኞች ጋር በሰላም ለመኖር ጥንቃቄ በማያደርጉ አማኞች ምክንያት በበርካታ አብያተ ክርስቲያናት ፍቅር ጠፍቶ አንድነት ተናግቷል።

በአንዷት የማትጠነቀቅ ዶሮ መዘዝ በአንድ ገበሬ ግቢ ውስጥ ስለደረሰ ትልቅ ችግር የሚነገር ታሪክ አለ። አንዷት መንቀዥቀዥ የምትወድ ዶሮ ከሌሎች እንስሳት ጋር ሆና በአንድ ገበሬ ግቢ ትኖር ነበር። ችግሩ ይህች ዶሮ ለርምጃዋ የማትጠነቀቅ ነበረች። ከዕለታት አንድ ቀን ከወዲያ ወዲህ እየዞረች ስትጭር ድንገት በዳክዬ እግር ላይ ትቆማለች። ዳክዬዋ ምንም አልተጐዳችም፤ ነገር ግን በዶሮዪቱ በመናደዷ «ቆይ እኔ ደግሞ ሁለት እጥፍ ባልመልስልሽ!» ብላ ዶሮዋን ተከትላ ማሳደድ ጀመረች። ዳክዬ አሳቧ ያለው ዶሮዋ ላይ ስለነበር ሳታውቅ ፊት ለፊቷ የነበረውን እርኩም በክንፍዋ መታችው። እርኩሙም በበኩሉ ተናደደና «ቆይ ባላሳይሽ!» እያለ ከዳክዬ ኋላ መሮጥ ጀመረ። ድመት ተዝናንታ ፀሐይ ትሞቅ ነበር፤ እርኩሙ በመሮጥ ላይ እያለ ሳያውቅ በጥፍሩ ድመትን ይቧጥጣታል። ድመትም «መደፈሬስ!» ትልና እርኩምን በጥፍርዋ ለመሞነጫጨር በጥጃ እግር ሥር መሰስ ብዬ አልፋለሁ ስትል በእግርዋ ጥጃውን መታ ታደርጋለች። ጥጃ ምንም አልተጐዳም፤ ነገር ግን እርሱም በበኩሉ «እንዴት እደፈራለሁ!» ይልና ድመትን ሲያባርር ከፊት ለፊቱ ጐምለል እያለ ይመጣ የነበረው ውሻ ላይ ይወጣበታል። ውሻም በበኩሉ ተናደደና



ጥጃውን በጥርሱ ለመዘንጠል ሲሮጥ ላምን ያስደነብራታል። ላምም ተበሳጭታ ውሻውን በቀንዷ ለመውጋት ስትከተል ውሻ ዘሎ ፈረስ ሥር ይገባል። ላምም ውሻን በቀንዷ እወጋለሁ ብላ ኃይ ስትል ፈረስን ከኋላው ወግታ ታቈስላለች። ፈረስም በንዴት ብዙ ጊዜ ከዘለለ በኋላ ቁጭቱን ለመወጣት ወደ ላሟ ይሮጥ ጀመር። የዚህ ጊዜ ነበር ግቢው ሲተራመስ ገበሬው ከቤቱ ወጥቶ የሚሆነውን በመገረም የተመለከተው።

የገበሬው ቤት እንደዚህ ለምን ሊተራመስ ቻለ? የችግሩን መንሥኤ ስንመለከት ይህ ሁሉ ሁከትና መተራመስ የተፈጠረው ለአረማመዷ ጥንቃቄ በጐደላት አንዷት ዶሮ ምክንያት ነው። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ጥንቃቄ በማያደርጉ አንድ ወንድ ወይም ሴት የተነሣ ምእመኑ ሁሉ የሚታወክበት ችግር ሊፈጠር ይችላል።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ይህንን በማወቅ በመጀመሪያ ለራሳቸው ርምጃ በመጠንቀቅ፥ ቀጥሎ ሌሎችን ከስሕተት በማረም በቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን የመንፈስ አንድነት መጠበቅ ይገባቸዋል።

> «ወደ አንተ እንዳይቀርቡ በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጕሙአቸው ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና በቅሎ አትሁኑ» (መዝ. 32፥9)።

## ሐ. ለተጠሩበት ጥሪ ተገቢ የሆነ ርምጃ ማድረግ

አንድነትን መጠበቅ ለተጠራንበት ዓላማ ተገቢ የሆነውን ርምጃ ማድረግ ነው። «ርምጃ» የሚለው ቃል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መመላለስ እንደሚገባን የሚያሳይ ቃል ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የጻፈውን መልእክት በሁለት ቦታ ከፍሎ ማየት ይቻላል። ቀዳሚዎቹ ሦስት ምዕራፎች የሚገልጹት እግዚአብሔር በክርስቶስ ስላደረገውና ስለፈጸመው ሥራ ነው። በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ የቀረቡት አሳቦች አማኞች እምነታቸውን ሊመሠርቱበት የሚገባ እውነቶች ናቸው። ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ያሉት ሦስት ምዕራፎች ደግሞ የሚያተኵሩት፥ አማኞች እምነታቸውን በተግባር መግለጽ ወይም ማሳየት የሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ ነው። «ነን» እንደሚሉት መመላለስ ለተጠሩበት ጥሪ ተገቢ የሆነ ርምጃ ማድረግ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ምዕራፍ 4፥1 ላይ «... በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ» ይላል (ኤፌ. 4፥1)።

«ቤተ ክርስቲያን» ማለት «ተጠርተው የወጡ» ማለት እንደሆነ፥ «የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን» ማለትም «በአንድ አጥቢያ የሚገኙ

ተጠርተው የወጡ ሰዎች ስብስብ» ማለት መሆኑን ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የትምህርት ክፍሎች ተረድተናል። ጥሪው ከየት ወዴት፥ ከምን ወደ ምን እንደሆነ በጠቅላላው ስለ ጥሪው ክቡርነት ብዙ ተወያይተናል። እግዚአብሔር እኛን በክርስቶስ በኩል ወደ መንግሥቱ የጠራንና ያዳነን ለዓላማ ነው። ጥሪያችን መለኮታዊ የሆነ እቅድ (design) አለው። እግዚአብሔር ለጠራቸው ልጆቹ ያለው እቅድ አንድ እንዲሆኑ ነው። ጥሪውን ተቀብለው የመጡ ሁሉ ከነገድ፥ ከቋንቋ ከዘር የተውጣጡ ናቸው። ሌሎችም ልዩነቶች አሉ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ የምንመጣው ወደ አንድነት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሳለ ለተከታዮቹ የጸለየው ለዚህ አንድነት ነው።

«ለጥሪያችሁ ተገቢ የሆነ ርምጃ አድርጉ» ማለት እያንዳንዱ አማኝ ያለበትን ሃላፊነት ያመለክታል። ይህም ሃላፊነት ተገቢ የሆነ ርምጃ ማድረግ ነው። ተገቢ ያልሆነ ርምጃ ባይኖር ኖሮ፥ «ተገቢ የሆነ ርምጃ እንድታደርጉ እለምናችኋለሁ» አይባልም። ሃላፊነት የጐደለው የግዴለሽ ርምጃ የሚራመዱ ሰዎች አሉ። ለዚህ ነው ለተጠራችሁበት ጥሪ ተገቢ የሆነ ርምጃ አድርጉ የተባለው።

የመንፈስ አንድነትን መጠበቅ በተጠሩበት መጠራት እንደሚገባ መመላለስ ነው። በአማኞች መካከል የመለያየትን ዘር መዝራትና የክርስቶስን አካል መከፋፈል ተገቢ ያልሆነ ርምጃ ነው። ተገቢ ላልሆነ ርምጃ ጥሩ ምሳሌ የምትሆነን በቆሮንቶስ የነበረችው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ናት። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በተለያየ ቡድን ይከፋፈሉ ነበር። አማኞች «እኔ የእገሌ ቡድን ነኝ» እንዲሉ የሚያደርጉና የሚከፋፍሉ ክርስቲያኖች በውስጥዋ ነበሩ። በዚህ ምክንያት አንድነትና ሰላም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተናጋ፤ ብዙ ጭቅጭቆች ተፈጠሩ። ከዚህ ተገቢ ያልሆነ አረማመዳቸው የተነሣ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ» ያላቸው (1ቆሮ. 1፥10)።

የቆሮንቶስ ምእመናን መለያየትና መከፋፈል የነበራቸው በመንፈስ ሕፃናት ስለሆኑና መንፈሳዊነት ስለሚጐድላቸው ነው። ሥጋዊ ክርስቲያኖች ነበሩ። ሰይጣን ሰውነታቸውን እየተዋሰ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን የሚጐዳና የሚከፋፍል ሥራ ያሠራቸው ነበር (1ቆሮ. 1፥10-17፤ 3፥1-3)።



ሰይጣን በዘመናት ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የሚጠቀምበት ዘዴ አልተለወጠም። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋትና ለመጉዳት የተጠቀመበት መንገድ 3 ዐይነት ነበር። እነዚህም :-

1ኛ) ዓላማ ማስለወጥ - (Diversion)፤ ሐዋርያት የተጠሩበትን ዋና ጥሪ ትተው በሌላ ሥራ እንዲጠመዱና እንዲያዙ ምኞቱ ነበር፤ አልተሳካም። ምክንያቱም ሐዋርያት ዋና ሥራቸውን ቢተዉ የሚከተለውን ስለተረዱ ለችግሩ ጥሩ መፍትሔ አገኙለት (ሐ.ሥ. 6፥1-7)።

2ኛ) ስደት - (Persecution) (ሐ.ሥ. 8)፤ ስደት ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከምና ለማጥፋት በዘመናት ሁሉ የተጠቀመበት መሣሪያ ነው። ነገር ግን፥ በኢትዮጵያ ውስጥም በታየው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ቤተ ክርስቲያን በስደት ምክንያት ትበረታለች። የምእመናቿም ቊጥር ይጨምራል፤ የሕይወታቸውም ጥራት የተሻለ ይሆናል። በስደት ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን መጉዳት አይችልም።

3ኛ) መለያየት - (Dissention)፤ ሰይጣን ከውጭ ሆኖ ያቃተውን ውጤት ማግኘት የሚችለው ከውስጥ በአማኞች መካከል መለያየትን በማምጣት ነው። የሥጋዊ ክርስቲያኖችን አካል ይዋስና መለያየትን ዘርቶ መከፋፈልን ይፈጥራል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ለሚገኙ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፥

«ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ» (ሮሜ 16፥17)።

የሚለው አንድነትን መጠበቅ ለጥሪው ተገቢ የሆነ ርምጃ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ዋና ሕይወት የሆነውን የቃሉን እውነት በመቃወም፥ ማሰናከያና መለያየትን ማምጣት ቤተ ክርስቲያንን የሚጐዳ ተግባር ነው። የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ እያንዳንዱ ክርስቲያን ተግቶ መሥራት አለበት።

በጦርነት ታሪክ «የ5ኛ ረድፍ» ስለሚባል የጦር ግንባር ሰምተን ይሆናል። «የአምስተኛው ረድፍ» የሚለው ሀረግ በዕለታዊ ቋንቋ ውስጥ መግባት የጀመረው በስፔይን የሲቪል ጦርነት ጊዜ ሲሆን (1936-1939)፥ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የታወቀና የተለመደ ሆኖ ነበር።

የጠላት ጦር ለወረራ የሚሰለፈውና ከበባ የሚያደርገው በ4ቱም ማዕዘን ነው። ተከላካዩ ወገንም ጦሩን ለመከላከል የሚያሰልፈው ጠላት በሚመጣበት አራቱም ማዕዘን ነው። ይህ የተለመደ ወታደራዊ አሰላለፍ ነበር። ነገር ግን በስፔይን የሲቪል ጦርነት ጊዜ ወራሪው ጦር የማድሪድን ከተማ ወርሮ ሳለ፥ ሰዎች ጀኔራል ኤሚሎሞሌ ቫይዳል የተባለውን የጦር ጀኔራል፥ ከአራቱ የትኛው ረድፍ አሸንፎ ከተማይቱን ለመያዝ እንደሚችል ጠየቁት። እርሱም ሲመልስ፥ «ጦርነቱን የሚያሸንፈው የ5ኛው ረድፍ» (The fifth column) ነው አላቸው። ‹የአምስተኛው ረድፍ የጦር ግንባር› ሲል የሰየማቸው፥ በማድሪድ ከተማ ውስጥ ተሰግስገው ወሬ እየፈጠሩ በፕሮፓጋንዳ፥ በስለላ፥ በሻጥር ተከላካዩን ጦር ያሸብሩ የነበሩትን የውስጥ አርበኞች ነው።

አሜሪካንም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመኖች ጋር በአውሮጳ ውስጥ ስትዋጋ፥ አሜሪካ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ጀርመኖች ልዩ ልዩ ሻጥርና (Sabotage) ስለላ ያካሂዱ ነበር። እነርሱ «የ5ኛው ረድፍ» ተብለው ተጠርተዋል።

ሰይጣን በአራቱም አቅጣጫ የከፋት ሰራዊቱን አሰልፎ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጦርነት በማካሄድ ላይ ይገኛል። ድሉ የቤተ ክርስቲያን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነገር ቢሆንም፥ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተነጣው ጠላት በቀላሉ ተስፋ የሚቈርጥ ባለመሆኑ የሚናቅ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በአራቱም ማዕዘን ተኩስ የከፈተባት በቂ ጠላት አላት። ለጥፋትዋ የሚታገሉት የክፋት ሰራዊቶች ብዙዎች ናቸው፤ ስለዚህ የማያስፈልጋት ነገር ቢኖር ከውስጥዋ ሆኖ የሚጐዳት የ5ኛው ረድፍ ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ቤተ ክርስቲያኑን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከውስጥ ሆነው መለያየትን በመዝራት የሚዋጉትን ሥጋዊ ክርስቲያኖች መከላከል ሃላፊነቱ ነው። አንድነት ክቡር ነው፤ ብዙ ጥንቃቄም ስለሚጠይቅ እያንዳንዱ አባል፥ ከውስጥ ሆኖ አንድነትን የሚያጠፋውን ኃይል በመቃወም ኅብረትንና አንድነትን መጠበቅ አለበት።

መለያየትና መከፋፈል በአማኞች መካከል ሲኖር ቤተ ክርስቲያን በሚከተሉት መንገዶች ትጐዳለች።

1ኛ) የአማኞች ትዙረት ሰይጣን ላይ መሆኑ ይቀርና እርስ በርሳቸው ላይ ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ያስጠነቅቃል፤ «እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ» ይላል። (ገላ. 5፥15)።

2ኛ) መለያየት ሲኖር አማኞች የወንጌል ሥራ ላይ ማተኰራቸውና በአየር ላይ ካሉት ሥልጣናትና ኃይላት ጋር መዋጋታቸው ይቀራል። ኃይላቸውን የሚጨርሱት እርስ በርስ በመጐዳዳት ይሆናል።

3ኛ) በወንድማማችና በእኅትማማች መካከል ሊኖር የሚገባው ፍቅር ይጠፋል። ይህ ለሰይጣን ጆሮ ጣፋጭ ሙዚቃ ነው።

4ኛ) ለዓለም ሰዎች የተሳሳተ መልእክት ይሰጣል፤ «የክርስቶስ አካል የተከፋፈለ ነው ምንም አንድነት የላቸውም» በማለት ይሥቃሉ።

5ኛ) የአማኞች ምስክርነትና የወንጌል ሥራ ይጐዳል። የክርስቲያኖችን ወሬና ሐሜት ሰምቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣትም ክርስቶስን መቀበልም ማንም አይፈልግም።

6ኛ) ለክርስቶስ በመሥራት ፈንታ ሁሉም የራሱን ቲፎዞ ለማበጀት ይራወጣል።

7ኛ) ኅብረት ይበላሽና መንፈስ ቅዱስ በኅብረቱ መካከል በነፃነት እንዳይመላለስ ያግዳል።

ስለዚህ የእውነተኛ ክርስቲያን ብስለቱና መንፈሳዊነቱ የሚታወቀው ለተጠራበት መጠራት ተገቢ የሆነ መመላለስ ሲያደርግ ነው። «ነን» እንደምንለው ሆነን እንገኝ፤ የመንፈስን አንድነት እንጠብቅ።

## ልዩ ቡድን አለመፍጠር

አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል የመንፈስ አንድነትን እንደ ዓይኑ ብሌን መጠበቅ እንደሚገባው ቀደም ሲል አትተናል። እግዚአብሔር የሚሠራውና በረከቱን የሚለቀው የመንፈስ አንድነት ፍሰት ባለበት ስፍራ ነው (መዝ. 133)።

ለመንፈስ አንድነት ፍሰት ተፃራሪና ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥራ እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች አንዱ የግል ዓላማና አጀንዳ ባላቸው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሚፈጠሩት ልዩ ቡድኖች (groups) ናቸው። ብዙ ጊዜ እንዚህ ልዩ ቡድኖች የሚፈጠሩት ጸሎትን በመሳሰሉ መልካም ነገሮች ስም ነው። የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም አንድ ወጥ በሆነ መመሪያና አሠራር መካሄድ አለበት። ከዚህ ውጭ የግለሰቦችን አጀንዳ ተከትለው የሚፈጠሩ ልዩ ቡድኖች ሲኖሩ ለቤተ ክርስቲያን ጤንነትና ሰላም ትልቅ እንቅፋቶች ይሆናሉ።

በግል መኖሪያ ቤቶች የሚካሄዱ የጸሎት ስብሰባዎች በቤተ ክርስቲያን መመሪያ ሥር ሲሆኑ፥ ለምእመናን ጤናም ዕድገትም ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው። ብዙ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እንደአስፈላጊነቱ ምእመናችን

በየሰፈሮቻቸው የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን እንዲኖራቸው አንድ ወጥ በሆነ አገልግሎት የሚያደራጇቸው ለዚህ ነው። ከቤተ ክርስቲያን አመራር ውጭ የተለየ አጀንዳ ባላቸው ግለሰቦች ሲካሄዱ ግን የቤተ ክርስቲያንን አሠራር ከመፃረርና ከመጕዳት በቀር ምንም ጥቅም አይሰጡም፤ ለመንፈስ አንድነትም ጠንቅ ናቸው። በርካታ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፥ ጸሎትና የመሳሰለው መልካም ክርስቲያናዊ ተግባር ላይ ብቻ በማተኮር፥ ሳያውቁት ለቤተ ክርስቲያናቸው አንድነትና አሠራር ተፃራሪ የሆነ ቡድን አባል ሆነዋል።

ከቤተ ክርስቲያን አመራር ውጭ ልዩ ቡድን መፍጠር ፦ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን፤ በኣየር ውስጥ ኣየር፤ ለአንድ ዓላማ በተሰየመ አገልግሎት ውስጥ የግል ዓላማ ማካሄድ ነው። የግል አጀንዳ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አጀንዳ ካልታዘዘ ውጤቱ ሁል ጊዜ ለአንድነትና ለወንጌል ሥራ ጠንቅ ነው።

ልዩ ቡድን ሁል ጊዜ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግሮች ምንጭ ነው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከተናወጠችባቸው ችግሮች አንዱ ‹ልዩ ቡድን› እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ችግር በተመለከተ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ተግሣጽና መመሪያ ሰጥቷል (1ቆሮ. 1፥10-25፤ 3፥1-10፤ 11፥17-23)።

«ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ። በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና። ይህንንም እላለሁ ፦ እያንዳንዳችሁ ፦ እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?» (1ቆሮ. 1፥10-14)።

የቆሮንቶስ ምእመናን በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እያሉ በአራት ቡድን ተከፋፍለው ነበር። በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የግል አጀንዳ የነበራቸው ቀንደኛ መሪዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ሊከፋፈሉ በማይችሉ አገልጋዮችና በክርስቶስ ስም የግል አጀንዳቸውን ያካሂዱ ነበር። የሚያሳዝነው ለግል አጀንዳ ሲሉ ክርስቶስ የሞተላት ቤተ ክርስቲያን እንድትከፋፈልና የመንፈስ አንድነት እንዲናወጥ መምረጣቸው ነው። ብዙዎች እንዲህ ያለውን አስነዋሪ ተግባር ከመንፈስ ቅዱስ አሠራር ጋር ለማገናኘት መሞከራቸው ደግሞ የበለጠ አስገራሚ ነው። መንፈስ ቅዱስ



የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሥራ እየባረከ የመንፈስ አንድነት እንዲፈስ ያደርጋል እንጂ አይከፋፍልም።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ቡድን፥ በጥንት ቤተ ክርስቲያን «የፍቅር ግብዣ» የተባለውን የተለመደ የአንድነት ጊዜ ሳይቀር ጤናማ ባልሆነ መንገድ በክሎት ነበር። «የፍቅር ግብዣ» የሚባለው፥ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኒቷ ምእመን የሚበላውን ይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣና ሁሉም ያመጡትን ደባልቀው አብረው ይበሉ የነበረው ልምምድ ነው። የሚበላ ማምጣት የማይችሉ ምእመናን ቢኖሩ እንኳን ምንም ሳይሰማቸው በግብዣው ላይ ተገኝተው አብረው የቀረበውን ይበሉና ይጠጡ ነበር።

«የፍቅር ግብዣ» ዓላማው አንድነትን፥ ፍቅርንና፥ ኅብረትን ለማጠናከር ነበር። ነገር ግን በ1ቆሮንቶስ 11፥11-22 እንደምንመለከተው፥ ቡድን የፈጠሩት ሰዎች ተለይተው በመብላትና በመጠጣት አንድነቱ እንዲመሰቃቀል አደረጉ። ድሆችም፥ ያላቸው ሰዎች ካመጡት ምግብ ሳይካፈሉ ቀሩ። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ፥ «የፍቅር ግብዣ» ይደረግ የነበረው ከቅዱስ ቍርባን ቀደም ብሎ ስለነበር፥ እነዚህ ሰዎች ከቤታቸው የሚያሰክር ወይን ይዘው መጥተው በመጠጣት መስከራቸው ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ለማሳፈር በመልእክቱ በግልጽ የገሠጸና ያረማቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግር ከውጭ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን፥ ከውስጥም እንደሚነሣ ለማሳሰብ የሐዋርያት ሥራ 20 ላይ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፥ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ» ብሏል (ቍ. 28-31)። ብዙ ጊዜ በጸሎት ርእሶች ወይም ለቤተ ክርስቲያን አሳቢ መስለው በሚሰጡ አስተያየቶች አማካይነት አንድነትን የሚጎዱ ጠማማ ወሬዎች የሚስፋፉት ከቤተ ክርስቲያን አመራር ውጭ በሚካሄዱ ጤናማ ባልሆኑ ቡድኖች ነው።

«መለያየትን የሚያነሣ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ፥ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሠጽኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ» (ቲቶ 3፥10-11)።

«ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። ... በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችንን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር፥ ይህን ተመልከቱት፥ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተባበሩ» (2ተሰ. 3፥6፡ 14)።

«ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ፈቀቅ በሉ» (ሮሜ 16፥17)።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል፥ (ሀ) ሳያውቀው ራሱን እንደዚህ ካለ ቡድን ውስጥ እንዳያስገባ መጠንቀቅ፤ (ለ) የተሳሳቱትንም በፍቅር ስሕተታቸውን በመንገር መመለስ አለበት። እንኳን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ አንድ ዓላማ ባለው ማንኛውም ድርጅት ውስጥ የልዩ ቡድን መፈጠር የማኅበሩን ሥራ ያዳክማል እንጂ አያራምድም። በተለይ ደግሞ ለአንድነት ከፍተኛ እንቅፋት ነው።

## ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መልካም መናገር

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፍጹምነት ባይኖራትም ማንም ሳያስገድድህ ወደህና መርጠህ የገባህባት ቤተሰብህ ናት። ቤተሰቡን ማንም አይሳደብም፤ ቤተሰቡን የሚሳደብ ራሱን ይሳደባል።

አንድ ጊዜ፥ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙ አባሎች መካከል በጣት የሚቈጠሩት ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው መልካም በመናገር ፈንታ ሁል ጊዜ ክፉ መናገር ይመርጡ ነበር። እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እያናናቁና እያንቋሸሹ በመናገራቸው ቀስ በቀስ የብዙ አባላት አእምሮ ተበከለ። ቤተ ክርስቲያኒቷ ምንም ሕይወት እንደሌላትና ዋጋ እንዳጣች የሚወራው ወሬ ቀስ በቀስ መጋቢው ጆሮ ደረሰ።

መጋቢው፥ እየተዛመተ በመሮጥ ላይ ያለው ወሬ የጥቂት ሰዎች አጀንዳ ያዘለ የግል አስተያየትና የወሬው መንፈስም ለመገንባት አለመሆኑን ተረዳ። ወሬውን የሰሙት ሁሉ እንዳዘኑ በመገመቱ እሁድ ጠዋት ለምእመናኑ፥ «ቤተ ክርስቲያናችን ዋጋ የላትም፤ ሞታለችም፤ ዛሬ ማታ የአሸኛኘት ፕሮግራም አድርገን የቀብር ሥነ ሥርዓት ስለምናደርግላት አባሎቿ የሆናችሁ ሁሉ እንድትገኙ» ሲል ማስታወቂያ አደረገ። የማታው ስብሰባ ከመድረሱ በፊት መጋቢው የሬሳ ሳጥን ገዛ። በሬሳው ሳጥን ልክ የፊት መስተዋት አስቈረጠና ከሳጥኑ ውስጥ አስቀመጠ። የሬሳ ሳጥኑንም ከምስባኩ (ከፑልፒቱ) በታች ከሕዝቡ መቀመጫ ፊት ለፊት አስቀመጠ።



ማታ ምእመናኑ ለሽኝቱ ፕሮግራም ሲሰበሰቡ መዝሙር ከተዘመረ በኋላ መጋቢው ተነሥቶ «ምእመናን ሆይ! ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ሞተች ከመቀበራችን በፊት እያንዳንዳችሁ ወደ አስከሬኑ ቀርባችሁ የመጨረሻ ስንብት አድርጉላት» አለና የሬሳ ሳጥኑን ከፍቶ ቁጭ አለ። ምእመናኑም እንደተጠየቁት አንድ በአንድ ወደ ሬሳ ሳጥኑ እየመጡ አስከሬኑን ለመሰናበት ጐንበስ ሲሉ የየራሳቸውን ፊት ያዩ ነበር። ያን ጊዜ ሁሉም መጋቢው ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ገባቸው።

ማንም ራሱን ሳይጐዳ ቤተሰቡን የሚሳደብ የለም። ቤተ ክርስቲያን ስትጐዳ ሁላችንም እንጐዳለን። በተለይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች ማንም ክርስቶስን ሳይጐዳ ቤተ ክርስቲያንን መጕዳት አይችልም።

በአንዳንድ ግለሰቦች ላይ ችግር ያለው ሰው፥ የእግዚአብሔር ቃል በማቴዎስ 18፥15-18 በሚለው መሠረት ጕዳዩ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር በቀጥታ መነጋገር ይገባዋል። በቀጥታ መነጋገር ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ነገር ግን እንዲሁ ቤተ ክርስቲያንን ወይም አገልጋዮችን መንቀፍና ጠማማ ወሬ ማስፋፋት ከአንድ መንፈሳዊ ሰው የማይጠበቅ አሳፋሪ ባሕርይ ነው።

አንድ አባል በራሱ ፈቃድ መርጦ ቤተሰቡ ስላደረጋት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መልካም እንጂ ክፉ መናገር የለበትም። መልካም መናገር ለማያምኑ ሰዎች መስክሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት ያስችላል። አንድ ሰው ስለ ቤተ ክርስቲያኑ የሚናገረው ክፉ ከሆነ የዚህን ሰው ምስክርነት ሰምቶ ማን ወደዚያች ቤተ ክርስቲያን ሊመጣ ይችላል? ስለ ቤተ ክርስቲያን ክፉ ማውራት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ከማቍሰሉም በላይ፥ በውጭ ያሉት እንዳይድኑ በር ይዘጋል። ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን መልካም እንጂ ክፉ መናገር የሌለብን ለዚህ ነው።

## በሚያራርቅ ሳይሆን በሚያቀራርብ ነገር ላይ ትኵረት ማድረግ

እግዚአብሔር በዓለም ላይ አንድ ዐይነት አድርጎ የፈጠራቸው ሁለት ሰዎች የሉም። ልዩ ልዩ መሆናችን የብርታት እንጂ የድካም ምክንያት አይደለም።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከሌላው ጋር ባለው ግንኙነት የሚያራርቀው ነገር ላይ ሳይሆን የሚያቀራርበው ላይ ማተኰር አለበት። የመንፈስ አንድነት የሚጠበቀው፥ በቤተ ክርስቲያን የወንድማማችነትና የእኅትማማችነት ፍቅር የሚኖረው፥ ሰላምም የሚበዛው እንዲህ ያለውን ትክክለኛ ምርጫ ስናደርግ ነው።

## ከሚገባ በላይ አለመጠበቅ

ዳዊት በመዝሙሩ «ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን? መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና» ይላል (መዝ. 62፥1)። የእንግሊዝኛው ትርጉም «ነፍሴ በፀጥታ እግዚአብሔርን ትጠብቃለች፤ የምጠብቀው ከእርሱ ነው» ይላል።

አንድ ሰው ተስፋ የሚቈርጠው የጠበቀውን ሳያገኝ ሲቀር ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች በአገልጋዮችና በቤተ ክርስቲያን ተስፋ የሚቈርጡት ከልክ በላይ የሆነ ጥበቃ ስላላቸው ነው። ስለዚህ ገና አባል በምትሆንበት ጊዜ እንዲደረግልህ የምትፈልገው ነገር ካለ በግልጽ ጠይቀህ መልሱን አግኝ። ይህንን ብታደርግ መጠበቅ የሚገባህንና የማይገባህን ለይተህ ትረዳለህ። አንዳንድ ጊዜ ችግሮች የሚፈጠሩት ሰዎች ይህንን ሳያደርጉ ሲቀርና በአጠቃላይ ከሰዎች ብዙ ሲጠብቁ ነው።

## ከመንቀፍ ይልቅ ማበረታታትን መምረጥ

«አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል» (ሮሜ 14፥4)።

መጽሐፍ ቅዱስ በፍቅር እውነትን እንድንነጋገር ያስተምራል። በሌላው ላይ መፍረድንና መንቀፍን ግን አይደግፍም (ማቴ. 7፥1-2)።

ሌላውን ሰው የሚነቅፍ :-

- ከወንድሙ ጋር ያለውን ኅብረት ያበላሻል፤
- በአብዛኛው እርሱ መልካም መስሎ ለመታየት ስለሆነ የሚፈልገው፥ ሁሉንም ከሚያውቅ አምላኩ ጋር ያለውን ኅብረት ያበላሻል፤
- በሌላው ላይ ዳኛ ሆኖ በመፍረዱ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንዲፈርድበት ይጋብዛል (ማቴ. 7፥1-2)፤
- በነቀፋው ምክንያት ወንድምና ወንድምን ስለሚያራርቅ የመንፈስ አንድነትን ያናጋል።

ስለዚህ አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል በቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙትን ሰዎች በመንቀፍ ፈንታ ማበረታታትን ሊመርጥ ይገባዋል።

## ሐሜትን አለመስማት

(ምሳ. 16፥28፤ 17፥4፤ 20፥19፤ 25፥9፤ 26፥20)



ሌባ የሰረቀውን ዕቃ መቀበልና የሐሜተኛን ሐሜት መስማት አንድ ነው። ተቀባዩ የሌባውን ያህል ወንጀል እንደፈጸመ፥ ሐሜት ተቀባዩም ከሐሜተኛው እኩል ኃጢአት ይፈጽማል።

ሐሜት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጣው ጥፋት ዐያሌ ስለሆነ፥ ከመስማትህ በፊት የሶቅራጥስን ሦስት የሐሜት ማበጠሪያ ፈተናዎች ተጠቀም።

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ሶቅራጥስ መጣና፥ «ስለ ጓደኛህ የሰማሁትን ወሬ ልንገርህ!» አለው። ሶቅራጥስም «ቆይ ከመንገርህ በፊት 3 የማበጠሪያ ፈተናዎች እናድርግለት» አለውና የሚከተሉትን ሦስት ፈተናዎች አቀረበለት።

ሀ) የእውነትነቱ መፈተኛ

ሶቅራጥስ፥ «አሁን ልትነግረኝ የፈለግከው ነገር እውነት ለመሆኑ ፍጹም እርግጠኛ ነህን?» ሲል ጠየቀ። ሰውየውም «አይደለሁም፤ ነገሩን የሰማሁት ገና አሁን ነው» አለ።

ለ) የመልካምነቱ መፈተኛ

ሶቅራጥስም፥ «እውነት መሆን አለመሆኑን አታውቅም። አሁን ደግሞ ሌላ ጥያቄ ልጠይቅህ። ይህ ስለ ጓደኛዬ ልትነግረኝ የፈለግከው ነገር መልካም ነውን?» ሲል ጠየቀ። ሰውየውም «አይደለም!» አለ።

ሐ) የጠቃሚነቱ መፈተኛ

ሶቅራጥስም እንደገና፥ «ይህ ስለ ጓደኛዬ ልትነግረኝ የፈለግከው ነገር ለእኔ ጠቃሚነት አለውን?» ሲል ጠየቀ። ሰውየውም «ጠቃሚ አይመስለኝም» አለ። ሶቅራጥስም «ልትነግረኝ የፈለግከው ነገር እውነት ለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆንክ፥ መልካም ካልሆነና የማይጠቅመኝ ከሆነ ነገሩን ለመስማት አልፈልግም» አለ ይባላል።

እያንዳንዳችን ስለ ሌሎች ለምንሰማው ወሬ እነዚህን መፈተኛዎች ብንጠቀም ሐሜትን አናደፋፍርም። አንድ አባል የቤተ ክርስቲያኑን አንድነትና ጥሩ ስም የሚጠብቀው ሐሜትን በማደፋፈር ፈንታ ሲቃወምና ሲያስወግድ ነው። ከሌላ ሰው ጋር ችግር ያለው፥ ጌታ በማቴ. 18፥15-20 በሰጠው መመሪያ መሠረት ጉዳዩን በቀጥታ ከሚመለከተው ጋር በመነጋገር እንዲያስተካክል እንጂ ሐሜትን እንዳያስፋፋ ማረም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሃላፊነት ነው።

### የችግሩ ሳይሆን የመፍትሔው ክፍል መሆን

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚነሡ ችግሮች አብዛኞቹ በአሳብ ካለመግባባት የሚመጡ ናቸው። ይህንን በአሳብ አለመግባባት አንዳንዶች በሐሜት፥ በነቀፋ፥ በማጉረምረም፥ በስም ማጥፋት ወዘተ መልክ ለሌሎች ጆሮ እንዲዳረስ ያደርጉታል። አንድ ጥናት እንደሚያሳየው፥ ከእንዲህ ያሉት ችግሮች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ችግር በነበራቸው ሰዎች የተደገሙ ናቸው።

ስለዚህ አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል በቀላሉ በሚሰማው ሁሉ ተወስዶ የችግሩ ክፍል ከሚሆን፥ ትክክለኛውን ምክር በመስጠትና ሰዎችን ከስሕተት በመመለስ የመፍትሔው (መልሱ) ክፍል መሆን አለበት።

### በኵራትንና አሥራትን በታማኝነት መክፈል

መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ አማኝ ከገቢው 10 በመቶ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጥ ያዛል (ሚልክ. 3፥8-12)። ስለዚህ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሃላፊነት አንዱ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በሰዓቱና በጊዜው ወደ ጐተራው (ቤተ ክርስቲያን) መመለስ ነው። አሥራት መክፈል በመሠረቱ ለጌታ መስጠት ሳይሆን፥ ጌታ «የእኔ ነው» ያለውን የራሱን ድርሻ (1/10ኛ) ለእርሱ ማስረከብ ነው። ማንም ሰው አሥራቱን ከመስጠቱ በፊት ለእግዚአብሔር ስጦታ ሰጠሁ ብሎ ማሰብ የለበትም። አስቀድሞ አሥራት ሳይከፈል ስጦታ እንደተሰጠ መቍጠር አይቻልም። እግዚአብሔር የገቢያችንን አንድ አሥረኛ «የእኔ ነው» ካለ፥ የአሥራት ገንዘብ ከእኛ ኪስ ወይም የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቈየት የለበትም።

የእግዚአብሔር የሆነውን ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመመለስ፥ አማኝ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ አማካይነት የሚከናወነውን የእግዚአብሔር ሥራ ይደግፋል። አሥራት የሚከፍል ሰው የእግዚአብሔር ሥራ እንዲሠራ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ እንዳይጓተት ድምፅ ይሰጣል። አሥራቱን የማይሰጥም የዚህ ተቃራኒ እንዲሆን የመረጠ ነው።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል እስከ አሁን ድረስ በተወያየንባቸው ነጥቦች ያነሣናቸውን ሃላፊነቶች ሁሉ መፈጸም አለበት። ክብርት ለሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ትክክለኛው አመለካከት ሊኖረው ይገባል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ልዩ ልዩ ችግሮች ሲከሰቱ የችግሩ ክፍል ሳይሆን የችግሩን መፍትሔ ከሚፈልጉት አንዱ መሆን አለበት።



## ምዕራፍ አሥራ አራት

## የቤተ ክርስቲያን ዲሲፕሊን

አንድ ሰራዊት ጥሩ ውጤት የሚያመጣውና ከዓላማና ከግቡ የሚደርሰው በዲሲፕሊን የተገነባ ሲሆን ነው። ትምህርት ቤቶች ስኬት የሚያገኙት ለተማሪዎቻቸው የቀለም ትምህርት ብቻ ሲያስተምሩ ሳይሆን፥ ሕይወታቸው በዲሲፕሊን እየተገነባ እንዲያድግ ሲያደርጉ ነው። ያለ ዲሲፕሊን የቀለም ትምህርት ብቻ ለተማሪዎች ምንም ጠቃሚነት የለውም። እንደዚሁም ወላጆች ልጆቻቸውን ሲሳሳቱና ሲያጠፉ ተገቢ የሆነውን ተግሣጽ፥ ምክርና፥ ቅጣት እየሰጡ በጥሩ ዲሲፕሊን ማሳደግ አለባቸው። ይህንን ባያደርጉ ልጆቹ አግድም አደግና ብልሹ መሆናቸው የማይቀር ነው። ዲሲፕሊን የጐደለው ምንም ዐይነት ተቋም የቆመለትን ግብ መምታት አይችልም።

ዲሲፕሊን፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአማኞችን ሕይወት በእግዚአብሔር ቃልና በዲሲፕሊን በመገንባት በእንክብካቤ ማሳደግ ይገባታል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጠፉትን በወንጌል ፈልጎ ወደ ክርስቶስ ማምጣት ብቻ አይደለም። የክርስትና ግቡ ክርስቶስ ስለሆነ፥ የአማኞች ሕይወት ክርስቶስን እንዲመስል፥ በቃሉ ምክር እየተቀረጸና እየታነጸ እንዲያድግ ማድረግ ይገባታል። ቤተ ክርስቲያን የአማኞችን ሕይወት ከምትቀርጽበት መንገድ አንዱ ዲሲፕሊን በመሆኑ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሥፍራ ሊሰጠው ይገባል።

ወላጆች ለልጆቻቸው ምክርና አቅጣጫ እንደሚሰጡ፥ ቤተ ክርስቲያንም ለምእመኖቿ አቅጣጫና ምክር በመስጠት ሕይወታቸውን መምራት አለባት። ልጆች ሲያጠፉ ወላጆቻቸው በተግሣጽና በቅጣት ከስሕተታቸው እንዲመለሱ እንደሚያደርጉ፥ ቤተ ክርስቲያንም ምእመኖቿን ከስሕተት ለመመለስ አስፈላጊውን ምክርና ተግሣጽ መስጠት አለባት። ምክርና ተግሣጽ የማይመልሳቸውን ደግሞ የዲሲፕሊን ርምጃ በመውሰድ ከክፉው መታደግ ይገባታል። ልጆቻቸው በስሕተት ጐዳና ሲራመዱ አይተው ዝም የሚሉ ወላጆችና፥ ምእመኖቿ ሲስቱ የማታቃና

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም መጨረሻ ላይ በሚገኘው ውጤት ማዘናቸውና መጸጸታቸው የማይቀር ነው።

ሕይወት ፈተናና ችግሮች ስለሞሉባት፥ ሰዎች መሳሳታቸውና መውደቃቸው አይቀርም። ይህን ለመከላከል የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ ለምእመናቿ ከቃሉ የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክርና አቅጣጫ በመስጠት ዲሲፕሊን ማስተማር አለባት። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሁሉ አድርጋ አንዳንድ ምእመናን ከስሕተት ላይ መውደቃቸው የማይቀር ከሆነ፥ ለስሕተታቸው ተጠያቂነት (accountability) እንዲኖራቸው ማድረግና ተመልሰው እንዲቃኑም የዲሲፕሊን ርምጃዎችን መውሰድ ይገባል።

## 1. የዲሲፕሊን ዐይነቶች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዲሲፕሊን በሦስት ይመደባል፤

ሀ) የግል ዲሲፕሊን (Self discipline)

‹የግል ዲሲፕሊን› የምንለው፥ አንድ አማኝ ማንም ሳይነግረው ራሱ በጌታ ፊት ሕይወቱን በቃሉ የሚመረምርበትና ስሕተት ካየ በራሱ ፈርዶ ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክልበት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስተምር «ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፤ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር» ይላል (1ቆሮ. 11፥28-31)። ራሱን በመመርመርና በራሱ በመፍረድ ሕይወቱን የሚያስተካክል ሰው፥ ዲሲፕሊን ስለሚለማመድ እግዚአብሔር አይፈርድበትም። ለክርስትና ሕይወት ንጽሕናና እድገት የግል ዲሲፕሊን በጣም ጠቃሚ ነው።

ለ) አስቀድሞ የመከላከል ዲሲፕሊን (Preventive discipline)

አንዳንድ ሰዎች ይህንን፥ ‹አቅጣጫ ሰጪ ዲሲፕሊን› (Directive discipline) ሲሉት፥ ሌሎች ደግሞ ‹የሚያሳውቅ ዲሲፕሊን› (Formative discipline) ይሉታል። በየትኛውም ስም እንጥራው የዚህ ዐይነቱ ዲሲፕሊን አንድ ስሕተት ከመደረጉ፥ ኃጢአት ከመፈጸሙ አስቀድሞ ምእመናን ውድቀት ላይ እንዳይደርሱ ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠው ምክርና ትምህርት ሁሉ የመከላከል ዲሲፕሊን ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ምእመናቿ ራሳቸውን እየመረመሩ ከስሕተት ተጠብቀው እንዲራመዱ የተለያየ ትምህርትና ምክር ትሰጣለች። ይህ የመከላከል ዲሲፕሊን ማድረግ ነው።



ሐ) የእርምት ዲሲፕሊን - (Corrective discipline)

ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ የመከላከያ ዲሲፕሊን ብትሰጥም አልፎ አልፎ ከስሕተት የሚወድቁና ኃጢአት የሚፈጽሙ ምእመናን አይጠፉም። የእርምት ዲሲፕሊን የሚሰጠው፥ ስሕተት ያደረገውን ወይም ኃጢአት የሠራውን ምእመን ለማቃናትና ለማስተካከል ነው። ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን ርምጃ የምትወስደው የተሳሳተውን ወንድም ለማጥፋትና ለመጉዳት ሳይሆን፥ ተጸጽቶ ንስሐ እንዲገባ ነው። ምክርን፥ ተግሣጽንና ለእርምት የሚሰጠውን የዲሲፕሊን ቅጣት የማይቀበል ሰው በሚኖርበት ጊዜ፥ ወረድ ብለን እንደምንመለከተው፥ ቤተ ክርስቲያን ከረር ያለ ቅጣት ያለው የዲሲፕሊን ርምጃ መውሰድ ትችላለች።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፥ እንዲስተካከልበት የተሰጠውን ቅጣት አልቀበልም ብሎ የኰራ ሰው ከፍተኛ ቅጣት እንደሚደርስበት በኦሪት ዘዳግም እናያለን።

> «እንዳስተማሩህም ሕግ፥ እንደነገሩህም ፍርድ አድርግ፤ ከነገሩህ ፍርድ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። ማናቸውም ሰው ቢኰራ፥ በዚያም አምላክህን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቆመውን ካህኑን ወይም ፈራጁን ለመስማት ባይወድድ፥ ያ ሰው ይሙት፥ ከእስራኤልም ዘንድ ክፉትን አስወግድ፤ ሕዝቡም ሁሉ ሰምቶ ይፈራል፥ ከዚያም ወዲያ አይኰራም» (ዘዳ. 17፥11-13)።

ዘመኑ የጸጋ በመሆኑ ዛሬ መወገርና መሞት የለም። ይሁንና ቤተ ክርስቲያን፥ እምቢ በሚለውና በማይሰማው ላይ ለሌሎችም ትምህርት እንዲሆን የመጨረሻ ቅጣት የሚሰጥ ዲሲፕሊን (Punitive disciplene) ለማድረግ ትችላለች። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሰይጣን እንኳን አሳልፎ የሰጣቸው ሰዎች እንደነበሩ አዲስ ኪዳን ውስጥ እናነባለን (1ቆሮ. 5፥5፤ 1ጢሞ. 1፥20)።

ዛሬ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉት፥ ችላ ያሉት ነገር ቢኖር የዲሲፕሊን ጉዳይ ነው። ዲሲፕሊን ማስተማር ችላ ያሉበትም ምክንያት እንደየአብያተ ክርስቲያናቱ የተለያየ ነው። በአንዳንድ ስፍራ የዲሲፕሊን ርምጃ የማይለማመዱት፥ በርካታ ምእመናን ዲሲፕሊን አይቀበሉምና ዲሲፕሊን ቢደረጉ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሄዱብናል ብለው በመፍራት ነው። በመሠረቱ ግን ይህና ሌላውም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ የተሰጣትን ሥልጣን ከመጠቀምና ልጆቿን ከማረም ሊከለክላት አይገባም። ዲሲፕሊን

በጐደለበት የትም ቦታ ችግር እንደሚኖር፥ ቤተ ክርስቲያንም ምእመናኗን ዲሲፕሊን ካላደረገች በውስጧ ብዙ ችግሮች ይከሰታሉ።

## 2. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን አስፈላጊነት

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዲሲፕሊን ሥርዓት እንዲኖር የሚያስፈልገው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

ሀ) የእግዚአብሔር ቅድስና

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗን በዲሲፕሊን እያቃናችና እያረመች ከምታሳድግበት ምክንያቶች አንዱ የእግዚአብሔር ቅድስና ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ያስተምራል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ለክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ሲናገር፥

> «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» ይላል (1ጴጥ. 1፥15)።

እግዚአብሔር፥ ቅዱስ የሆነው ማንነቱ ከሕዝቡ ቅድስናን እንዲጠይቅ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ኃጢአትን በአየበት ቦታ ሁሉና በአገኘበት ሰው ሕይወት ሁሉ ይጠላዋል። እግዚአብሔር ኃጢአትን፥ እርሱን በማያውቁ ሰዎች ሕይወት ሲያየው የሚጠላውን ያህል፥ በአማኞች ሕይወትና በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሲያየው ይጠላዋል። በአማኞች ሕይወት ሲያየው «ይህ የልጆቼ ነውና ግዴለም» አይልም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ «ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» የሚለው (12፥14)። በዕብራውያን 12፥10 ላይም፥ «... እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል» ይላል። እንዲሁም፥ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ» ተብሎ ተጽፎአል (1ቆሮ. 3፥16-17)።

እግዚአብሔር ምን ዐይነት አባት እንደሆነ ለማወቅ ከፈለግን በዕብራውያን 12፥5-15 ያለውን ክፍል መመልከት ተገቢ ነው። እግዚአብሔር እንደማንኛውም ወላጅ ለጥቅማችን ዲሲፕሊን የሚያደርግና የሚቀጣ አባት ነው። እግዚአብሔር፥ በጥፋት ጐዳና የሚሄዱትን ልጆች ስለሚያውቅ በቀጥታ ራሱ ዲሲፕሊን ያደርጋል፤ እንዲመለሱ ለጥቅማቸው ይቀጣል። የአንድ ሰው ኃጢአት የሚታወቅና የሚታይ ከሆነ



ደግሞ ዲሲፕሊን የመስጠቱን ሥልጣን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል (ማቴ. 18፥15-20፤ 1ቆሮ. 5፥12-13)።

እርሾ ካልተወገደ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ፥ ክፋትም ካልተወገደ ወደ ሌሎች ይተላለፋልና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ይጐዳል (1ቆሮ. 5፥6-8)። የሚናገሩትና የሚኖሩት ሕይወት ከተለያየ ምእመናን ምስክርነታቸው ይበላሻል (ሮሜ 2፥17-24)። ኃጢአት በምእመናን ሕይወት ሲኖር ልክ በጭቃ እንደተለወሰ መስተዋት ይሆናሉ። የእርሱን ክብር መፈንጠቅ አይችሉም። ሰዎች የሚያዩት የሚፈነጥቁትን ክብር ሳይሆን፥ የተለቀለቁትን ጭቃ ስለሚሆን ምስክርነት ይበላሻል።

የዲሲፕሊን ርምጃ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር ያለበት የእግዚአብሔር ቅድስና ስለሚጠይቅ ነው። ቤተ ክርስቲያን በዲሲፕሊናዊ ርምጃ የሳቱትንና ኃጢአት ያደረጉትን በማቃናት በንስሐ ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ታደርጋለች።

ለ) በቃሉ ስለታዘዘ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗን በዲሲፕሊናዊ ርምጃ የምታቃናው ጉዳዩ በእግዚአብሔር ቃል ስለታዘዘ ነው። ገና ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ከመመሥረቷ በፊት ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፥ በሁለት ወንድማማቾች መካከል ችግር ቢኖር ነገሩን ለመጨረሻ ጊዜ በዳኝነት የምትመለከተውና የዲሲፕሊን ርምጃ የምትወስደው ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ተናግሯል (ማቴ. 18፥15-20)። ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን ቅጣት እንደምትሰጥ በሌሎችም ክፍሎች በቃሉ ተገልጿል (ሮሜ 16፥17፤ 1ቆሮ. 5፥1-13፤ 2ቆሮ. 2፥5-11፤ 2ተሰ. 3፥6-15፤ 1ጢሞ. 1፥18-20፤ ቲቶ 3፥10-11፤ ራእ. 2፥20)።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን ርምጃ የምትወስደው የእግዚአብሔር ቅድስና ስለሚጠይቀውና በቃሉ የታዘዘ ሥርዓት በመሆኑ ነው።

## 3. የዲሲፕሊን ጥቅምና ዓላማ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዲሲፕሊን የምትሰጠው የሚከተሉት ጥቅሞች ስላሉት ነው።

ሀ) ሰው እንዲጸጸትና ንስሐ እንዲገባ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለአንድ አባል የዲሲፕሊን ቅጣት የምትሰጥበት የመጀመሪያ ዓላማዋ ያ ሰው ተጸጽቶ በንስሐ ከጥፋቱ

እንዲመለስ ለማድረግ ነው። ዲሲፕሊን አንድን አማኝ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ያለውን ግንኙነት አስተካክሎ እንዲታደስ ዕድል ይሰጠዋል።

ለ) ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት

አንድ አማኝ በጥፋቱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ዲሲፕሊን ሰጥታው ንስሐ ሲገባና ሲስተካከል እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ሌሎችም ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሰጡ ይሆናል።

ሐ) ሌሎችን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ

የዲሲፕሊን ርምጃ፥ ሌሎች አማኞች የዲሲፕሊን ቅጣት ያገኘውን ሰው በመመልከት እነርሱም ተመሳሳይ በሆነ ውድቀት ውስጥ ላለመገኘት እንዲጠነቀቁ ያደርጋል። ሰዎችም እግዚአብሔርን መፍራት ይጀምራሉ። በሐናኒያና በሰጲራ የደረሰው ቅጣት በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ነገሩን በሰሙት ሁሉ ላይ ፍርሃት እንዲኖር አድርጓል (ሐ.ሥ. 5፥1-11)።

መ) የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነትና ንጽሕና ለመጠበቅ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመኖቿን ዲሲፕሊን ስታደርግ፥ የቤተ ክርስቲያን ንጽሕናና ምስክርነት ይጠበቃል።

ሠ) የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ (ዶክትሪን) ንጽሕና ለመጠበቅ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ከቃሉ የወጣ ኑፋቄ በመካከልዋ ሆነው የሚያስተምሩትን ዲሲፕሊን ስታደርግና ስታወግዝ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ንጽሕና እንዲጠበቅ ታደርጋለች።

## 4. የቤተ ክርስቲያንን የዲሲፕሊን ርምጃ የሚጠይቁ ሁኔታዎች

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን ርምጃዎች የምትወስደው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲደርሱ ነው።

ሀ) በሁለት ግለሰቦች መካከል ያለው ችግር ሳይፈታ ሲቀርና ጉዳዩ ለቤተ ክርስቲያን ሲቀርብ።

ጌታ በማቴዎስ 18፥15-17 ባለው ክፍል እንዳዘዘው አንድ አማኝ ወንድሙ ከበደለው ሊወስዳቸው የሚገቡት ርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የመጀመሪያው ርምጃ፤ በግል መውቀስ (private reproof) ነው። የተበደለው ሰው በደለኝ ወደሚለው ወገን በቀጥታ ሄዶ ይወቅሰዋል። ቍጥር 15 ላይ «ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው» ይላል። ጉዳዩ የሚመለከተውን ሳያነጋግር ለሌሎች ሰዎች ማውራት፥ ስም



አጥፊነትና መንፈሳዊነት የጐደለው ተግባር ነው። ብዙ ጊዜ እንደተከሰተው፥ የሚመለከተውን ሰው በማናገር ፈንታ ተበደልኩ ብሎ የሰውየውን ስም ማጥፋት ለነገሩ መፍትሔ በማምጣት ፈንታ ችግሩን ያባብሳል።

- ሁለተኛው ርምጃ፤ የግል ስብሰባ private conference ማድረግ ነው፤ ሆኖም **መነጋገሩ መፍትሔውን** ባያመጣ፥ ጌታ ቍጥር 16 ላይ «ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ» ይላል። ሁለት ሰዎች ሆናችሁ ተነጋገሩበት። የሚሆን ከሆነ መልካም፤ የማይሆን ከሆነ ሦስተኛውን ርምጃ ውሰድ።
- ሦስተኛው ርምጃ፤ ለቤተ ክርስቲያን መንገር። ቍጥር 18፥ «እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት» ይላል። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን፥ ጉዳያችንን ይዘን የምናመጣው ወደምንገለገልበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ነው። በሂውስተን ያለውን ችግር ለዳላስ ቤተ ክርስቲያን፥ የአዋሳን ችግር ለአዲስ አበባ ቤተ ክርስቲያን ተናገር ማለት አይደለም። በዚህ ዐይነት ሁኔታ አንድ ችግር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲደርስ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለቱንም ወገኖች በማነጋገር፥ ምስክሮችም በመስማት ጉዳዩን ካጣሩና ከጸለዩበት በኋላ ፍርድ ይሰጣሉ፤ ችግሩን ያስወግዳሉ። አሁንም ያ ሰው ቤተ ክርስቲያንን የማይሰማ ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ የዲሲፕሊን ቅጣት ለዚያ ሰው ትሰጣለች፤ ጉዳዩም ለምእመናን ሁሉ ይነገራል። ያ ሰው እንደ ቀራጭ ይሆናል። ከኅብረቱ እስከ ማግለል ድረስ ቅጣት ሊሰጠው ይችላል።

ለ) የሞራል ኃጢአት ሲፈጸም

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሞራል ኃጢአት መኖሩ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ሲታወቅ ቤተ ክርስቲያን በጉዳዩ ከመከረችና ከተወያየችበት በኋላ እንደ ሁኔታው አስፈላጊውን ቅጣት ትሰጣለች።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአባቱን ሚስት ያገባ አባል ነበር። ይህ ዝሙት ስለሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ምእመናን ጋር ሆኖ የዚህ ሰው ሥጋ ለሰይጣን እንዲሰጥ ነፍሱ ግን እንድትድን የዲሲፕሊን ቅጣት እንደሰጠ 1ቆሮንቶስ 5 ላይ እናነባለን።

አንድ አባል የዚህ ዐይነት ኢሞራላዊ ሕይወት ይዞ ሲመላለስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የቅጣት ዐይነቶች ልትሰጠው

ትችላለች። ያ ሰው የመድረክ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ከሁሉ አስቀድሞ ከአገልግሎቱ ማገድና ማሳረፍ ተገቢ ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቅጣቱን በሽማግሌዎች ጉባዔ ብቻ ልትወስን ወይም እንደ ነገሩ ክብደትና ሁኔታ ልዩ ስብሰባ ጠርታ ለአባላቱ ሁሉ ልታስታውቅ ትችላለች።

ሐ) ትክክለኛ ያልሆነ አካሄድ ሲታይ

አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከቃሉ የወጣ አካሄድ ሲያሳይ፥ መጋቢው ወይም ሽማግሌዎች በግል ጠርተው እንዲቃና ምክርና ተግሣጽ ይሰጡታል። ያንን ዲሲፕሊን የማይቀበልና የማይስተካከል ከሆነ፥ ከዚያ የጠነከረ የዲሲፕሊን ርምጃ ይወስዱበታል (2ተሰ. 3፥6-15፤ 2ጢሞ. 3፥6-7)።

መ) የመንፈስ አንድነትን የሚያናጉና መከፋፈልን የሚፈጥሩ ሲገኙ

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ አንድነትን የሚያናጉና መከፋፈልን የሚያመጡ ሲኖሩ፥ ቤተ ክርስቲያን እነዚያን ግለሰቦች በግል ጠርታ አስፈላጊውን ምክርና ግሣጼ ትሰጣለች። ሆኖም ግለሰቦቹ ከተግባራቸው የማይመለሱና የሚቀጥሉ ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን የዲሲፕሊን ርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ሥልጣን አላት።

> «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፥ በመልካምና በሚያቈላምጥ ንግግርም ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ» (ሮሜ 16፥17-18)።

> «መለያየትን የሚያነሣ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ፥ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሥጽኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ» (ቲቶ 3፥10-11)።

ሠ) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ሲኖሩ

ከቃሉ የሚቃረን የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ ሲኖሩ፥ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ጥራት ለመጠበቅ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ባሉት አስተማሪዎች ላይ የዲሲፕሊን ርምጃ ትወስዳለች (ገላ. 1፥8-9፤ 1ጢሞ. 1፥20፤ 6፥1-5፤ 2ጢሞ. 2፥17-18፤ 2ዮሐ. 10-11)።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የዲሲፕሊን ርምጃ የምትወስደው በመጀመሪያ ከመከረችና ከገሠጸች በኋላ ነው። ሰዎች ምክር የማይሰሙ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ቅጣት መስጠት ትችላለች።



የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ የምትወስዳቸው ቅጣቶች ከአገልግሎት ማሳረፍ፥ ቅዱስ ቊርባን ለተወሰነ ጊዜ እንዳይካፈሉ መከልከልና የመሳሰሉት ናቸው። ምንጊዜም የዲሲፕሊን ዓላማ ለማረምና ለመመለስ መሆን አለበት። በተለይ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያናጉና መከፋፈልን የሚፈጥሩ፥ እንደዚሁም የሐሰት ትምህርት የሚያሠራጩ ሲገኙ ለማቃናት ምክር ከሰጠች በኋላ የማይመለሱ ከሆነ፥ ከአባልነት የመሰረዝና ከእነርሱ ጋር ምእመናን ኅብረት እንዳያደርጉ የማውገዝ ሥልጣኗን ልትጠቀም ትችላለች። ውሳኔዋንም ለአባላቱ በአባላት ስብሰባ ወይም በቅዱስ ቊርባን ሥርዓት ላይ ለማስታወቅ ትችላለች።

ዲሲፕሊን የተደረጉት ከተግባራቸው አለመመለስ ብቻ ሳይሆን፥ በቀጣይነት ወደ ስብሰባ እየመጡ ካወኩ ወይም ከሕግ ውጭ የሆነ እንቅስቃሴ ካደረጉ፥ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ርምጃ ለመውሰድ ትችላለች። ይሁንና እንዲህ ዐይነት የከረሩ ውሳኔዎች ሊወሰኑ የሚገባቸው፥ ከብዙ ትዕግሥትና ጸሎት በኋላ ተስፋ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው።

> «ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፥ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፥ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም። ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፥ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው፤ ከእርሱም የተነሣ፥ አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፥ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል» (ኤፌ. 4፥14-16፥ አ.መ.ት.)።

## አንቺ ቤተ ክርስቲያን

1. ገንዘቡ አድርጎሻል ታላቅ ዋጋን ከፍሎ
ኢየሱስ በደሙ ቀድሶሻል አጥቦ
አሆሆ! አንቺ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ምሥጢር
እግዚአብሔር የለየሽ በአንቺ ሊከብር
　　የክርስቶስ አካል ለመሆን በቅተሻል
　　አንቺ ቤተ ክርስቲያን ጸጋ በዝቶልሻል
　　በዘር መለያየት በአንቺ ዘንድ ቀርቷል
　　ከነገድ ከቋንቋ ሁሉን ሰብስበሻል።

2. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ
ክብርት ተብለሻል በኢየሱስ ሥራ
አሆሆ! የፊት መጨማደድ ጉድፍ እንዳይዝሽ
መንፈስ ቅዱስ ሆኗል የበላይ ጠባቂሽ
　　እጅግ ያማረ ስያሜሽ ነው ብዙ
　　የእ/ር ሕንፃ ሆነሻል መቅደሱ
　　የአምላክ ቤተሰብ ወራሽ አድርጎሻል
　　በጸጋ ላይ ጸጋ ሞገስ አግኝተሻል

3. የገሃነም ደጆች የማይቋቋሙሽ
ለማሠር ለመፍታት ሥልጣን የተሰጠሽ
ማንነትሽን ሊሽር ከቶ ማን ይችላል?
ፅኑ የእውነት አምድ መሠረት ሆነሻል።
　　ለጨለማው ዓለም እውነትን አብስሪ
　　እስኪፈጸም ድረስ የዓለም ተልእኮሽ
　　አንቺ ቤተ ክርስቲያን መብራትሽን አብሪ
　　መራራውን ዓለም ጨው ሆነሽ አጣፍጪ!

4. ቅዱሳን ሁላችሁ ባንድ አካል ያላችሁ
በሰላም ማሰሪያ በፍቅር ቆማችሁ
አሆሆ! የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ጠብቁ
በጠላት አሠራር እንዳትዘናጉ።
　　ኢየሱስ ሊመጣ ሊገለጽ ከሰማይ
　　ጊዜያቱ ተቃርቧል አስተውለን ብናይ
　　ተዘጋጅተን እንቁም እንትጋ ለሥራ
　　የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለ ከእኛ ጋራ

(የመዝሙር ግጥም በው. ዘ.)